# የ ለ ው ጡ ረ መ ጥ የ ታ ሪ ክ ማ ስ ታ ወ ሻ

ከ 1966 እስከ 1968 ዓ ም

ከሻለቃ ጌታቸው የርም

*From the Library of*

***ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ***
***FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES***

ከሻለቃ ጌታቸው የርማ
ዋሽንግተን ዲሲ
[illegible] እና [illegible]
1982 ዓ.ም
1990 © Printed in the U.S.A.

የሽፋን ስዕል ከፋንታሁን
ከርቶም ሱዳን

*From the Library of*
***ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ***
***FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES***

# ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| የኢትዮጵያ መሰዮ ሰበዝ ቅድመ ሁኔታ | 1 |
| የበረና ጦር እንቅስቃሴ | 2 |
| የአዲስ አበባ መኩንኖች እንቅስቃሴ | 3 |
| የገን ጉ ዘማቾች እንቅስቃሴ | 4 |
| የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሰራዊትና ብሔራዊ ጦር | 6 |
| የንጉሡ ከዙፋን መውረድና መታሰር | 8 |
| ንዑስ ደርግና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት | 10 |
| ደርግና ጄ ኔራል አማን አንዶም | 13 |
| ንጉሡ በእስር ቤት ዘመናቸው | 17 |
| የደርጉ የውስጥ ችግር | 19 |
| የነጄ ኔራል ተፈሪ በንቲ አገዳደል | 23 |
| ተወሰበው የቀ ዩ ሁ ኔታዎችና | |
| የኢማሌድህ ግንባር | 27 |
| የሽብር ፈጣሪ ቡድን | 31 |
| የራዛ ዘመቻ | 38 |
| የነበልባል ጦር | 45 |
| በደርጉ ውዥንብር የተፈጸሙ ስህተቶች | 48 |
| የግለሰቦች ሚና | |
| ኮሎኔል ዓለም ዘውድ ተሰማ | 56 |
| ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ | 60 |
| ሌ/ ኮ አጥናፉ አባተ | 63 |
| ሌ/ ኮ ዳንኤል አስፋው | 65 |
| ብ/ ጄ ጌታቸው ናደው | 67 |
| እነ መርዕድ ብሩ | 69 |
| ደጃዝማች ፀሐዩ እንቁሥላሴ | 71 |
| ጄ ኔራል ተፈራ ደኚደስ | 74 |




# ልዩ ማስታዎሻ

በዚህች አነስተኛ በሆነችው መጽሐፍ ላይ የገለፅኳቸው ሁሉ በብዛት የማውቀው ስለሆነ አቀራረቤ ዋናውን አስኳል በቀጥታ በማስቀመጥ እንጂ ለመተቸት ወይም ቃላት ለማሳመር ያደረግሁት ጥረት የለም።

ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት የነበረውን ሁኔታ እያስታወስኩ ለጽፍ በመነሳሴ ብዙ ነገሮች ይታዩኛል። ለሁሉም መጽሐፉን በማንበብ ምን ማለቴ እንደሆነ ሊገባችሁ ስለሚችል ብዙ ትዝታዎች ሊደቀኑባችሁ ይችል ይሆናል ብዬ እገምታለሁ

ይህ መጽሐፍ ከ1966 ዓ.ም እስከ 1968 ዓ.ም የሁለቱን ዓመት ሁኔታ ብቻ የሚያብራራ ስለሆነ ብዙ ነገሮች ይቀሩታል። ግን ወደፊት በአስተያየትና በትችት እንዲሁም በሌሎች አርዕስቶች ላይ በመዘጋጀት ሌላ መጽሐፍ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

ለዚሁም ወደፊት ለማወጣው መጽሐፍ ይረዳኝ ዘንድ ትችት፣ ሀሳብ ወይም ይታከልበት የሚሉ አስተያየቶችን በተገለጸው አድራሻ ብትልኩልኝ በፍፁም ወንድምነት በሜት እየተቀበልኩ ለማስተካከል የሚያስፈልጉትን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ።

ወደፊት ለመዘርዘር የምዘጋጅባቸው ጉዳዮች

- በዚህ መጽሐፍ አስተያየትና ዝርዝር ሁኔታውን በሚመለከት
- ደርጉን ለመጠናከር ከበቀት ምክንያቶች
- ከደርግ ጋር በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የተሳሰሩ ሴቶች የጠሉት ሞንክሬ
- በድንገት የጠቀሱ ነጋዴዎችና የንብረታቸው ክምችት
- መጋለጥ ካለባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ጋር በማከል

ለወደፊቱ እንደገና ከሌላ መጽሐፍ ጋር ስለምመለስ እነዚህን ሁኔታዎች በሚመለከት መገለጽ ያለባቸውን ጥቆማዎች ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ ስለሆንኩ ከላይ እንደገለጽኩት ቢላኩልኝ ደስታዬ ወሰን የለውም።

*P.O. Box 26262*
*Washington D. C., NW 20001*

## ምስጋና።

አቶ ፈንታሁን ጥሩነህ
የስምና ወርቅ መጽሔት ዋና አዘጋጅ ነዋሪነቱ ዋሽንግተን ዲሲ
ሀሳብ በማካፈልና ስጠየቅሁት ሁሉ ሳይታክት ድጋፉን ስለሰጠኝ
ከልብ ሳመሰግነው እፈልጋለሁ።

አቶ ብንያም ጥላሁን
ነዋሪነቱ ሲያትል ዋሽንግተን
ይህንን ጽሑፍ በዳሽን ኢንጅነሪንግ ፕሮግራም በመጠቀም ስለቀረጸልኝና አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ስላደረገልኝ በጣም አመሰግናለሁ።

- የመቶ አለቃ ስምኦን ጥላሁን
- የመቶ አለቃ መስፍን ጥላሁን
- ሌ/ ኮ ንስማየሁ አሰፋው
- የመቶ አለቃ ታሪኩ በላይ

ስለውለታቸው ከልብ አመሰግናለሁ።





## መታሰቢያ

ለአለፉት 15 ዓመታት በአሁኑ ጊዜ ያለውን መንግሥት በመቃወም እያሉ ሲቪሎችና ወታደራዊ አባሎች መስዋዕትነት ከፍለዋል። የሁሉንም ስም ለመዘርዘር የመጽሐፉ ገጽ ስለማይችለው በዚህ ለውጥ መስዋዕት ለሆኑት አራት ሰዎች መታሰቢያ እንዲሆን አድርጊያለሁ። ነገር ግን ከዚህ በታች በስማቸው የገለጽኳቸው አራት ግለሰቦች በፈጸሙት ሙያ ሁሉ የረካሁ በመሆኔና የተለየ ስሜት ስላለኝ ነው።

### በተለይም

፩ኛ/ ሻለቃ ዮሐንስ ኩምሲሽ ሥራ ዊት
አበደና የመኩንኖች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ኮርስ ምሩቅ፤ መንግስቱ ኃይለ ማርያምና ጭፍሮቹ በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ እነ ተፈሪ በንቲን በረሸኑበት ቀን ዶክተር ሰናይ ልኬንና ዋናውን ፋሽስት ኮሎ ኔል ደንኤልን በመግደል፤ መንግሥቱ ኃይለማርያም በሩጫ ከመሰጠው በኋላ ብቻውን ተታኩሶ በመጨረሻ የራሱን ሕይወት በማጥፋት መስዋዕት የሆነ፤ ታሪኩን ከመጽሐፉ ውስጥ ይመልከቱ።

፪ኛ/ የመቶ አለቃ መርዕድ ማሰው፤
የሐረር የጦር አካዳሚ የ13ኛ ኮርስ ምሩቅ የአየር ወለድ ባልደረባ የነበረ በ1966 ዓመተ ምሕረት በነበረው ለውጥ ከፍተኛ ተሳትፎ የነበረው እምባገነኑን መንግሥቱ ኃይለማርያም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትከሻ ለማውረድ በተደረገው የመግደል ሙከራ ተካፋይ የነበረ ነው። ታሪኩን ከመጽሐፉ ውስጥ ይመልከቱ።

፫ኛ/ ሻለቃ ጌታቸው ዮሴፍ
ከአበደና ፖሊስ የአምስተኛ ኮርስ ምሩቅ በተለያዩ ቦታዎች ለሀገሩ ያገለገለ፤ ወታደራዊውን መንግሥት በመቃዎም ፀረ- ሕዝብ ድርጊት አልፈጽምም በማለት ከሰራዊቱ ጫካ በመግባት ፀረ- ደርግ በሆኑ ድርጅት ተሳትፎ በመታገል ላይ እንዳለ፤ በመጨረሻ በነበረበት ድርጅት የመሪዎች ስህተት ምክንያት በደርግ እጅ እንዲወድቅና ህይወቱ እንዲጠፋ ሆነ።

፬ኛ/ የትግል (የሜዳ) ስሙ ኤፍሬም
የትግራይ ክፍለ ሀገር ተወላጅ፤ በጎንደር ክፍለ ሀገር ጫቆ እግን ከዉ በተባለው መንደር በኔ ህይወት ላይ በደርግ በተጠመደ ደፈጣ የተተኮሰብኝ ጥይት እኔን ስቶ በኤፍሬም ላይ ዐረፈ። ጓደኛዬ ኤፍሬም በኔ ምክንያት ህይወቱን አሳልፎ በሰጠ ምንግዜም አልረሳውም። ኤፍሬምን እውነተኛ ስሙን ባለማወቄ ቆራጥነቱንና ጀግንነቱን ለቤተሰቦቹ ለማሳወቅ ባለመቻሌ ከልብ እያዘንኩ ለወደፊት ቤተሰቦቹን ከመፈለግና ከማስረዳት አልቆጠብም።

# መግቢያ

ወደመጽሐፉ ውስጥ ከመግባታችሁ በፊት በቀድሞውና በአሁኑ መንግሥት የነበረኝ ሀላፊነት ላገልጽ እወዳለሁ።

በኢትዮጵያ የፖሊስ ሠራዊት ሻለቃ በመሆን
በፖሊስ ሠራዊት የራዲዮ መገናኛ መምሪያ በሃላፊነት
በፖሊስ ሠራዊት የወንጀል መከላከል በዋና ሹምነት
የወንጀል ምርመራ በጠቅላይ ግዛት ዋና ሹም
የአውራጃና የወረዳ ፖሊስ አዛዥ በመሆን
በአስተዳደር ሹምነት
ራዛ በተባለው በኤርትራ ግዛት ለመዝመት በደርጉ በወጣው ዕቅድ በጎንደር ሁመራ በአዛዥነት
አዲስ በሰለጠነው የነበልባል ጦር በአሰልጣኝነትና በአዛዥነት
ለውጡን ለመቆጣጠርና ለማስተካከል ተብሎ በተፈጠረው አዲሱ የደርግ ፕሮግራም የለውጥ ሀዋርያ በመሆን ሰርቻለሁ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠናቀሩት ሁሉ ከ1966 ዓ ም እስከ 1968 ዓ ም በኢትዮጵያ ውስጥ ስለተካሄደው ለውጥ፤ በተለይም የመለዮ ለባሹን አመጣጥ እውነተኛ በሆኑት ነገሮች ላይ በመመርኮዝ ነው።

በሀገራችን ለውጡ ከመጣም በኋላ መለዮ ለባሹ የመረጠው አስተባባሪ ኮሚቴ (ደርግ) የተሰከበት ዓላማ በሥልጣናቸው በደል የሠሩትን ከቦታው ለማግለል፤ በምትኩም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመርጠውን መንግሥት ለመደገፍ ነበር። አስተባባሪ ኮሚቴ ግን የተሰከበትን ግዳጅና ዓላማ በማጣመም ሥልጣን ከሰፊው ሕዝብ በመንጠቅ ሀገሪቱ አሁን ለደረሰችበት ውድቀት ምክንያት ሆኗል።

በዚህ መጽሐፍ ያሉ ሁኔታዎች በዓይን የታዩትንና በግልጽም ሆነ በሚስጢር የተሠሩትን ድርጊቶች ናቸው። ይህንንም ማስታወሻ ከ12 ዓመት በላይ ከኔ ጋር የቆየ ሲሆን አብዛኛው ማስታወሻ በሀገር ቤት በዘዋወር በጠላት እጅ እንዳይወድቅ በማለት ተበላው ሰቀረ፤ በአሁኑ ጊዜ የዚህን መጽሐፍ ይዘት ሊያሟላልኝ አልቻለም። ወደፊትም ጊዜና ቦታ ሲፈቅድ በሰፊው በተለያዩ ሰዎች ይተረካሉ ብዬ እምናለሁ። እውነተኛውን የሀገራችንን ሁኔታ ለወገን አቅርቦ ማሳየት ግዴታየ ነው ብዬ ስላመንኩ በለውጡም ወቅት በነበረኝ የሥራ ኃላፊነት ይህንን ታሪካዊ ሂደት ለመቅረጽ ብዙ ሙከራዎችን አድርጌአለሁ። የለውጡም ሂደት አቅጣጫውን እየለወጠ ማንኛውም ሥልጣን በደርግ መዳፍ ሥር እየተሰበሰበ ገደብ የለሽ ግድያና እስራት ስለነበረ ሁኔታውን ገምግሜ የግል ውሳኔ መውሰድ ተገቢ በመሆኑ በለመሰለኝና የሚፈጸመውን ግድያና እሥራት እንዲቆም ይጥሩ ከነበሩ የሥራ ባልደረቦቼ ጋር ለጊዜው እራሳችንን አድነንን በውጭ መታገሉ ይበጃል በማለት ከወጡት አያሌ ኢትዮጵያውያን አንዱ ነኝ።





## ክፍል ፩

## 1 የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ቅድመ ሁኔታ።

የኢትዮጵያ ታሪክ ሲነካ ወይም የኢትዮጵያ ችግር ሲተነተንና እድገቷም ጥምር ሲወጋ ከኋላ ሳይጠቀሙ የማይታለፉት ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ለረጅም ዘመናት ኢትዮጵያን ባስተዳደሩበት ወቅት ስተፈፀመት ሁሉ አበይት ነገሮች ታሪክ እያስታወሳቸው ይኖራል። ከፉም ይሁን ደግ አስተዳደራቸው ሊመዘን የሚችለው ከሳቸው በኋላ በሚተካው የአስተዳደር ይዘትና በየጊዜው በሚፈራረቀው ውስብስብ ሁኔታ ነው። ይህም በመሆኑ አንዳንድ ነገሮች ከእሳቸው አስተዳደር ውስጥ ሰንጠቅስ በቀጥታ ወደ ሌላ መግባት ሀሳባችንን አጭር ያደርገዋል።

ንጉሡ በዘመነ መንግሥታቸው ያጋጠማቸውን የስልጣን ተቃዋሚዎች ሁሉ በመደምሰስና በአጭሩ በመቅጨት ለረጅም ዘመን የነገሡ ቢሆንም በጣቂት ፲፱፻፷፮ ዓ ም ህዝባዊና ወታደራዊ አመጽ ለመግታት ከዕድሚያቸው ጋር ዘዴአቸውና ኃይላቸው አብሮ ያረጀ በመሆኑ እንደበፊታቸው ጉልበቱ ለህዝብ ጆሮ ሊሰጥ አልቻለም ነበር። በዚህ መሰረት በ፲፱፻፷፮ የተቀጣጠለው ህዝባዊና ወታደራዊ አመጽ ለእኔ ኃይለ ሥላሴ የመጨረሻቸው እንጂ የመጀመሪያቸው አልነበረም። ነገር ግን አመጹን የተለየ የሚያደርገው ለንጉሠ ነገሥት ሥልጣን መከላከያ የነበረው የመለዮ ለባሹ ክፍል ንጉሡን ከድቶ ከህዝብ ጋር መሰለፍ ነው። በዚህም መሰረት የንጉሡ የረጅም ጊዜ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ህዝብ ትከሻ ላይ እንዲወርድ መለዮ ለባሹ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል።

የመለዮ ለባሹ ንቅናቄ በለውጡ ውስጥ ሚና እንዳለው የተረዱ አያሌ ኢትዮጵያዊያን ከጎኑ ተሰልፈው ድጋፍ በመስጠት ወደር፤ ውጋ ንቀል ሲሉ በጅተዋል። መለዮ ለባሹ የኢትዮጵያ ህዝብ አካል እንደመሆኑ መጠን በህዝቡ የደረሰው በደልና ጭቆና ሁሉ በምንም ተነጥሎ አይታይም። በተለይም በዚህ ወቅት የወታደሩ አመጽ እየተባባሰ የመጣው በማዕረግ፣ በንብረት ከበርቴዎችና ከተራው መለዮ ለባሽ ርቀት የነበራቸው አለቆች በነበረው መንግሥታዊ መዋቅር ድጋፍ ስለነበራቸው የአስተዳደሩ በደሎች በወታደሩ ላይ ከፍተኛ ችግር በመፍጠሩ ነው።

በተለይ የወታደሩ ችግር ጎልቶ ይታይ የነበረው እስቀም ወደ ፷፮ ዓ ም ገደማ የማይገረሰስ ኃይል እንዳላቸው በማስመሰል ከነሱ በታች ለነበሩ የሠራዊት አባላት ሁሉ አስተዳደርና ዓላማ ያገኙቸው የአንድ ቤት ሰብ አባሎች መሆናቸውን የረሱ ነበሩ። ዘመኑ እየተለዋወጠ ሹሞች እየተቀያየሩ ቢመጡም ወታደሩ ኑሮውን የሚገፋበት የቀበሌና የደመወዝ ጭማሪ የሚያገኝበት ዘዴ ባለመፈጠሩ ለዘመናት ተቸግሯል። ስለዚህ በደረሰው የወታደሩና የሲቪሉ ሰንል ችግሩ ጎልቶ ይታይ የነበረው በሁሉም አቅጣጫ እንደነበረ እንረዳለን።

በዚህም የለውጥ ዋዜማ ሰሞን የአለቃና የጭፍራ ግንኙነት፣ የጌታና የባሪያ አሰራር መልክ ይዞ የነበረው በመቀየር መጠነኛ ግንኙነት እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ እብርም እንዲያብር ረድቶታል። የንጉሡ ኃይል የኢትዮጵያን ህዝብ በቁጥጥሩ ስር ለዘመናት ያቆየ ቢሆንም አሁን አርጅተውና እፍጅተው ንጉሣዊ መዋቅራቸው በግንበሩ ሲደፋ ሲታረብ የእባቸው ህይወት ከማለፉ በፊት ግርግዳና ማገር ሆኖ የቆየ መሣፍንትና መኳንንት እንዲሁም በጠቀሰሰው ባላባታዊ ስርዓት ተርበደበደ። የመኖር ህልውናቸው ከንጉሡ ህይወት ጋር አድርገው የቆዩ ሁሉ ንጉሡ አፈር ከመቀመሳቸው በፊት የነሱ ህልውና ቀድሞ ተደመሰሰ፤ ታሪካቸውና ህይወታቸው ተቀበረ።

እንደያውም ንጉሡ ነገሥቱ ከዚህ በኋላ በድዳቸው ለመግዛት አብረዋቸው የነበሩትን ሁሉ ርግፍ አድርገው ትተው እራሳቸውን ወደ አዲሱ ትውልድ ለማስገባት ያደረጉት ሙከራ ቀላል አልነበረም። ዘላለማዊ ህይወት ዘላለማዊ ኃይል ሊኖር አይችልምና አዲሱን እቅዳቸውን ከግቡ ለማድረስ ሁለንተናዊ ሁሉ ጠባብ እየሆነ በለመጣ ወደዱም ጠሉም በህዝባዊ ማዕበል ማግ ውስጥ መስመጣቸው አልቀረም። ስለዚህ ይህ የተወሳሰበ ሂደት እውን ሆኖ የየካቲት ወር ህዝባዊና ወታደራዊ እመጽን ፈጠረ።

## 2 የበረናው ጦር እንቅስቃሴ።

ኰሎኔል ፍቅሩ ወልደ ትንሣይ የበረና ነገሌ ጦር አዛዥ ሆነው ሥራቸውን ለመጀመር ወደ በረና ሄዱ። ወዲያውም ውለው ሳያድሩ እንደገና ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ከተለያዩ የጦር ባለሥልጣኖች ጋር በመገናኘት የጦሩን ችግር አስረዳለሁ ማለታቸው ስለተሰማ የደመወዝ ጭማሪ ለማግኘት የሚጓጓው በአካባቢው ያለው ጦር የኰሎኔል ፍቅሩን የመጨረሻ ሁኔታ ሲከታተል ሰንብቷል። ምክንያቱም ወታደሩ የደመወዝ ጭማሪ ለማግኘት ጥያቄ ስለነበረው ነው።

ኰሎኔል ፍቅሩ ግን ምን እንዳደረጉ ሳይሰማና ሳይታወቅ በመጡበት እኪሄን ወደ በረና ነገሌ ሄዱ። የኰሎኔል ፍቅሩ ሁኔታ አልታወቀም እንጂ የበረናው ጦር እስቃው በተመለሱ ማግስት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን በመቋጠር መፍትሄ እንዲሰጠው የመከላከያ ሚኒስተር የነበሩት ጄኔራል ከበደ ገብሬን እንዲያነጋግሩት ጥሪ አድርጉ ነበር። የአዲስ አበባ ባለስልጣኖችም ጄኔራል ከበደን አስቀርተው የምድር ጦር ዋና አዛዥ ጄኔራል ድረሴ ዱብአለን ሄደው እንዲያነጋግሩ ወደ በረና እነቃነቃቸው።

ጄኔራል ድረሴ በረና እንደደረሱ ከጦሩ የቀረበላቸው ጥያቄ መሸከም አልቻሉምና በጦሩ ዘብ መደብ ተቀምጠው ውሲኒያቸውን እንዲጠብቁ ሆኖ በሠራዊቱ ታሪክ የመጀመሪያ በመሆን ለንቅናቄው ዋዜማ ግንበር ቀደም እስረኛ ሆኑ። ንጉሡ የሚያውቁትን ያህል ቢያውቁም ከሌሎች ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን በደረሰው ሽብር ጄኔራል ድረሴን





አስፈትተው ጦሩ ያጋጠመውን ችግር እንደሚወገድ አስረድተው እንዲመለሱ የአየር ኃይል አዛዥ ጄኔራል አበራ ወልደማርያምን ላኩቸው። ጄኔራል አበራም ጦሩን አግባብተው እስረኛ የነበሩት ጄኔራል ድረሴን አስፈትተው ሲመለሱ ይኸንን ጊዜ እኔም ቤት እሳት አለ በማለት የአየር ኃይሉን የወደፊት አመጽ ተነበዩ። እንደፈሩት አልቀረም አዲስ አበባ እንደደረሱ ጥያቄን የሆነ ምክንያት በመፍጠር የአየር ኃይሉ የውስጥ ለውስጥ እንቅስቃሴ ቀጠለ።

## 3 የአዲስ አበባ መኰንኖች እንቅስቃሴ

በመጀመሪያው የካቲት ፳፮ ቀን ምሽት ሹሞች ንቅናቄ ጊዜ በአሥመራ ፪ኛ ክፍለ ጦር መኰንኖችን አስረው በማስታየታቸው ምክንያት ሁኔታውን በመቃወምና እንዲሁም በሠራዊቱ ውስጥ ለነበሩት አያሌ ጥያቄዎች መፍትሄ ለመፈለግ አዲስ አበባ በሚገኘው ሸላሚክ ውስጥ በተወሰኑ መኰንኖች የሚሰጥር «የሜክ» ስብሰባ ተጀመረ። በስብሰባውም መጨረሻ ላይ በመኰንኖች ክበብ ውስጥ በደፋ እንዲደረግ ተስማምተው በዚሁ ስብሰባ ላይ ከመቶ በላይ የሚሆኑ መኰንኖች ተገኝተው ነበር።

በዚህ ስብሰባ ላይ የሚያስተባብር ኮሚቴ መሰየም አለበት ተብሎ በስተወሰነ ለመጀመሪያ ጊዜ በኮሚቴ የሚመራ ንቅናቄ ጥንስስ የሆኑት አምስት ሠዎች ተመረጡ፤ እነሱም ከዚህ በታች በማቸው የተጠቀሱት ነበሩ።

1 ኰሎኔል ዓለምዘውድ ተሰማ
2 ሻለቃ ሽመልስ መታፈሪያ
3 ሻለቃ ተፈራ ተክለአብ
4 ሻለቃ አጥናፉ አባተ
5 ሻምበል እንዳለ ተሰማ

በዚህ እለት ይህ ኮሚቴ የወሰደው እርምጃ ቢኖር፤ የሚቀጥለው ስብሰባ በሚደረግበት ጊዜ ቁጥራችን እንዲጨምር በርከት ያሉ መኰንኖችን ለማሰባሰብ ወረቀት ተጽፎ በጥታው ላሉ ለልዩ ልዩ ክፍሎች እንዲበተን ሁሉንም ለማዳረስ እንዲረዳና አሁን ያሉትንም ለማወቅ እንድንችል እዚህ ያላችሁ በማችሁን ስጡን ሲባል ብዙዎች ሽልክ እያሉ ወጥተው ሄዱ።

ይህንን ስብሰባ የሚቃወሙም አልጠፉም ነበር። ለምሳሌ የክብር ዘበኛው አዛዥ የነበሩት ጄኔራል ታፈሰ ስብሰባ እንዲይደረግ በለተቃወሙ ከክብር ዘበኛ የተጋበዙት መኰንኖች በነቸው ማስፈራራት ስብሰባውን ሳይካፈሉ ቀርተዋል።

በሁለተኛው ስብሰባ ጊዜ ግን ብዙ መኰንኖች በለተገኙና ደመቅ ያለ በመሆኑም ተጨማሪ አባል እንዲመረጥ ተደርጉ ሻለቃ ጥበበ መንክር ጠሚቴው አባል ሆኖ ተመረጠ። የመለዮ ለባሹ ንቅናቄ በዚህ እንዳለ እዯ እክሊሉ ሀብተወልድ ከሥልጣን ወረዱና ውስጥም

ሳያደሩ ካቢኔ ሚኒስትሮችና የጦር መሪዎችም ሳይቀሩ ተይዘው መታሰር ጀመሩ። በአቶ አክሊሉ ምትክ ጀኔራል አቢይ አበበ ጠቅላይ ሚኒስተር ሊሆኑ ነው እየተባለ ሲወራ ቆይቶ ባልታወቀ ምክንያት ሊሊቱን ተቀይሮ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ሹመቱን ወሰዱ።

በዚህ ወቅት ፦

ጀኔራል አቢይ አበበ የመከላከያ ሚንስተር
ጀኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ የጦር ኃይሎች ኢታማጆር
ጀኔራል ታደሰ መልኬ የ፬ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ
ጀኔራል ተፈራ ባንቲ የ፬ኛ ክፍለ ጦር ምክትል አዛዥ

ሆነው ተሾሙ። ጀኔራል አቢይ ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት የኔንን የመከላከያ ሚንስትርነት ትቀበላላችሁ ወይ ብለው ስለጠየቁ ጦሩም በአንድ ድምፅ እንደሚደግፋቸው ስላረጋገጡ ሥራቸውን ጀመሩ።

የጦር ኃይሎች ኢታማጆር ሆነው የተሾሙት ጀኔራል ሀይሌ ግን ሐረር ያለው የ፫ኛ ክፍለ ጦር ባልደረቦች በጠየቁት መሰረት በኮሚቴው ተይዘው ታሰሩና በምትካቸው ጀኔራል ወልደሥላሴ በረካ ተሾሙ። በጠቅላይ ሚኒስተር እንዳልካቸው ለሁለተኛ ጊዜ የተቋቋመው ኮሚቴ በሕግ ተደንግጎ የምርመራ ኮሚሽን በመባል በመከላከያ ሚንስቴር ሥር እንዲውል አደረጉ። በዚህ ጊዜ የፈጥኖ ደራሽ አዛዥ ብ/ ጀ ሙሉጌታ ወልደዮሐንስ፤ ከፖሊስ ኮሎኔል ፈለቀ ታቦርና ሌሎችም ተጨምረው ኮሚቴው እንደጠናከር ተባለ።

## 4 የኮንጎ ዘማቾች ጥያቄ

ከአንደኛ እስከ አራተኛ ጠቅል ብርጌድ ኮንጎ ዘምተው የነበሩት የሠራዊቱ አባሎች ከተባበሩት መንግሥታት የተፈቀደላቸውን ገንዘብ የኢትዮጵያ መንግሥት አልከፈለም በማለት ለብዙ ዘመን ሲጨቃጨቁ ቆይተዋል። በለውጡ ወቅት ሁሉም ችግሩን የሚገልጽበት ጊዜ ስለነበር ይህንን ሁኔታ በመጠቀም የኮንጎ ዘማቾች የተፈቀደልን ገንዘባችን ይሰጠን አሉ። ከዚህ በፊት ሦስት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች የተሰየሙበት ኮሚቴ ጉዳዩን አጥንቶ ሊከፈላቸው አይገባም ብሎ ወስኖ ነበር። በኮሚቴውም ውስጥ ጀኔራል አቢይ አበበ የመከላከያ ሚንስትሩ ይገኙበት ነበር።

የዘማቾች ግንባር ቀደም የነበረው የሻምበል ባሻ ፀሐዬ የራስ አስራት ካሣ ዘመድ ነው ይባላል።

የአልፍኝ አስከልካዩ ጀኔራል አሰፋ ደምሴ ለመከላከያ ምኒስተሩ ለጀኔራል አቢይ ስልክ ደውለው አርባ የሚሆኑ የኮንጎ ዘማቾች ቤተ መንግሥት እንዲቀርቡ ከቤተ መንግሥቱ የታዘዙ መሆኑን ገለጹላቸው። ነገሩ ሀሰት ከመሆኑም በላይ ለተንኰል የተወጠነ ነበር። ሆኖም በትዕዛዙ መሰረት ወታደሮቹ በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ ገብተው





እንዲጠባበቁ ተደረገና ጀኔራል አቢይ በአስቸኳይ ተጠርተው ቤተ መንግሥት እንዲገኙ ሆነ።

ጀኔራል አብይ ከጃንሆይ ጋር በምን ነጥብ ላይ እንደተነጋገሩ አይታወቅ እንጂ ብዙ ሰዓት ቆይተው ወጡ። ጃንሆይም ወደ ሥራ ለመሄድ ብቅ ሲሉ ወታደሮች ተሰልፈው ተመለከቱና ምንድናቸው ብለው ጠየቁ። የኮንጎ ዘማቾች መሆናቸውና ችግራቸውም ምን እንደሆነ በአጭሩ ተዘረዘረላቸው፤ ሳያመነቱ «ይህ ጉዳይ ቀደም ብሎ ተወስኖ የለም እንዴ? አሁን ምን አዲስ ጉዳይ ተፈጠረ?» በማለት ተቆጡና ጉዟቸውን ቀጠሉ። ይህን ጉዳይ የመኳንንቱና በመሳፍንቱ ዙሪያ የተጠነሰሰ ሴራ እንጂ ንጉሡ ጨርሰው የሚያውቁት ነገር እንዳልነበረ እንረዳለን። ከዚህም ሌላ ራስ እሥራተ ካሣ በበኩላቸው ራሳቸውን በሚመለከት የሚጫወቱት ሚና እለ ስለሚባል ቀጠሮቸው ነው በሚባለው ባሻ ፀሐዬ እየተጠቀሙ በኮንጎ ዘማቾች አማካኝነት ብጥብጡ ቀጠሉ በንጉሡም ሆነ በመኳንንቱና በመሳፍንቱ መካከል ለምምነት እንዲደፍር ጥረት እንደነበራቸው ተገምቷል። ጀኔራል አቢይም ጠቅላይ ሚኒስተር ይሆናሉ እየተባለ ይወራ ስለነበር በዚህ ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት የተሞከረ ሤራ እንደነበር ቢገመትም በዚህ ጉዳይ ውስጥ እጃቸውን ያስገቡ ሁሉ የጠነሰሱት ሤራ እንዳሰደናቸውና እንዲያውም ችግሩን የበለጠ እንዳፈጠነው ይገልጻል። በዚህ አይነት የኮንጎ ዘማቾች ጉዳይ ከተወሰነ በኋላ ወታደሮቹ ከቤተ መንግሥት በቀጥታ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር በመሄድ በክፍለ ጦሩ ውስጥ ለሚገኘው ኮሚቴ በማመልከት በበለጠ ችግሩ እንዲባባስ በማድረግ ጀኔራል አቢይ እንዲታሰሩላቸው አመለከቱ። ጀኔራል አቢይም ጉዳዩን ሰምተው ሥራቸውን በመልቀቅ ለመደበቅ ሞከሩ፤ ቢሆንም በኋላ ተይዘው ታሰሩ።

## የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር የወጥታ ኮሚቴ መቋቋም።

በግንቦት 1966 ዓ ም በ፬ኛ ክፍለ ጦር ቅጥር ግቢ ውስጥ በ፬ኛ ክፍለ ጦር አባሎችና በክንፉ ዘማች ወታደሮች ተባብረኑት ተቋቋመ። አዲስ አበባ እና በአካባቢው ለሚገኙ የጦር ክፍሎች በሻለቃ ተፈራ ተክለአብ፣ ኤርክራፍትማን ዮሐንስ ፍቅዱ እና አንድ ከመሀንዲስ የመጣ የበታች ሹም አማካኝነት ጦሩ ወኪል እንዲልክና እንዲተባበር ለማስረዳት ሲዘዋወሩ እመሹ። በማግስቱም በሻለቃ አጥናፉ አባተ አስተባባሪነት ከሻለቃ በታች የሆኑ መኰንንና አንድ የበታች ሹም ከየክፍሉ እንዲሰክ በተጠየቀው መሰረት ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር መምጣት ጀመሩ። አንዳንድ ክፍሎች ደግሞ ሁኔታውን በግልጽ ባለማወቃቸው በተባለው መሰረት አንድ መኰንንና ሌላ የበታች ሹም መርጠው ላኩ። ነገር ግን አንዳንድ ክፍሎች ሁኔታው ስላልገባቸው የተላኩት አባሎች ሁኔታውን ብቻ አጣርተው እንዲመለሱ ቢላኩም ከኮሚቴው ከደረሱ በኋላ ምስጢር እይተጥልና አይመለሱም የሚል መልስ ከተሰጠ በኋላ የደርግ አባል ሆነው እንዲቀሩ ሆነ።

ይህ ኮሚቴ የተፈጠረው የክብር ዘበኛ ወኪሎች ሳይላኩ ነበር። ሆኖም ከአራተኛ ክፍለጦር ጉን መሿለኪያ አጠገብ ያለው የቤተ መንግሥት ጠባቂ ሦስተኛ ብርጌድ ለመጀመሪያ ጊዜ ተወካዮቹን ላከ።ይህም የነበረውን ጭንቀት ቀሰቀሰው፤ ከሁለት ቀን በሂላም የቀሩት የክብር ዘበኛ ብርጌድ አባሎች ተወክለው መጡ። በየክፍለ ሀገሩም ያለው የጦር ክፍል አባሎቹን እንዲልክ ቴሌግራም ተላለፈ።

ሐረር ከተማ አካባቢ የነበረው የሦስተኛ ክፍለ ጦር ል ዑ ል ዑ ክፍሎች ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምንና የሀምሳ አለቃ ለገሠ አስፋውን በዚሁ በግንቦት ወር 1966 ዓ ም ወደ አዲስ አበባ ላከ። ሁሉንም የመለዮ ለባሽ የሚወክሉ አባላት ወደ ስምንቱ መጨረሻ መጡ። በመጀመሪያም ጋባዥ በነበረው ክፍለ ጦር በአራተኛው ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ ስለሆነ ስብሰባው የሚካሄደው ሻለቃ አጥናፉ አባተ በሊቀ መንበርነት ሲመራ ቆየ። ሻለቃ መንግሥቱ ከመጣ በኋላ ደግሞ ሁሉም የመለዮ ለባሽ ወኪሎች ሳይገኙ የተካሄደው ምርጫ ትክክል አይደለም በማለት በሰመለከተ ድጋሚ ምርጫ ተካሄዶ ሻለቃ መንግሥቱ ሊቀመንበር ሻለቃ አጥናፉ ምክትል ሆነው ግንቦት 1966 ዓ ም ተመረጡ።

የዚህ ኮሚቴ አላማ «ከንጉሡ በታች ለሀገሪቱ እንቅፋት የሆኑትን ባለ ሥልጣኖች ለማጽዳት» ነበር። አላማውም በጥቂር ሰሌዳ በአራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ተጽፎ ነበር። ይህ ሁሉ ሁኔታ የሚርግር ጊዜ ስለነበር ቀን ከቀን በብዛት ባለ ሥልጣኖች እየተያዙ መታሰራቸው ቀጠለ። ለዚህ ንቅናቄ መቋቋምም ከፍተኛ አስተዋጽዖ የከፈለው ሻለቃ ተፈራ ተክለአብ የተባለው ከአዲስ አበባ ወደ ሐረር ሄዶ ለክፍለ ጦሩ አባላት ልወክሉችሁ የምችለው እኔነኝ፣ እንደናንተው እንጋራ እንጃራ በልቸ ያደግሁ በመሆኑ፣





የፈረንጅ እንቁላል እየበላ እንግሊዝ አገር ያደገ አይደለም፤ በማለት በጊዜው የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስተር እንዳልካቸውን በመጠቆም አሸሟጠጠ።

ሻለቃ ተፈራ ተክለአብ በመጀመሪያው የስብሰባ ቀን ንጉሡ መስቀል አስባቸው በማለት የተሰበሰቡትን አባላት ከዳራቹ ሸሽተው እንዲወጡ ያደረገ ሰው ነው። ሐረር ያለው የሦስተኛ ክፍለ ጦር ወታደሮች በሻለቃ ተፈራ የግል ፍላጐት ባለመደሰታቸው ያቀረቡላቸውን ሀሳብ ሁሉ አልተቀበሉትም። በዚህም መሰረት አዲስ አበባ ሲመለስ ተይዞ ያለፍርድ ለብዙ ዓመታት ታሰረ።

በመጀመሪያ ቀን ይህ ኮሚቴ አዲስ አበባ ስብሰባው ሲጀመር በጊዜው የምድር ጦር አዛዥ የነበሩት ብርጋዲር ጄ ኔራል ግዛው በላይነህ ለኮሚቴው መቋቋሚያ እንዲሆን ከምድር ጦር ካዝና ሽሺ ብር ፈቀዱ። ሁኔታዎችም ውስጥ እያደሩ ሲሄዱ ኮሚቴው እንዲጠናከር አደረገው። ሠራዊቱ ከነበረው ከተለመደው የዕዝ ሰንሰለት ከመከላከያ ሚኒስተር ትዕዛዝ ውጭ በሌላ መልክ ደርግ ተብሎ ተቋቋመ። ይህም ሁኔታ በጊዜው ብዙ ችግር ፈጠረ። የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስተር እንዳልካቸው መኰንን የጥምር መንግሥት ለመመስረት ቢሞክሩም ይህ ኮሚቴ (ደርግ) ፈቃደኛ አለመሆኑን ገለጸ።

መለዮ ለባሹ፣ ደርግ የተባለው ቡድን በመጀመሪያ የላከው ለተወሰነ ስራ ስለሆነ ወደ መጡበት ክፍሊ እንዲመለሱ በምትካቸውም ደምበኛ ምርጫ እናካሂዳለን ብሎ ኮሚቴውን (ደርግን) ቢጠይቅ ምስጢር ስላወቅን ወደ ክምፕ እንመለስም በማለት እምቢ አሉ። በምትካቸውም ማንኛውንም ጉዳይ የሚፈጽመው በየበታው ንዑስ ደርግ ተቋቋመ። ከሐረር ከጅጅጋ ከኦጋዴን ያለው ጦር ሻለቃ መንግሥቱ ወደ አዲስ አበባ የተላከው በሐረር ከተማ አካባቢ የሚገኘው ጦር ጄ ኔራል ሀይሌ ባይከዳኝ እንዲያዙ በተደረገው ስምምነት መሰረት ስልሆነ ሻለቃ መንግሥቱና ፃ አለቃ ለገሰ አስፋው የሦስተኛ ክፍለ ጦር በሙሉ የወከላቸውና የተሰማማባቸውን አባሎቹን መለክ አለብን በማለት ጦሩ ያቀረበው ጥያቄ በሻለቃ መንግሥቱ እምቢተኝነት ሳይሳካ ቀርቷል።

ጄ ኔራል ሀይሌ ባይከዳኝ የሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩት ሻለቃ መንግሥቱ በግል በድለውኛል በማለት ለውጡን እስመልክቶ የጦሩንና የህዝቡን እንቅስቃሴ መጠቀሚያ በማድረግ ሐረር ከተማ የሚገኙትን ወታደሮች እሳደው ጄ ኔራሉ እንዲታሰሩ ከፍተኛ ግፊት ያደርግ ነበር። በመጨረሻም ሀሳቡ ስለተሳካለት ጄ ኔራሉ ከ60 የቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር ከተኙበት ሆስፒታል እስ ጉትቶ እንዲገደሉ አድርጓል። –




ሌ/ጀ ሀይሌ ፡ ባይከዳኝ



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ



## ክፍል ፪
## የንጉሡ ከዙፋን መውረድና መታሰር።

ንጉሠ ኃይለ ሥላሴ በ1966 ዓ ም በየካቲት ወር ለፈነዳው ታሪካዊ ለውጥ አስተዋጽዖ እንዳደረጉ ተደብቀው የቀሩ ምስጢሮችና በግልጽ የታዩት ግብረኛዎች ይጠቁማሉ። ይህንን አስመልክቶ ወደፊት ከሚያጋጥመው ችግር ነፃ ለመውጣትና እንደገናም ከአዲስ ትውልድ ጋር ለመቀጠል ይመስል ነበር። በተለይም የመታደሩን ክፍል በመያዝ እሳቸውን አቅፎ በሰለው ላይ ያሸውን እንዲፈፅም ድጋፍ በመስጠት ያከናዱትን ጥበብ ያልተረዳ አልነበረም። ያልተረዱም ቢኖሩ በነቸው ኃይል የሚንቀሳቀሱ መሣፍንትና መኳንንት እንዲሁም የጦር አለቆቻቸው ነበሩ። ነገር ግን ከነበሩት ከፍተኛ የጦር አዛዦች ውስጥ የክብር ዘበኛው አዛዥ ጄኔራል አበበ ገመዳ ለንጉሡ ታማኝ በመሆን የንቅናቄውን መሪዎች እደመስሳለሁ ብለው በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ ንጉሡ ተው እርፈህ ተቀመጥ ከኛ ፈቃድ አንችም ነው በማለት ከከለከሏቸው በኋላ ከሥልጣናቸው አውረደው እንደታሰሩ ሆነ።

ቃል ኪዳን ሆኖ ሳይታወቅ ምስጢር ተደብቆ ይቆር እንጂ በየቦታው የተነሳው የጦሩ እንቅስቃሴ በዱብዕዳ የተወለደ አልነበረም። ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች የአንዳንድ ወታደራዊ ግለሰቦች ከንጉሡ ጋር የተያያዘ ግንኙነት እንደነበራቸው ለመግለጽ እንሞክራለን።

ኮሎኔል ዓለምዘውድ ተሰማ የአየር ወለድ አዛዥ የነበረውን ገድሉ፣ ያሰረውን እስር ሥልጣን እንዲጨብጥ የተደረገው መከራ ቀላል አልነበረም። ኮሎኔሉ ግን ይህንን ዘዴ አልተጠቀመም። ሆኖም ጄኔራል አቢይ ደምሴና ብዛታ እደግሙ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ኮሎኔሉን ይገፉ ነበር።

አሁን በሥልጣን ላይ ያሉና የተገደሉም መኮንኖች ከንጉሡ ጋር ከፍተኛ ቤተ እንደነበራቸው አይዘነጋም። ለምሳሌ ያህል የአየር ኃይሉ ባልደረባ ሲኒየር ቴክኒሺያን ግርማ ዘለቀ የአየር ኃይል ጦር ንቅናቄ ባደረገበት ጊዜ ግንባር ቀደም በመሆን ለተጀመረው እንቅስቃሴ መስበት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረገ ቢሆንም ለንጉሡም ቅርብ መሆኑ ይሰማ ነበር። ሻምበል ብሩ አርአያ የተባለው የአየር ወለድ ባልደረባ በዚህ ወቅት አየር ወለድን ያስተባብርና ያሰማራ የነበረ በቀጥታ ከንጉሡ ጋር ግንኙነት እንደነበረው ምልክቶች ነበሩ። ለማስታወስ ያህል ይህ ሰው ከጓደኞቹ ጋር የሞጆን ባንክ ዘርፈሃል ተብሎ ተገደለ። ሻምበል አጫሉ ኑር የተባለው የአየር ወለድ የአስተዳደር መኮንን የነበረው ከንጉሡ ጋር የቅርብ ግንኙነት እያደረገ ለውጡ በንጉሡ ቁጥጥር ስር እንዲቆይ ይጥር የነበረ መኮንን ነበር። ያደረገው መከራ ባይሳካለት ሲቀር ወደውጭ ለመውጣት በጎንደር በኩል መከራ አድርጎ ሳይሳካለት ስለቀረ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ ታሰረ።

እነዚህ በቅርብ የተደረሰባቸው እንጂ ከከፍተኛ መኮንኖች እስከ ተራ ወታደሮች በሚስጢርና በቀጥታም ከንጉሡ ጋር ይገናኙ የነበሩና በመጨረሻም ደርጉ ደርሶባቸው እርምጃ

የተወሰደባቸው ብዙዎች ናቸው። እንግዲህ ይህንን የመሰሰሉ ነገሮች እንደሚያመለክቱት ንጉሠ ነገሥቱ ሁኔታውን ለመቆጣጠር እስከ ተራ ወታደሩ ድረስ በመውረድ ይጥሩ እንደነበር ነው። ነገር ግን በዙሪያቸው የተኮለኮሉት ባለሥልጣኖች ሁሉ በስቸው ጥላ የሚኖሩ እንደመሆናቸው መጠን ንጉሡን ለማገዝ የአደረጉት አንድም ጥረት አልነበረም።

ይህ ሁሉ የንጉሡ ጥረት የጸጥታውን ኮሚቴ ከፍተኛ ቢጋት ላይ ስለጣለው ያወቃቸውን ሰብስቦ ሊያስር የመለጡትና ያልታወቀባቸው ተደብቀው ቀርተዋል። ንጉሡም በዚህ መንገድ አልበከ ቢሏቸው የእልፍኝ አስከልካያቸው በጀ ኔራል አሰፋ ደምቤና በንጉሡ የቅርብ አገልጋይ በብላታ አድማሱ ረታ አማካይነት ከፍተኛ ገንዘብ ወደ ጉጃምና ጎንደር በመላክ ህዝቡን ለማሸፈትና ሁውከት ለመፍጠር ጥረት እያደረጉ ነው ስለተባለ ጀ ኔራል አሰፋ እጃቸውን እንዲሰጡ ተጠየቁ።

የተወሰኑ የደርግ አባላትና የክብር ዘበኛው የንዑስ ደርግ ሊቀመንበር የነበረው ሻምበል ደምሴ ጀ ኔራል አሰፋ እጃቸውን እንዲሰጡ ንጉሡን ጠይቀው ጀ ኔራሉን አሳልፈ እልሰጥም ስላሉ የክብር ዘበኛው የንዑስ ደርግ በጊዜው የክብር ዘበኛ አዛዥ የነበሩት ጀ ኔራል ታፈሰ ከቤተ መንግሥት ጀ ኔራል አሰፋ ታፍነው እንደወጡ ለዘበኞችና ለእንጋቾች ትዕዛዝ እንዲሰጡ ተጠየቁ። ጀ ኔራል ታፈሰም ወዲያቸው እንዲታፈኑ ፈቃድ ሰጡ። ጀ ኔራል አሰፋም በክብር ዘበኛው ንዑስ ደርግ አባላትና በእንጋቾች አንገጫቸውን በጡጫ ተመተው ከቤተ መንግሥት ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር እስር ቤት ወረዱ።

አሁን የቀሩት ብላታ አድማሱ በመሆናቸው ተጠራጥረው ወደ ትውልድ አገራቸው ጎንደር ሲያመሩ በሥልጣን ሆነው ያልጎበኙት አገር፤ ቀደም ብለው ያልረዱት ዘመድ መሽጉጫ ሊሆን አይችልምና ገራ ሲገባቸው ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ በመመለስ እጃቸውን ለፀጥታው ኮሚቴ ሰጥተው ታሰሩ። ከዚህ በኋላ የንጉሡ ቤተ መንግሥት ስለአደ እንደልብ በመግባትና በመውጣት ሁሉንም መቆጣጠር ስለተቻለ የሚቀጥል ስራ ቢኖር ከንጉሡ የገንዘብ ክምችት ለማግኘት ስለነበር ኮሚቴው ንጉሡን ሲያስቀይማቸው የለሰለሰ ግንኙነት በማድረግ በቀድሞው ጓደኛቸው በራስ እምሩና በግቢ ሚኒስትር በደጃዝማች ከበደ ተሰማ አማካኝነት መለማመጡን ቀጠለ። ንጉሡ ግን አሻፈረኝ አሉ።

እራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ለንጉሡ የረጅም ጊዜ ጓደኛ በመሆናቸው ያሳቸውን ያህል እምነው ቀንጥረው እንዲሰጡ ያደረጉት ጥረት ሁሉ ከንቱ ሆኖ ስለቀረ ይህንኑ ለኮሚቴው አስረድተው ዘወር አሉ። ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ግን ከእሁኑ መንግሥት ጋር እራት መንግሥት ሲያገለግሉ የኖሩ በመሆናቸው የነገሥታቱን ወይም የቤተ መንግሥቱን ተንኮል ጠንቅቀው በማወቃቸው በቀላሉ ወደቤታቸው መመለስ አልፈለጉም። የአፄ ምኒልክ የንግሥት ዘውዲቱ የንጉሥ ኃይለ ሥላሴ አድራጊ ፈጣሪ እንደነበሩ ከታሪካቸው መረዳት ይቻላል።

ደጃዝማች ከበደ ከንጉሡ ገንዘብ እንደማይገኝ የገባቸው መሆኑን ቢያውቁም ንጉሡ





ከመንበራቸው ገለል እንዲሉ አድርገው ፀጥታው እንዲረጋጋ አገር እንዳይፈርስ ሁሉም ነገር የተቃና እንዲሆን በመኳንንቱና በመሣፍንቱ እንዲሁም በጦር አዛዦች ላይ ምን መደረግ እንዳለበት ጥበባቸውን ሲያካፍሉ ቆይተዋል። ይህ ሁሉ ሲፈጸም በደጃዝማች ከበደና በሸለቃ መንግሥቱ መካከል ያለው ግንኙነትና ዝምድና ግልጽ አልነበረም። በመጨረሻም የንጉሡ እምቢተኝነት ከተረጋገጠ በኋላ በመጀመሪያው ቀን ንጉሣውያን ቤተሰቦች መስከረም 1ቀን 1966 ዓ ም ተሰብስበው ታሰሩ። በዚሁ ምሽት ማታውኑ ጆናታን ዲንቢልብይ የተባለው እንግሊዛዊ ስለ ወሎ ረሀብ የቀረጸው ፊልም በቴሌቪዥን ሲታይ አመሸ። ለወታደራዊ ክፍሎችም ጉዳዩ በምስጢር ተላለፈ።

ሊሊቱን በሙሉ ጥበቃው ሲጠናቀቅ ከደረ በኋላ ከንጉሡ ግቢ ውጭ የዘብ መደብ በታንክ ተጠናከረ። መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ ም ከጥዋቱ 10ሰዓት ላይ በሻምበል ደበላ ዲንሳ የሚመራ ወታደራዊ ቡድን የቤተ መንግሥቱን በር በርግዶ ዘው ሲል አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ በሚገባ ለብሰውና ተዘጋጅተው ቆሞ ብለው ጠበቁ። ሻምበል ደበላ ዲንሳ አጭር ማስታወሻ በማንበብ ከሥልጣን የወረዱ መሆኑን በማረዳት ወደውጭ እንዲወጡለት ጠየቀ። ንጉሡም ከቤተ መንግሥቱ ከወጡ በኋላ ከተዘጋጀላቸው ቮልስዋገን መኪና ለመግባት ቅሬታ ቢታይባቸውም ከወታደሮች በደረሰባቸው የቃላት ጉሽምታ መሰረት ከመኪናው ውስጥ ገብተው ቁጭ እንዲሉ በመስቀል አደባባይ በኩል ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ሲያመሩ በአጋጣሚ የተመለከታቸው ህዝብ ሲሞህባቸው አንገታቸውን በመስበት ብቅ አድርገው ከሀዲ ይሉ ነበር። አራተኛ ክፍለ ጦር እስር ቤት ከገቡ በኋላ የተፈጥሮ ኃይል ደከመ፤ ጃንሆይነታቸው አከተመ። በዚሁ ዕለት ንጉሡ ከስልጣን ሲወርዱ ከደርግ የተውጣጡ አባሎችና የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ከፖሊስ ሠራዊት በተውጣጣ ልዩ ጓድ ቤተ መንግሥቱ ፍተሻ ሲደረግ በመጀመሪያ $780120. 44 ከንጉሡ መኝታ ቤት በሁለተኛው ቀን ደግሞ $2500 በሦስተኛው ቀን ፍተሻ ከንጉሡ ልዩ ፅሕፈ ቤት $179,193.15 በድምሩ $961813.59 ከመኝታ ቤታቸውና በቢሮአቸው ውስጥ ተገኝቷል።

## ንዑስ ደርጎችና ጊዚያዊ ህዝባዊ መንግሥት።

የደርግ ሥልጣን መያዝ ያስገረመው የጦሩ አባላትን ነበር። አንድ ሸለቃ ጦር መምራት የማይችሉ ስለ ኢኮኖሚ፤ የመንግሥት አሠራር ወዘተ ምንም የማያውቁ ህዝብ ያልመረጣቸው እንዴት መንግሥት ይሆናሉ? ደርግ ውስጥም ያሉ የበታች ሹማምንት ሳይቀሩ በተለያዩ ክፍሎች ተመድበአለሁ ብለው ለጦሩ አባላት ሲናገሩ ስለሚሰሙ መሰዮ ለበሹ በህዝቡ እየቀለዱ ነው፤ በማለት ከመምህራንና ከሌሎችም ክፍል የተውጣጣ ግዝያዊ ህዝባዊ መንግሥት ይቋቋም በማለት ንዑስ ደርጉ ጥያቄ ማቅረብ ጀመረ።

ዋናው ደርግ ከተቋቋመ በኋላ የሥራ ብዛት በየቀኑ እየጨመረ በመሄዱ እራቱ ያሉ

በታያችንም በቁጥጥር ስር ለማድረግ፤ እንዲሁም በዋናው ደርግና በመለዮ ለባሹ መካከል ድልድይ እንዲሆኑ በየበታው ንዑስ ደርግ ከመቋቋሙ አንስቶ ከዋናው ደርግ ጋር አለመግባባት ተፈጠረ። በተለይም ሠራዊቱ ዋናው ደርግ ውስጥ ያሉትን አባላት የመረጥናቸው ባለሥልጣኖችን ለማሰር እንጂ ሀገር ለመምራት ስላልሆነ ወደየክፍላቸው እንዲመለሱ በማለት ጠየቀ። አስተባባሪ ኮሚቴው ግን ምስጢር ስለወቀን አንመለስም አለ። ይህ በዚህ እንዳለ ንዑስ ደርጎች ዋናውን ኮሚቴ (ደርግ) ሳያማክሩ በራሳቸው በሚወስዱት እርምጃ በሁለቱ መካከል ግጭት ተፈጠረ። መምህራን ተማሪዎች ወዘተ በአዲስ አበባ ከተማና በሌሎችም ግዚያዊ ህዝባዊ መንግሥት ይቋቋም በማለት ሠላማዊ ሰልፍ ጀመሩ። ይህንን ጥያቄ በመደገፍ በአየር ኃይል፤ በክቡር ዘበኛ፤ በመሐንዲስ፤ በአርሚ አቪየሽን እና በብዙ በተለያዩ ክፍሎች ይህ ጥያቄ ተደጋግሞ ቀረበ። በተለይም አርሚአቪየሽን አዛዦቻቸው በመታሰሩ ከመሐንዲስም አንዱ አባል የደረሰበት ስለአልታወቀ ወደ ደርግ የላኳቸውን አባላት እንዲመለሱ ተጠየቀ። ይህም የለጠውን ደርግ ውስጥ ያሉትን አባላት አስቆጣ። ይህ ሁኔታ በድምፅ ብልጫ እንዲወሰን ከየክፍለ ሀገሩ ያሉት የንዑስ ደርግ ሊቀመንበሮች ለስብሰባ አዲስ አበባ ተጠሩ። የመጡትም አባላት ከጦራቸው ይዘው የመጡት ጥያቄ ተመሳሳይ በመሆኑ ደርግን ስለአሳሰበው ልዑካኑ በአረፉባቸው ሆቴሎች እየሄዱ ሀሳባቸውን እንዲቀይሩ ጥረት አደረጉ። በመጨረሻም የአየር ኃይልና የክቡር ዘበኛ ንዑስ ደርግ በስተቀር ሁሉም ከደርግ ጃርባ ተሰለፉ። የመሐንዲስና የአርሚ አቪየሽን ወኪሎች ደርግ ወደጦር ሰፈራቸው እንዲመለሱ በጠየቀው መሰረት ተመለሱ።

በአራት ኪሎ አካባቢ በየቀኑ በመካሄድ ላይ ሳለው ሰላማዊ ሠልፍ ብተና የንጉሡ የአንጋች ሻንበል ጦር ታዞ ከመኪና ሳይወርድ በተማሪዎች ላይ አለስተኩሰም በማለት ሳይሳተፍ ቀረ። በዚህ ምክንያት በደርግና በክቡር ዘበኛ የነበረው ቅራኔ እየሰፋ ሄደ በአዲስ አበባ ዙሪያ በዛ ያለ ጦር የነበረው ክቡር ዘበኛ ስለነበረ ሁኔታው ደርግን በጣም ስለአሳሰበው ከጅጅጋ ሜከናይዝድ ብርጌድና ተወጣሪ ታንኮች ከነገሌ በረና ፬ኛ የመድፈኛ ሻለቃን በአስቸኳይ አስመጣ። ሁኔታው እየተባባሰ ሲሄድ ሌላ የ፶፫ቱ ዓመተ ምህረት ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈጸም ይታይ ጀመር። ሆኖም በአዲስ አበባ አካባቢ አንዱ የጦር ክፍል ከደርግ ጋር ነኝ ሲል ሌላው ደግሞ የጊዚያዊ ህዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ከሚደግፉት ጋር ነኝ በማለት ህዝብ ከተሰበሰበበት አካባቢ ወረቀት መበተን ጀመሩ።

የክቡር ዘበኛም የንዑስ ደርግ ሊቀመንበር የነበረው ሻምበል ደምሴ ሽፈራው በነ ምክንያት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ውጊያ እንዳይጀመር በማለት በቀጥታ ሄዶ እጁን ለደርግ ሰጠ። የመሐንዲስ ጦር አባላት ለምሣ በሄዱበት ጊዜ የሜከናይዝድ ሻምበል ጦር ግቢውን ከበው ተኩስ በመክፈት በህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ። የዚህን እለት አርሚ አቪየሽን ተከቦ የክፍሉ አባላት በቀጥታ ወደ ሆለታ ተላኩ። ከነዚህ ክፍሎች በመጀመሪያ ወደ ደርግ የተላኩት ወኪሎች በቤተ መንግሥት በተቋቋመው እስር ቤት ገቡ። ደርጉ ለመጀመሪያ





ጊዜ መለዮ ለባሹ ላይ ያለምንም ወንጀል ደም አፈሰሰ። የታሰሩት የመሐንዲስና የአርሚ አቪየሽን የደርግ አባላት የክቡር ዘበኛው የንዑስ ደርግ ሊቀመንበር ጭምር ከስልሳዎቹ ባለስልጣኖች መካከል አብረው ተረሽኑ። ወንጀላቸው ግን ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ማለታቸው ነበር።

ይህን በመሳሰለው ምክንያት ከመለዮ ለባሾች ውስጥ የጠረጠሯቸውን መኮንኖችና ወታደሮች ልዩ ልዩ ምክንያት በመደርደር በለሰጣን ባልገባ ብለው ከገደሏቸው የቀድሞ የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣኖች ጋር በመደረብ ከገደሏቸው አባሎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበቸዋል።

1 ኮሎኔል የማለምዘውድ ተሰማ የአየር ወለድ አዛዥ
2 ኮሎኔል ይገዙ ይመኑ የአርሚ አቪየሽን አዛዥ
3 ሻምበል ደምሴ ሽፈራው ክቡር ዘበኛ ንዑስ ደርግ
4 ሻምበል በላይ ፀጋዬ ምድብት
5 ሻምበል ወልደዮሐንስ ዘርጋው
6 መቶ አለቃ ተክሌ ሀይሌ
7 መቶ አለቃ ተበጀ ተክሌ
8 ፶ አለቃ በቀለ ወልደ ጊዮርጊስ
9 ሌ/ ጄ አማን አንዶም የደርጉ ሊቀመንበር (ርዕብሔር)
10 ኤርክራፍት ማን ዮሐንስ ፍትዊ

የተወነጀሉበት ምክንያት ቢኖር ሀሳቦቻችንን አይደግፉም፤ ወታደሩን ያነሳሳሉ፤ የህዝባዊ መንግሥትን መቋቋም በጥብቅ ይደግፋሉ የሚል ነው። ከነዚህ ውስጥ የደርግ አባላት የነበሩትን የ፶ አለቃ በቀለ ወልደጊዮርጊስና መቶ አለቃ ተበጀ ተክሌ ከደርጉ ኮሚቴ አባላት ውስጥ ተወስደው ነው በዚሁ እለት የተገደሉት።

## ክፍል ፪
## ደርግና ጀኔራል አማን አንዶም

የንጉሡ መውረድ ሥነሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ የጸጥታው ኮሚቴ ደርግ በሚል ስም እራሱን ሰይሞ ከ፬ኛው ክፍለ ጦር ወደ ላይኛው ቤተ መንግሥት ቢሮውንና እስር ቤቱን አዛወረ። መለዮ ለባሹ ለውጡ በተጀመረ ማግስት የጎደለውን አስተካክሉ ወደ ጦር ሠፈር እመለሳለሁ ያለውን ቃል ኪዳን ጥሶ በአፄ መንበር ላይ ተኮፈሰ። ጀኔራል አማንም ውሉ የማያድር ስልጣን ተቀብለው ሕዝቡንና ወታደሩን ለማስተባበር ጥረት ማድረጋቸውን ቀጠሉ፤ ነገር ግን በጦር ዘንድ ተወዳጅ ታዋቂ የነበሩት እኚህ ጀኔራል በወታደሩ ወይም ምልእተ ሕዝብ ዘንድ ተደጋፊነታቸው ገና በሚያጠራጥር ሁኔታ ላይ እያለ ከመቅጽበት በኤርትራ ችግር ውስጥ ዘው ብለው ገቡ። የኤርትራ ችግር ለብዙ ዘመናት ያወከና የነበረውም መንግሥት መፍትሄ ያልሰጠው ችግር ነበር። ጀኔራሉ ግን በድንገት የወሰዱት እርምጃ በደርግም ሆነ በኤርትራ ቂያሞች ዘንድ ድጋፍ አላገኘም። ምንም እንኳን ጥረታቸው ከልብ የመነጨ የአገርና የወገን ስሜት ላይ ያተኮረ ነው ቢባልም ደርግ የጀኔራሉን ጉብኝት የተመለከተው ስለ ኤርትራ ጉዳይ ስጋት አድርበት ሳይሆን መከራቸው ተባክቶ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ድጋፍ ካገኙ ጦሩም ስለሚደግፋቸው ለወደፊቱ ከሥልጣን ሊወርዱን አይችሉም ከሚል የሥልጣን ስጋት አንፃር ነበር። የዚህን አፀፋ ለመመለስ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም በጉፋ የጦር ሠፈር ጦሩ እንዲሰበሰብ አድርጉ እራሱንም በመሪ ደረጃ አስቀምጦ የመጀመሪያ ንግግሩን በማድረግ ለጦሩና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን አስተዋወቀ። በጦሩም ጉብኝት ወቅት ኮሎኔል ከፈለኝ ይብዛ የተባሉት የክብር ሰላምታ በመስጠት ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ መኮንኖች ዘንድ ውርደትን አተረፈ። ጉብኝቱም ለመጀመሪያ ጊዜ በራዲዮ ተገለፀ።

ጀኔራል አማንም ያልጠበቁት ውርደት ስለደረሰባቸው ሥራቸውን አቁመው ወደ ቤታቸው ተከተቱ። ሌ/ ኮ መንግሥቱና አበሮቹ ጀኔራሉን በመረጃ እየተከታተሉ መገናኛቸውን ሁሉ በማጥበብ በርጋታ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ይለምኑ ጀመር። ጀኔራል አማን ግን የደርጉን ልመና አልተቀበሉም። ደርግም የጀኔራሉን ሁኔታ ከገመገመ በኋላ አምስት ነጥብ የያዘ ወንጀል በመጥቀስ በጠቅላላው ጦሩን እየሰበሰበ ማስረዳት ጀመረ። በዚህ ብቻ አላበቃም በተገኘው መገናኛ ሁሉ ጦሩ ባለበት ክፍል ተቀባይነት እንዲያገኙ ወነጀላቸው።

ጀኔራሉ ህዳር 18 ቀን 1967 ዓ ም ከቀረበባቸው የክስ ነጥቦች ውስጥ

1 የህዝቡንና የመለዮ ለባሹን ድምጽ በመከተል ለኢትዮጵያ ትቅደም በሚል ከመሰረተው አይደሎጂ ተፃራሪ የሆኑ ጉዳዮችን በመፈፀማቸው።

2 የህዝቡንና የወታደሩን ንቅናቄ ለማክሸፍና የግል ስልጣናቸውን ለመመስረት፤





የህዝብን ቃልኪዳን አፍርሰው በህዝቡና በወታደሩ ንቅናቄ ላይ ማሴራቸው።

3 በንቅናቄው ላይ ያቀዱት ሴራ እንዳልተሳካላቸው ሲያውቁ ደርጉንና ወታደሩን ለማለያየት በመሞከራቸው።

4 በዲሞክራሲያዊ መንፈስ የተቋቋመውን ደርግ ላይ ተጽዕኖ በማሳደርና በከፍተኛ የድምፅ ብልጫ የተላለፉትን ብሔራዊ ውሳኔዎች በስራ ላይ እንዲውሉ ባለማድረጋቸው።

5 ደርግ ለቆመለት ህዝብ ደጋግሞ እንደገለፀው የሀገሪቱን ችግር ካስተካከለ በኋላ በህዝብ የተመረጠ ህዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ወደ ጦር ሰፈሩ ለመመለስ እንጂ ጉልበቱ ባልተበሰ አዲስ አምባገነን መዳፍ ውስጥ ለመጨመር ባለመሆኑ ጀኔራሉ ተንኮላቸውን አቁመው በስራቸው ላይ እንዲቀጥሉ ብዙ ጊዜ ተመክረው ለሰምንት ቀናት ከሊቀመንበርነት ስራቸው ስለቀሩ ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ ም ከሥልጣን ወርደዋል አሉ። ከዚህም በስተቀር እየተዘዋወሩ ለጦሩ ሲያስረዱ ጀኔራሉ የመብራት ዕዳ አልከፈሉም እያሉ ጦሩን ለማሳመን ሞክረዋል።

ጦሩ ግን ፈጥኖ የወሰደው ርምጃ የለም። ሆኖም በጀኔራሉ ምክንያት የሚፈጠረው ሁኔታ አስጊነቱን በመገምገም አነሻለቃ መንግሥቱ የደርግ አባሎችን እየነጣጠሉ በማስረዳትና በመጨረሻም በስብሰባ በማየት በጀኔራል አማን ላይ እርምጃ እንዲወሰድ አጽድቀው ግዳጁን እንዲያስፈጽም ሌ/ ኮ ዳንኤል አስፋው ታዘዘ። ዳንኤልም በጥበቃ ከሚገኘው ጦር በማንሳት በታንክ ታጅቦ አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ በሚገኘው የጀኔራሉ መኖሪያ ቤት በመሄድ ዙሪያውን ከበ ተኩስ ከከፈተባቸው በኋላ ከጀኔራሉ በተሰጠው የተኩስ መልስ ዳንኤልና ሦስት ወታደሮች በቀላሉ ሲቆስሉ ጀኔራሉ ተገደሉ።

የጀኔራሉ መገደል ድንጋጤ በፈጠረው ምክንያት በግቢው ውስጥ ታስረው የሚገኙት የቀድሞ ባለሥልጣኖች ወደ አቃቂ ወህኒ ቤት በመውሰድ በሻለቃ ጌታቸው ሽበሽ አማካኝነት ተረሸነው በግቢው ውስጥ በግሬደር በተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ ጨምረው አፈር ደልድለው እንዳይታወቅ ሽንኩርት ተከሉ።

ምንም እንኳን ለይስሙላ የደርግ አባሎች ተሰብስበው በባለሥልጣኖች መገደል ወሰኑ ይባል እንጂ እንዲገደሉ የተወሰነባቸው የባለሥልጣኖች የስም ዝርዝር ለሻለቃ ጌታቸው ሽበሽና ለአንድ ሌላ መኮንን ከጠረጴዛ መሳቢያ ውስጥ አውጥቶ ሻለቃ መንግሥቱ እንደሰጣቸው ስለታወቀ የባለ ሥልጣኖች አገዳደል በድንገት የተወሰደ እርምጃ ነው ማለት ያስቸግራል። ሆኖም ሻለቃ ጌታቸው ሽበሽና ሌላው መኮንን ሆነው ባለሥልጣኖች ከታሰሩበት እስር ቤት ሄደው ስም እየጠሩ ወደ መኪና በሚጭኗቸው ጊዜ ደጃዝማች ሀረጎት አባይ ሻለቃ ጌታቸው ሽበሽ በሚጠሩበት ዝርዝር ውስጥ ሲኖሩበት በሌላው ግን አልነበሩበትም፤ ስለዚህም ያልታዘዙትን አልገልም በማለት ሌላው መኮንን ጭቅጭቅ ስለፈጠረ ጊዜው አስቸኳይ ስለሆነ ደጃዝማች ሀረጎት ወደ እስር ቤት እንዲመለሱ ሆኖ ሌሎችን ወስደው ገድለዋል። ደጃዝማች ሀረጎት አባይ ግን ከአመት በላይ ከታሰሩ በኋላ ወዴት እንደደረሱ ካልታወቀ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር የምስጢር ውሳኔ እንደተሰጣቸው ይታመናል።

የተገደሉት ፷ የቀድሞ ባለሥልጣኖች ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ፩ | አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ | ጠቅላይ ሚኒስትር |
| ፪ | ልዑል እሥራት ካሣ | የዘውድ ም/ ቤት ፕሬዝዳንት |
| ፫ | ልጅ እንዳልካቸው መኮንን | አዲሱ ጠ/ ሚኒስትር |
| ፬ | ራስ መስፍን ስለሺ | የሸዋ እንደራሴ |
| ፭ | ሌ/ ኮ ታምራት ይገዙ | የጎንደር እንደራሴ |
| ፮ | አቶ አካለወርቅ ሀብተወልድ | የፍርድ ሚኒስትር |
| ፯ | ዶ/ ር ተስፋዬ ገ/ እግዚእ | የማስታወቂያ ሚኒስትር |
| ፰ | አቶ ሙላቱ ደበበ | የሕዝብ ልማት ሚኒስትር |
| ፱ | አቶ አበበ ረታ | የጤና ጥበቃ ሚኒስትር |
| ፲ | ደጃ. ሰለሞን አብርሃ | የወሎ እንደራሴ የነበሩ |
| ፲፩ | ደጃ. ለገሠ በዙ | አዲሱ የወሎ እንደራሴ |
| ፲፪ | ደጃ. ሳህሉ ድፋዬ | የአርሲ እንደራሴ |
| ፲፫ | ደጃ. ወርቅነህ ወ/ አማኑኤል | የግቢ ሚኒስትር |
| ፲፬ | ደጃ. ክፍሌ እርገቱ | የሀገር ግዛት ሚኒስትር |
| ፲፭ | ደጃ. ወርቁ እንቁሥላሴ | የኢሉባቦር እንደራሴ |
| ፲፮ | ደጃ. አእምሮ ሥላሴ አበበ | የጎሙ ጎፋ እንደራሴ |
| ፲፯ | ደጃ. ከበደ አሊ ወሌ | የወሎ ም/ ቤት እንደራሴ |
| ፲፰ | ኮሎኔል ሰለሞን ከድር | የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ |
| ፲፱ | ሊቀ መኳስ አበጀ ደባልቅ | የፍርድ ሰብሳቢ |
| ፳ | አቶ ነቢየልዑል ክፍሌ | ጠቢ ን ጋዜ |
| ፳፩ | ቀኛዝማች ይልማ አቦዬ | የንጉሥ ግምጃ ቤት |
| ፳፪ | አቶ ተገኝ የተሻወርቅ | የማስታወቂያ ሚኒስትር |
| ፳፫ | አቶ ሰለሞን ገብረማርያም | |
| ፳፬ | አቶ ኃይሉ ተክሉ | |
| ፳፭ | ልጅ ኃይሉ ደስታ | |
| ፳፮ | ብላታ አድማሱ ረታ | የንጉሡ የውስጥ አገልጋይ |
| ፳፯ | ፊት/ ደምሴ አለምረው | ጅማ ውስጥ አውራጃ ገዥ |
| ፳፰ | ፊት/ አምዴ አበራ | |
| ፳፱ | ፊት/ ታደሰ እንቁ ሥላሴ | ጅማ ውስጥ አውራጃ ገዥ |
| ፴ | ጄ/ ኤ/ አቢይ አበበ | አዲሱ የመከላከያ ሚኒስትር |
| ፴፩ | ሌ/ ጄ ከበደ ገብሬ | የቀድሞው የመከላከያ ሚኒስትር |





| | | |
|---|---|---|
| ፴፪ | ሌ/ ጄ ድረሴ ዱባለ | የምድር ጦር አዛዥ |
| ፴፫ | ሌ/ ጄ አበበ ገመዳ | የቀድሞው ክብር ዘበኛ አዛዥ |
| ፴፬ | ሌ/ ጄ ይልማ ሽበሺ | የፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ |
| ፴፭ | ሌ/ ጄ ኃይሌ ባይከዳኝ | ቺፍ ኦፍ ስታፍ (አዲሱ) |
| ፴፮ | ሌ/ ጄ አሰፋ አያና | ቺፍ ኦፍ ስታፍ (የቀድሞ) |
| ፴፯ | ሌ/ ጄ በለጠ አበበ | የብሔራዊ ጦር አዛዥ |
| ፴፰ | ሌ/ ጄ ኢሣያስ ገ/ ሥላሴ | የሲዳሞ እንደራሴ |
| ፴፱ | ሌ/ ጄ አሰፋ ደምሴ | የአልፍኝ አስከልካይ |
| ፵ | ሌ/ ጄ ደበበ ሀ/ ማርያም | የኤርትራ እንደራሴ |
| ፵፩ | ሜ/ ጄ ሥዩም ገድለ ጊዮርጊስ | |
| ፵፪ | ሜ/ ጄ ጋሻው ከበደ | የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ |
| ፵፫ | ሜ/ ጄ ታፈሰ ለማ | የክቡር ዘበኛ አዛዥ (አዲሱ) |
| ፵፬ | ሪ/ አ እስክንድር ደስታ | የባህር ኃይል አዛዥ |
| ፵፭ | ብ/ ጄ ሙሉጌታ ወ/ ዮሐንስ | የፈጥኖ ደራሽ አዛዥ |
| ፵፮ | ብ/ ጄ ወንድሙ አበበ | የአዲስ አበባ ፖሊስ አዛዥ |
| ፵፯ | ብ/ ጄ ግርማ ዮሐንስ | የቀድሞው የወሎ ፖሊስ አዛዥ |
| ፵፰ | ኮ/ ዓለም ዘውድ ተሰማ | የአየር ወለድ አዛዥ |
| ፵፱ | ኮ/ ጣሰው ሞጆ | የንጉሡ የአጀብ ክፍል |
| ፶ | ኮ/ ይገዙ ይመኑ | የአርሚ አቪየሽን አዛዥ |
| ፶፩ | ሻለ/ ብርሃኑ ሜጫ | ከፖሊስ ሠራዊት ልዩ ቅርንጫፍ |
| ፶፪ | ሻም/ ደምሴ ሽፈራው | ክብር ዘበኛ ንዑስ ደርግ |
| ፶፫ | ሻም/ በላይ ፀጋዬ | ከአርሚ አቪየሽን |
| ፶፬ | ሻም/ ወልደዮሐንስ ዘርጋው | |
| ፶፭ | ፲/ አ ተክሌ ኃይሌ | |
| ፶፮ | በቀለ ወልደጊዮርጊስ | |
| ፶፯ | ሻም/ ሞላ ዋኘው | |
| ፶፰ | ሌ/ ጄ አማን አንዶም | |
| ፶፱ | ፲/ አ ተስፋዬ ተክሌ | |
| ፷ | ኤርክራፍት ማን ዮሐንስ ፍትዊ ናቸው። | |



ሌ/ጄ አማን ፡ አንዶም

ቅዳሜ መስከረም ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓመተ ምሕረት ።

## ክፍል ፯
## ንጉሡ በእሥር ቤት ዘመናቸውና የዕድሜያቸው ፍጻሜ

ንጉሡ ነገሥቱ በእሥር ቤት ዘመናቸው የስቃይ ጊዜ አሳልፈዋል። በሦስት ዙር ጠባቂዎች የተጠናከረው እስር ቤት ንጉሡን ግራና ቀኝ ለማየት ወይም ለመዘዋወር የማያስችላቸው ሁኔታ ነበር።

አንዱ የጥበቃ ቡድን ከመኝታ ቤታቸው ገብቶ ከአልጋቸው ሥር የሚተኛ ሲሆን ከቤት ውስጥ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል።

ሁለተኛው ቡድን ከቤት ውጭ ዙሪያውን ከቦ የሚጠብቅ ሲሆን ከቤት ውስጥ የሚገኘው የጥበቃ ቡድን ጋር በየሰዓቱ ሪፖርት ይለዋወጣል።

ሦስተኛው ቡድን ከእሳቸው እስር ቤትና የባለሥልጣኖቹንም እስር ቤት ጠቅላይ ጥበቃውን አጠናክሮ የሚጠብቅ ነው።

ሌላው ችግራቸው ደግሞ ሻለቃ መንግሥቱ በየጊዜው እየሄደ ደብቀዋል የተባለውን ገንዘብ እንዲያመጡና ማንኛውንም ነገር እንዲያስረዱ የሚያቀርብላቸው ያልተቋረጠ ጥያቄ እእምሮአቸውን ነክቶት ነበር። የነበራቸውን የቤት ንብረትና የገጠር መሬት ቀደም ብለው ለልጆቻቸው ማከፋፈላቸውን ቢያስረዱም የሚያምናቸው ሰው ስላጡ የበለጠ የራስ መናወጥ የጤናም መታወክ ደርሶባቸው ነበር ይባላል። ከሁሉም የሚያበሳጫቸው ግን መንግሥቱ ጉብኝቱን ከጨረሰ በኋላ ከሀዲ የሚላቸው ነበር።

በመጨረሻ የሚናገሩትን ሁሉ የማይገነዘቡና እእምሮአቸው መሳት ስለጀመረ ልጃቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ አብረዋቸው እንዲቀመጡ ተደረገ። ሁለቱም አብረው በነበሩበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር። በተለይ ልዕልቲቱ ከገቡ በኋላ ሌላ ተንኮል ይሰሩ ይሆናል በሚል ፍራቻ በቤታቸው ውስጥና ውጭ በቴፕ ሪከርደር ተተብትቦ በየደቂቃው የሚናገሩትንና የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ሁሉ እነመንግሥቱ ይቆጣጠሩ ነበር።

የንገሡ በሕይወት መኖር ደርግን ተቃውመው በረሀ ለገቡ ባለሥልጣኖችና በየጉጡ እሽምቀው ለሚጠብቁ ፊውዳሉች ሞራል የሰጠ በመሆኑ ከዚህም በላይ በየቦታው ጥይት እየተኮሱ ሕዝቡን በማሰመጽ ተግባር ላይ ስለተሰማሩ በንጉሡ ሕይወት ላይ ርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው ብለው የደርግ አባሎች በሰመነበት አብረዋቸው የተቀመጡትን ልጃቸውን ልዕልት ተናኘ ወርቅን በመነጠል ወደቀድሞው እስር ቤታቸው መለሷቸው። ከዚህ በኋላ የንጉሡ ሕይወት በሻለቃ መንግሥቱ ብቻ የሚወሰን በመሆኑ ምንም እንኳን በዓይን የታየ ማረጋገጫ ባይኖርም ሌ/ ኮ ዳንኤል አስፋውን አስከትሎ ሕይወታቸውን እንዳጠፋት ይነገራል።

ዘወትር ከዘብ መደብ ይተሰለፍ የነበረው ዜና እንደሚያስረዳው መንግሥቱና ዳንኤል ወደንገሡ ቤት ሲገቡ ዘቦቹ በሙሉ ይወጡ ነበር። በዚያች ሌሊት ዘቦቹ ወደውጭ





እንዲወጡ ተደርጓል ነው የተባለ። ይህ የተፈፀመበት ሰዓት ከሌሊቱ እጋማሽ በመሆኑ ለዘቦቹ ንጉሡ መሞታቸውን የሚያረጋግጡበት ሁኔታ አልነበረም። ቀጥሎም የንጉሡ ሐኪም ዶክተር አስራት አልተገኙም የሚለው ዜና በዘቦቹ መደብ ከተነዘ በኋላ በሀመም መሞታቸው ይወራ ጀመር። ዶክተር አስራት ግን በስራ ምክንያት አሥመራ መሄዳቸውን እነ መንግሥቱ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። ግን የግል ሐኪማቸው ተፈልጉ ስለጠፉ ንጉሡ ሞቱ በማለት ማስታወቂያ በተቀላቀለበት የሬዲዮ ፕሮግራም ተገለጸ። ሌላው አስገራሚ ሁኔታ ደግሞ ከቤተ መንግሥቱ እጠገብ ከምትገኘው ከኪዳነምሕረት ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ንጉሡ ይቀበራ ሉ ተብሎ ሳጥን እጋድመው ጉድጓድ ሲቆፍሩ ከቆዩ በኋላ ባዶ ሳጥን አስቀምጠው ሬሳቸውን ግን በድናቸውን የሚያቃጥል መርዝ ነስንሰው ወደ ትልቁ ወሀኒ ቤት ወስደው ምልክት በሌለበት ስፍራ እንደቀበሯቸው ብዙ የሚጠቀሙ ማስረጃዎች ነበሩ። ንጉሡ በእንዴት አይነት ዘዴ እንደተገደሉ በመንግሥቱና በዳንኤል ብቻ ታፍኖ የቀረ ሲሆን እጠገባቸው የነበሩ ዘበኞች እንኳን ለማወቅ ሳይችሉ ቀርተዋል።

## ክፍል ፯
## የደርጉ የውስጥ ችግር

ከ1967 ዓ ም ጀምሮ በደርጉ ውስጥ ከፍተኛ የሥልጣን ትግል እየሆነ በመጣበት ወቅት ቀንደኛ የሆኑ የደርግ አባሎች በቡድን ተከፋፍለው አንዱ አንዱን ለመጣልና ሌላው ሌላውን የመናቅ ሥር የሰደደ የውስጥ ለውጥ ትግል በከኼዱበት ጊዜ ተጋልጠውና በግልጽ ታውቀው በከፍተኛ ትንቅንቅ ላይ ከነበሩት መካከል፤

፩ኛ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም

፪ኛ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ

፫ኛ ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል

፬ኛ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ

፭ኛ መቶ አለቃ በውቀቱ ካሣና

ሌሎችም ነበሩ።

ራሳቸውን በማጠናከር በሁለት ቡድን መካከል የተስነጠቁት የደርግ መንጋ ከወደት እንደሚጠጋ ግራ ሲጋባ በደርጉም ሆነ ከዉጭ ያሉትን መኰንኖች በማሰባሰብና የራሱ ጭፍራ ለማድረግ መንግሥቱ ኃማርያም ይጫወት የነበረው ሚና ቀላል አልነበረም። ከዚህም ሌላ ሌ/ ኰ ዳንኤል አስፋው የጥበቃው ኃላፊ ከመንግሥቱ ጋር በመመሳጠር ወደፊት ለሚወስዱት እርምጃ በተጠንቀቅ ላይ እንደነበረ ግልጽ ነው።

ሻንበል ሞገስና ሻንበል ዓለማየሁ ደግሞ ከቢሮክራሲውና ከምሁሩ ጋር በማበር (በመተባበር) በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሥራ ዘርፍ ሁሉ የራሳቸው የሆኑትን ሰዎች በሥልጣን ላይ በመሰግሰግ መንግሥታዊ መዋቅሩን ለመቆጣጠር ችለዋል። ከዚህም በስተቀር በደርጉ ውስጥ በማሰደም ለራሳቸው ድጋፍ እንዲያገኙ ጥረዋል። ነገር ግን በከፍተኛ ስህተት ያለፉት ነገር ቢኖር የመለዮ ለባሹን ድጋፍ ለማግኘትና በተለይም ቁልፍ የሆኑትን ከደርጉ ውጭ ያሉ መኰንኖችን በሰልፋቸው ውስጥ ያለማስገባታቸው ነው።

ትግሉና ችግሩ በነዚህ መኰንኖች ጉልቶ ይታይ እንጂ ሁሉም አንዳቸው በየደጃፉና በየበረንዳው የማይደልት አልነበረም። ሁኔታው በዚህ መልክ ሲጓዝ ከሰነበተ በኋላ በደርጉ ውስጥ በተደረገው ስብሰባ ላይ የሌ/ ኰ መንግሥቱ ሥልጣን ማከበቱ ተነስቶ ክርክር ከተደረገ በኋላ የዋና ጸሐፊነቱን ስልጣን በምርጫ ሻንበል ዓለማየሁ ኀይሌ ከአስተዳደርና እቃዎ ሊቀመንበርነቱ ጋር ደርበ ያዘ። መንግሥቱ በዚህ ዕለት ምላሱን ሸብበ ክብሩን ጠብቆ ከመዋሉ በስተቀር ምንም ሊያደርግ ባለመቻሉ በምክትል ሊቀመንበርነት ብቻ ተወሰነ።

በዚህ ዕለት ይህ ብቻ አልነበረም አስደናቂ የነበረው። የሌ/ ኰ መንግሥቱ ተባባሪ የሆነው ሌ/ ኰ ተካ ቱሉ የሕዝብ ደህንነት ሊቀመንበር ከሥልጣኑ እንዲወርድና ወደጡረታ





እንዲገባ ሲወሰን የነሻንበል ዓለማየሁ ቡድን ነው የተባለው ሌ/ ኰ ጎሩይ ደግሞ የተካ ቱሉ ምክትል ስለነበረ የሕዝብ ደኅንነቱ ዋና ሆኖ ተመረጠ። የሌ/ ኰ መንግሥቱ የሌ/ ኰ ተካ ቱሉ ወደጡረታ መገለሉ ተገቢ ስለአልሆነ ወደሶሺየት ህብረት ተልኮ የፖለቲካ ጥናት እንዲወስድ የነዓለማየሁን መድረክ ተማጠነ። በገብጌውም ወደሶቭየት ይላክ የሚለው ተደግፎ ስለተፈቀደለት ጓዙን ጠቅልሎ ከኢትዮጵያ ወጣ።

በዚህ ስብሰብ ላይ የታየው ለውጥ ለነመንግሥቱ ውርደት ለነዓለማየሁ ደግሞ ሞራል የሰጠ በመሆኑ በሁለቱም ወገኖች ትግሉ ገና እንደሚቀጥል ይታይ ነበር። ይህ በሆነ ማግስት ከጓደኛየ ጋር በሻንበል ዓለማየሁ ቤት በኩል ስናልፍ ሥራ ለመሄድ ከበሩ ቆሞ አገኘነው። እኛም እንኳን ደስ ያለአለህ አልነውና ቀለድንበት። እሱም ፈገግ አለና ምንደስታ አለ ገና ትግሉ ይቀጥላል አለን። አሁን በሕይወት ያለው ጓደኛዬ መጠንቀቅ ነው ጠመንጃ ይዘው በግቢያችሁ ውስጥ እያሉ እንዴት ይታመናሉ አለው። በመሀከላችን ሳቅ በዝቶ ነበር። ግን የዓለማየሁ ትዕቢት ደስ አላለንም። ቀጥሎም ዓለማየሁ በዚህ በሪያ ላይ እርምጃ መውሰድ አላቀተንም። እጁን የፈጥኝ አስረን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍርድ ለማቅረብ እንፈልጋለን ብሎ መኪናውን አስነስቶ ወደቢሮው ተጓዘ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ እነ ሻንበል ዓለማየሁና ሻንበል ሞገስ የኢሕአፖ ጥገኞች ሆነዋል እየተባለ በከፈው መወራት ጀመረ። ሆን ብለው የሚያስወሩት ግን እነ መንግሥቱ በነ ዓለማየሁ ላይ ምሰጭ ለመሰብ የሚያስችላቸውን ጉዳና እየጠረጉ ስለነበር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ መንግስቱ ከመኢሶን ጋር ገጥም ዳንኪራ እየተመታለት ነበር። ስለዚህ ምሁሩን በመከፋፈል መንግሥቱ የሚጫወተው ሚና አለ እየተባለ ይወራ ጀመር። ይህንን የሚያስወሩት ደግሞ እነ ዓለማየሁ አፀፋውን ለመመለስ ይመስላል።

ውጣ ውረዱ በከፍተኛ ደረጃ ቀጥሎ የሚጥለው እስከተረጋገጠ ድረስ ውጤቱን የሚናፍቁ ብዙ ተከታታዮች ነበሩ።በየቀኑ የጊዜው ሁኔታ የሚለዋወጥ ስለነበረ የሚሰጡት ውሳኔዎች ሁሉ ህዝቡንና በተለይም በለውጡ ላይ አደገኛ አዝማሚያ ሊከተል ስለሚችል ሁሉም በቅርብ የሚከታተለው ሁኔታ ነበር። እንደተባለውም አልቀረም ትግሉ እየከረረ መጣ።


በሌ/ ኰ መንግሥቱን የተደረገው ሴራ በደርጉ የውስጥ ቅራኔ ሳቢያ ብቻ የታሰበ አይደለም። በሜኢሶንና በኢህአፖ መካከል በነበረው የሥልጣን ትግል ጥያቄ ብዙ ሽኩቻ ነበረው። ቀንደኛ የሆኑትን የደርግ አባሎች ለመነጠል የሚያደርገው ሙከራ ሁሉ ቀላል አልነበረም። የሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌና የሻምበል ሞገስ በደርጉ ዙሪያ የደርግ አባል ካልሆኑ መኰንኖች ጋር በመመሳጠር በሰውር ያውጠነጥኑት የነበረው ሴራ በቀላሉ አይታይም። ይኸውም መኰንኖችን በማስተባበርና ከዚያም ጦሩን በማሰደም በነ ሌ/ ኰ መንግሥቱ ላይ ርምጃ ለመውሰድና የሚመኙትን ሥልጣን ለመንጠቅ ከሳቸው ዕቅድ በመነሳት ይመስላል። በተጨማሪም በኤርትራው ድርጅት ኢ ኤል ኤፍ እና ኢህአፖ መንግሥቱን ለመግደል

በተደረገው ሙከራ ውስጥ ለመዋራቸው በግድያው ላይ የተሰማሩ ቱ ሰዎች አስረድተዋል።

ስለዚህ ጉዳይ በጥሩ ለማስረዳት እሞክራለሁ። መስከረም ፲፭ ቀን ፷፱ ዓ ም ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ላይ መንግሥቱ ከቤተ መንግሥቱ ተነስቶ አራተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ቢቱ በመጓዝ ላይ ነበር። ደፈጣው በመስቀል አደባባይ ጀምሮ ወደአራተኛ ክፍለ ጦር ወደግራ መታጠፊያ ከብ የትራፊክ አራት ማዕዘን መንገድ ላይ ተዘጋጅቷል። ነጮብ በታዎች በግዩን ሆቴል አውቶብስ ማቆሚያ አንደኛው ሲሆን በቀኝ በኩል ደግሞ ሼል ቤንዚን ማደያ የልጅ እንዳልካቸው ህንጻ የሚታይበት ከብ የትራፊክ ማከፋፊያ ናቸው። የማሰሰቻ ፈንጅም ከቦሌ መገንጠያ መንገድና አሥመራ መንገድ ድልድይ አጠገብ ፈንድቶ ነበር። ለማንኛውም ከዚህ ጋር የተያያዘውን ንድፍን ይመልከቱ።







ሌ/ ኰ መንግሥቱ ከወጠበት ጊዜ ጀምሮ በታኖስ መኪና ከፊትለፊቱ በርቀት የሚከተሉት ነበረ ከታኖሱ በፊት ደግሞ በመግደያ በታ ምልክት የምትሰጥ ቀይ ቮልስዋገን መኪና ትበራለች። መንግሥቱ ከበታው እንደደረሰ በምልክቱ መሠረት ግራና ቀኝ ያደፈጡት አጃቢያቸን ነጥለው ሲመቱ በታኑሱ ውስጥ ያሉት ደግሞ በመንግሥቱ ላይ ተኩስ እንዲከፍቱ ነበር። ይህን ሁሉ እቅድ ምልክት ሰጪዋ ቀይ ቮልስዋገን በማሰበቷ ቡድኑ ግራ ተጋብቶ በታኑስ መኪና ውስጥ ያሉት ብቻ በመንግሥቱ ላይ ተኩስ ከፈቱ። የተኩሱ አቅጣጫ በሹፌሩ በኩል ስለነበረ መንግሥቱ በሳንድሮቨሩ መቀመጫ ውስጥ ገብቶ በሹፌሩ ጥንከሬ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር በመብረር ወደ ግቢው ውስጥ ዘለው በመግባት ዳኑ። ገዳይ ቡድኑም ለመከታተል ቢሞክርም አልተሳካለትምና በዚያው ወደ ደብረዘይት አቅጣጫ አምርቶ ተሰወረ። የማሰሰቻውም ፈንጅ ፈነዳና ለጊዜውም ቢሆን ለሚውን ሰው አደናግሮታል።

በታኑሱ ውስጥ ተከታትለው ለመግደል የሞከረት እንደኛው የመቶ አለቃ መርዕድ ማሰው የአየር ወለድ ባልደረባ፤ ሁለተኛው ግርማ ሣባ ኢ ኤል ኤፍ የተባለው የኤርትራው ድርጅት ባልደረባ ሦስተኛው ስሜነህ ሹምዬ የተባሉት ለመሆናቸው በተከታታይ በተወሰደው የደርግ የምርምራ እርምጃ ለማወቅ ተችሏል።

በማግስቱ ምሽት መንግሥቱ ሀይለማርያም በጄኔራል ተፈሪ በንቲና በሌ/ ኰ አጥናፉ አባተ ታጅበ በቴሌቪዥን ለህዝብ በቀረበበት ወቅት ለተደረገለት ጥያቄ ሲመልስ የቆሰለው በመሀይቱ ላይ መሆኑንና ቁስሉም ቀላል እንደነበረ ጅምናስቲክ እየሠራ ጤንነቱን ገለጸ። ከዚህ ስነሥርዓት በኋላ መንግሥቱ ያተኰረው ይህን ግድያ የፈጸሙበትን የማወቁ ጉዳይ ስለነበረ አዲስ አበባ ከተማና አካባቢው ሁሉ በመረጃዎች ተወረረ። ሁለት የቴክኒክ አዋቂዎች የሆኑ ሰንዳፋ ፖሊስ ኰሌጅ በፖለቲክ ትምህርት ላይ የሚገኙ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ በአስቸኳይ ወደቀይ መስቀል አደባባይ ሄደው እንዲያጣሩ በታዘዘው መሠረት ሄዱ። የተለቀመው ቀለህ የኢዚ ኢፍኢን ጠመንጃዎች ቀለህ መሆኑ የታወቀ ሲሆን የማን እንደሆነ አይታወቅ እንጅ አያሌ የገር ዱካዎች ተነስተዋል።

እንዲጋጣሚ ሆኖ ይህ ሙከራ ከመፈጸሙ ሦስት ቀን በፊት ሰንዳፋ የሚገኘው የፖሊስ መኰንኖች ትምህርት ቤት ዕቃ ግምጃ ቤት ሌሊት ተሰብሮ መጠኑ ብዙ የሆነ ኡዚ ኢፍኢን ከርባይን ባልታወቁ ሰዎች ተወሰደ። በዚሁ ዕለት ተረኛ መኰንኑና ሌሎች ለጥያቄ ሲያዙ በዘብ መደብ ላይ የነበረው ወታደር እጁን አልሰጥም ብሎ ኢህአፓ ያቸንፋል ካለ በኋላ ራሱን በያዘው ጠመንጃ በመግደሉ ድንጋጤ ተፈጠሮ ነበር። ወታደሩ እራሱን ሲገድል እኔም በበታው ነበርኩ።

ይህ በመሆኑ በአደጋው ላይ የተገኘው የቴክኒክ ማስረጃ በግምጃ ቤት ከጠፉት መሣሪያዎች ጋር ተመሳሳይ ከሆነ የፖሊሶች ሴራ ነው ተብሎ በነዓለማየሁ ላይ ቢያተኩርም በዚህ ደረጣ ላይ የመቶ አለቃ መርድ የተባለው ተከፋይ እንደነበረ በቂ መረጃ ሌ/ ኰ መንግሥቱ በማግኘቱ የምርመራው ኃላፊዎችን ሁሉ መቶ አለቃ መርዕድ ሳይሞት እጁን





ይዞ የሚያቀርብለት ውለታ ለመክፈል ቃል በመግባት ላይ እንዳለ ተሰማ። ይህንንም የሚያደርግበት ምክንያት ምርመራው ምናልባት ወደሸንበል ዓለማየሁ የሚያመራ ይሆናል ብሎ በመጓጓት ነበር።

የመቶ አለቃ መርዕድ ግን መንግሥቱን ከሳተ በኃላ የመደበቂያ በታውን ኰልፌ ወደ አሥረኛ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ በማዘር ወደ መርከቶና ወደሌሎቹም በታዎች በመዘዋወር በወታደሮች ላይ ምልመላ ያካኺድ በለነበረ እንዲጋጣሚ ሆኖ የመቶ አለቃ መርዕድ ኤርትራ በነበረ ጊዜ በጦሩ ውስጥ በተለይ በሱ የመቶ ይሠራ የነበረ የአየርወለድ ወታደር በፊቃድ ወደአዲስ አበባ መጥቶ ሲዘዋወር አገኘው። መርዕድም በናፍቆት ከነጋገረው በኋላ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ገልጾለት ሌሎችንም ወታደራዊ አባሉች እያመጣ እንዲያነጋገረው አደረገ። ይህ ወታደር ወዲያውኑ ወደ ፀጥታ መሥሪያ ቤት ሄዶ ሪፖርት አደረገ። የፀጥታው ክፍልም በአስቸኳይ ለመንግሥቱ አስተላለፈ። መንግሥቱም በጥንቃቄ እንደእንቁላል እንከባከቡችሁ እምጡልኝ ሲል በጉጉት ተማጠነ።

የቀጠሮው ሰዓት እንደደረሰ ሌ/ ኰ ልዑል ሰገድ ከፖሊስ የምርመራ ክፍል ሻለቃ መኰንን ሥዮም በፀጥታው ክፍል ለረዥም ጊዜ የሠራ የጦር ሠራዊት አባል ሌሎችም መኰንኖችና ወታደሮች አስከትለው ወደበታው ሄዱ። የመቶ አለቃ መርዕድ በቀጠሮው መሠረት በበታው ቆሟል። ሻለቃ መኰንን ስዮም ከመኪና ዘሉ በመውረድ በመቶ አለቃ መርዕድ ላይ ተጠመጠመ። መርዕድም በኪሱ የያዘውን በንብ በማፈንዳት የራሱንና የሻለቃውን ሰውነት ብትንትኑን አወጣው። ሌ/ ኰ ልዑል ሠገድ ከአደጋው ለማዳን ሲቃጣ በፍንጣሪ ስለቆሰለ ወዲያውኑ ወደፖሊስ ሆስፒታል ተላከ። አንድ ሌላ መኰንንና ወታደሮች በፍንጣሪ ሕይዎታቸውን አጡ። በዚህ እለት ሁኔታውን ለማወቅ እኔና ሌሎች መኰንኖች ሌ/ ኰ ልዑልሰረድ ከተኛበት ፖሊስ ሆስፒታል ድረስ በመሄድ ጠይቀነዋል። በጣምም የድንጋጤ መንፈስ ይታይበት ነበር።

ይህ ሁኔታ ለመንግሥቱ ሪፖርት ሲደርሰው አልተደሰተም ምክንያቱም የሌሎችን ስም ዝርዝር ይፈልግ ነበር። ሆኖም በመርዕድ ላይ የነበረውን ስጋት አስወገደ። የሌሎችን የመርዕድ ጓደኞች በዚህ ላይ ልገለጸውና ከኢኤልኤፍ ድርጅት የተላከው ግርማይ ሣባ በደህና ወደ ኤርትራ ሜዳ በመሄድ በሰላም ከድርጅቱ ተቀላቀለ። ግን ሜዳው አልተመቸውምና ፋሉል ብሉ ከተገነጠሉት ከኢኤልኤፍ ተስፈንጣሪ ጋር አብሪ በመሆኑ ለተወሰነ ጊዜ በዚሁ ውስጥ ቆየ። ይህ ሰው እንደገና አዲስ አበባ ተመልሶ ከኢህአፓ ጋር ተሰልፎ ነበር። ግን ከአዲስ አበባ ሳይወጣ የደርጉ ቀይ ሽብር ጊዜ ተይዞ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሏል። ሦስተኛው ስሜነህ ሹምየም በዚሁ ሽብር ጊዜ ተይዞ መገደሉ ተረጋግጧል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሁኔታ ያልተሳካ ሙከራ ከተደረገ በኋላ መንግሥቱ በቁጭት በጠላቶቹ ላይ እርምጃ መውሰዱን በመቀጠል የቅርብ የሥራ ጓደኞቹንና በጀኔራል ተፈሪ በንቲ ላይ የግድያ እርምጃ ወሰደ። ዝርዝር ሁኔታውን ክፍል ፫ ከሚለው ምዕራፍ መረዳት ይቻላል።



ብርጋዴር ጀኔራል ተፈሪ በንቲ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዋና ሊቀመንበር

ቅዳሜ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ ም



## ክፍል ፫
## የጄኔራል ተፈሪ በንቲ አገዳደል

1 ብጀኔራል ተፈሪ በንቲ ርዕሰ ብሔር ዘኢትዮጵያ ከጦር ሠራዊት
2 ሌ ኰ አሥራት ደስታ የማስታወቂያ ኃላፊ የደርግ አባል ከጦር ሠራ ዊት
3 ሌ ኰሎኔል ኃይለሥላሴ የደህንነት ኃላፊ የደርግ አባል ከጦር ሠራ ዊት
4 ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ የአስተዳደር ኃላፊና ዋና ጸሐፊ የደርግ አባል ከፖሊስ ሠራ ዊት
5 ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል የኢኮኖሚ ኃላፊ የደርግ አባል ከጦር ሠራ ዊት
6 ሻምበል ተፈራ የደርግ አባል ከፖሊስ ሠራ ዊት
7 የ፶ አለቃ ኃይሌ በላይ የደርግ አባል ከፖሊስ ሠራ ዊት

የካቲት 3 ቀን 1968 ዓም ከጧቱ ሁለት ሰዓት ላይ ያልታሰበ የደርግ አባሎች ስብሰባ ተደርጎ ሌ/ ኰ መንግሥቱ ሌ/ ኰ ተስፋዬ ወልደ ኪዳን የሃምሣ አለቃ ለገሠ አስፋው ሆነው ከሌ/ ኰ ዳንኤል አስፋው የደርጉ የጥበቃ ኃላፊ ጋር ስማቸው ከላይ የተጠቀሱት የደርግ አባላት ላይ እርምጃ ስለሚወሰድበት ጉዳይ በሚስጢር በመወያየት በደርጉ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ተወንጅለው እዲታሰሩ ተስማሙ። የደርግ አባላት አዳራሹ ውስጥ ከገቡ በኋላ ሌ/ ኰ ዳንኤ የታጠቁ ወታደሮችን አስከትሎ በደርጉ የስብሰባ አዳራሽ ዘው ብሎ ገብና ከትንሽ ማስታወሻ እያነበበ ከላይ የተዘረዘሩትን የሰባቱን የደርግ አባላት ስም እየጠራ እስኩቶ እያንዳንዳቸውን እጅ እያሰረ በተለያዩ በሮች አስወጥቶ ከደርጉ የስብሰባ አዳራሽ ሥር በሚገኘው የቤተ መንግሥቱ የጠጅ ቤትና የበረዶ ማከማቻ ውስጥ አስገባቸውና በሩም የፊጥኝ ተዘጋ። ወዲያውኑ ሌ/ ኰ ዳንኤል፣ ሌ/ ኰ ሥዩም መኩንን፣ ሻለቃ ታምራት ሻመና ዶክተር ሰናይ ልኬ ይሆኑና ተሰባስበው በሌሎቹም ላይ በተጨማሪ እርምጃ የሚወሰድባቸውን ሰዎች ዝርዝር በየበኩላቸው ለማቅረብ ተስማምተው ወደየቢሯቸው ተስማሩ። ሌ/ ኰ መንግሥቱ፣ ሌ/ ኰ ተስፋዬ ወ/ ኪዳንና የ፶ አለቃ ለገሠ አስፋው በመንግሥቱ ቢሮ መግቢያ በር ላይ ፊልድ ጃኬት እንደለበሱ በመወያየት ላይ ነበሩ።

ሻለቃ ዮሐንስ የደርጉ የምርመራ ሹም በቤተ መንግሥት ውስጥ የተፈጸመውን ሁሉ አላወቀም ነበርና የዘወትር ሥራውን ለማከናወን በዋናው ቤተመንግሥት በር ወታደራዊ ሰላምታ ተደርጎለት ወደቢሮው ይገባል። ዮሐንስ በሌ/ ኰ ዳንኤል ዝርዝር ውስጥ እርምጃ ከሚወሰድባቸው ሰዎች የመጀመሪያው ነው፤ በዚህ መሠረት ዳንኤል የዮሐንስን መግባት በመጠባበቅ ላይ ስለነበረ የዮሐንስ ወደ ቤተ መንግሥቱ መግባት የዳንኤል ትልቅ ፈንጠዝያ ነበር። ሻለቃ ዮሐንስ ትንሽ ቆጭ ብሎ ሲያስተውል በግቢው ውስጥ የሚዘዋወር ሰው ስለሌለና ጭር ስለአለ ይጠራጠርና ከቢሮው ወጥቶ መኪና እየነዳ ሊወጣ ሲሞክር እበሩ ላይ መግባት እንጅ መውጣት እንደማይቻል ተነገረው። እንደገና በሁለተኛው በር ቢሞክር ተመሳሳይ

መልሰ አገኘ። ከዚህ በኋላ ወደ ቢሮው ገብቶ ማዳመጥ ጀመረ። የሌ/ ኮ ዳንኤል መልእክተኞች በሞት ሠረገላ ተፈናጠው ከሻለቃ ዮሐንስ በር ላይ ደረሱና ጥሩት የሚለውን መልክት አስተሳሰፉ። ሻለቃ ዮሐንስም በጠረጴዛ ላይ ያጋደመውን ኡዚ መትረየስ አንስቶ ሽጉጡን ከጉያው ሰጥሮ መልክተኞቹን ከኋላው እየመራ የሃምሳ ሜትር ርቀት ካለው የዳንኤል ቢሮ ደረሱ። ሻለቃ ዮሐንስም ከኋላ ክላሽን ወድረው የሚከተሉትን አንድ የ፶ አለቃ አንድ የ፲ አለቃ ከመቅጽበት ወደኋላው ዙሮ በኡዚው መትረየስ ገደላቸው። ቀጥሎም የዳንኤልን በር ለመክፈት ሲሞክር ዝግ ሆነበትና የመስኮቱን መስታወት በፈሙዝ ሰብሮ ዳንኤል ክላሽን ጉትቶ ለመነሳት ሲቃጣ ጭንቅላቱን በኡዚ በመምታት ገደለው። ከዚህ በኋላ በሌ/ ኮ መንግሥቱ ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ የሁለቱን ወታደሮች ክላሽን ተሸክሞ ሲገሰግስ ግዳጅ የሚጠባበቀው ሥናይ ልኬ ተኩስ ሰምቶ ወደ ዳንኤል ቢሮ ሲሮጥ ከመንገድ ዮሐንስን አገኘትት ተፈጸመ ወይ ይለዋል። ዮሐንስም አወ ተፈጸመ በማለት ደረቱን በኡዚ መታው። ሆስፒታል ሲሳክ ከመንገድ ሞተ። (ተፈጸመ ወይ ማለት እነ ተፈሪ በንቲ ተገደሉ ወይ ማለት ነው።) ቀጥሎም ወደ መንግሥቱ ሲገሰግስ መንግሥቱ ተኩስ ሰምቶ ወደ ጥበቃ ክፍሉ በሩጫ ሲበር ከመንገድ ተያዮና እያሌ ጥይት ተረጭቶበት ሳይነካ ጥበቃው መደብ ዘሎ ገባ። ሥናይ ልኬ ከመንገድ ባያሰናክለው ኖሮ መንግሥቱ ባሳመለጠውም ነበር ብለን እንገምታለን።

ሻለቃ ዮሐንስ በዚህ ብቻ አልቆመም የያዛቸውን ክላሾኖችና ኡዚ እየቀያየረ ወደ ጥበቃው ክፍል ጥይት መርጨቱን አላቋረጠም። ነገር ግን ሌ/ ኮ መንግሥቱ ከታንክ ውስጥ ዘሎ በመግባት ዮሐንስ ወደሚገኝበት አቅጣጫ ያሉትን ውድ የቤተ መንግሥቱን ቤቶች እንዲያፈራርሱ የከባድ መሣሪያ ጥይት ማስተኩስ ጀመረ። ዮሐንስ ግን በታ እየለዋወጠ ስለነበረ በብዙ ሥራዊት የተከበቡ መስሏቸው የመከላከል እንጅ የማጥቃት ወኔ አላሳዩም። እነ መንግሥቱ በተኩስ ላይ እያሉ ሻለቃ ዮሐንስ ወደ ሌ/ ኮ ሥዮም መኮንን ቢሮ በመግባት ሥዮምን ካጣው በኋላ ወደ ውጭ ወጥቶ በራሱ ሽጉጥ ራሱን ገደለ። በሌ/ ኮ ሥዮም ቢሮ የገባው ሊገድለው ነው ለማለት ያስቸግራል ምክንያቱም ጥብቅ ወዳጅ ስለነበሩ።

ከዮሐንስ ሞት በኋላ እነመንግሥቱ ከምሽጋቸው ለመውጣት አልደፈሩም። በያቅጣጫው በቤተ መንግሥት ውስጥ የነበሩት ወታደሮችና የደርግ አባሎች ሲሰባሰቡ ተመልክቶ ለመጨረሻ ጊዜ ከታንክ ወጥቶ ነው የተቀላቀለው። ሻለቃ ዮሐንስ የፈጸመው ተግባር መንግሥቱ ጨርሶ አላወቀውም ነበር። እርሱ የሌ/ ኮ ዳንኤልና የዶክተር ሰናይን መገደል ከሰማ በኋላ በጣም ደነገጠ። ወድያው ጥቂት ገዳይ ቡድኖች አስከትሉ እነጀኔራል ተፈሪ በንቲን የታሰሩበትን ቤት በመከፈት በንዴት በመትረየስ ገደላቸውና አስከሬናቸውን ወህኒ ቤት ተወስደ በማይታወቅ በታ ተቀበረ። ግን ያዩና የሚያውቁ ሊኖሩ ይችላሉ። ወደ ወህኒቤት አስከሬናቸውን የወሰደው አይታወቅም። «አብዮተኞቹ» ሌ/ ኮ ዳንኤልና ዶክተር ሰናይ ልኬ አብዮታዊ አቀባበር እንዲደረግላቸው ሌ/ ኮ መንግሥቱ አዘዘ።





ቀጥሎም ምስ ሊያደርጉን የነበሩትን ፀረአብዮተኞች ቀድመን ቁርስ አደረግናቸው ብሎ ንግግር አደረገ።

እስከሁን ያልተነሰ ነገር ቢኖር የሌ/ ኮ አጥናፉ ጉዳይ ነው። በክፍል ሁለት እንደተመለከተው መንግሥቱ ላይ ግድያ በሚሞከርበት ጊዜ አጥናፉ ከዚያ በፊት አድርጎት የማያውቀውን ከመንግሥቱ ተነጥሉ ሰዎች ሊያነጋግር ወደኋላ ቀርቶ ነበር። በዚያም ምክንያት እንዴት ሊቀር ቻለ የሚለው ጉዳይ አጠያያቂ ስለነበረ በሴራው ውስጥ አጥናፉ ያለበት መሰሉ ታያቸው።

እነ ሌ/ ኮ መንግሥቱም የአጥናፉን ጉዳይ በሌላ በኩል እያጣሩ ቢሆንም በነጄኔራል ተፈሪ በንቲ ግድያ ላይ እንዳይገኝና አልበማማም ብሎ እንዳያስቸግር ለማገለል የወለጋን ክፍለ ሀገር እንዲጐበኝና ለወለጋ ህዝብ የታማኝነትን ባንዲራ እንዲሰጥ ተላከ። በአዲስ አበባ ቤተመንግሥት ውስጥ ይህ ሁሉ ግድያ ከተከናወነ በኋላ መንግሥቱ ለአጥናፉ ስልክ ደውሉ በአስቸኳይ እንድትመጣ ይለዋል። አጥናፉም ሁኔታውን በራዲዮ ሰምቶ ኖር ለምን እኔ እንዳውቅ አልተደረገም አለው። መንግሥቱም ከመጣህ በኋላ የምታቀርበው ጥያቄ ይሆናል ብሉ ስልኩን ዘጋበት።

አጥናፉ ወደ አዲስ አበባ እንዳይመለስ ከአዲስ አበባ ብዙ መልዕክት ደርሰት ነበር ግን ግትር በመሆኑና መንግሥቱ በሕይወቱ አንዳችም ነገር ያደርጋል ብሉ ስለማይጠረጥር በጥሪው መሰረት አዲስ አበባ ተመለሰ። ቀጥሎም የነበረው ፐሮግራም ወደ መንግሥቱ ቢሮ ገብቶ መነጋገር ስለነበረ ገቢና ሰላምታ ተሰጣጥተው ቁጭ አሉ። ቀጥሎም የነበረው የአጥናፉ ጥያቄ ለምን ይህ ሁሉ ጉዳይ እንደተፈጸመ ነበር፤ መንግሥቱ ግን ይህን ጥያቄህን በሌላ ጊዜ እንመለስበታለን አሁን የነሌ/ ኮ ዳንኤል አስሬውን የቀብር ሥነሥርዓት አስፈጽም እኔ እዚህ ሁኜ ማንኛውንም ሁኔታ እጠባበቃለሁ አለው። አጥናፉም በመቀመጫው በመንቆራጠጥ ጥያቄዎች ለመደርደር ሲዘጋጅ ከቢሮው ውስጥ በሁለት ማዕዘን መሣሪያ የዘቀዘቁ ወታደሮች ተመለከተ። በፍጥነትም የመንግሥቱ ሙከራ ስለገባው የመቃብሩን ሥነሥርአት ለማስፈጸም ተስማምቶ ወጣ። የዳንኤል አስከሬንም የአብዮተኞች መቃብር ከሆነው ዮሴፍ ቤተክርስቲያን በአብዮተኞች፣ በካድሬዎች፣ በፖለቲካ ኃላፊዎችና በአፋኞች ወዘተ ታጅቦ ነበር። «አንድ ዳንኤል ቢሞት የሽህ ፀረ አብዮተኞች ደም ይፈሳል» የሚለው የሌ/ ኮ መንግሥቱ መፈክር ተሰማ። ሌ/ ኮ አጥናፉም ይህን ሁኔታ ካየና ካስቀበረ በኋላ ወደቤቱ ተመለሰ።

በሌ/ ኮ አጥናፉ በተከታታይ መንግሥቱ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ያውቃል። ደግሞም ከተለያዩ ምንጮች ይነገረዋል የመንግሥቱ የወደፊት ርምጃ አስጊነቱን እየገመገመ ለአጥናፉም ሆነ ለሌሎች የደርግ አባላት የሚነግሩ አልታጡም ነበር። እሱ የሚለው ግን መንግሥቱ « ጉበዝ ሰው ነው» አገሩን ይወዳል እኛም ብንሆን በየደቂቃው እየተጋደልን አገሪቷን እንዴት ልንመራ እንችላለን ስለዚህ ዕድል ይሰጠው ነበር። ስለራሱም ደህንነት

ማስጠንቀቂያ ሲሰጠው የምንተማመን ስለሆነ ምንም አያደርገኝም እያለ ዘወትር የሚናገር ከመሆኑም በላይ ከሱ ጋር የወገኑ እያሌ ሰዎች ጉዳት ሲደርስባቸው በለዘብተኝነት አሳልፎታል። አጥናፉ እነደንኤልን በስቀበረ ቀን ማታውኑ ከመኖሪያ ቤቱ ለተገኙት ጓደኞቹ የሰጠው አስተያየት በመጠኑ ቢሆን የመንግሥቱ የወደፊት ጉዞ አደገኛ መሆኑን የሚያስረዱ መልእክቶች ነበሩ። በተለይ በቢሮው ውስጥ ጠመንጃ አስወድሮ ያደረገውን ውይይት ሲያነሳ እንደቲያትር አድርጐ ያቀርበዋል።ሆኖም አሁንም የቀረው እምነት አለው። መንግሥቱ ስሀገሩ ይሠራልና ዕድል እንስጠው ባይ ነበር።



መንግሥቱ ኃይለማርያም

ሻለቃ አጥናፉ አባተ





## ክፍል ፱

## ተወሳሰበው የቶ ዩ ሁኔታዎችና የኢማሌድህ ግንበር

ያለፈው ስርዓተ መንግሥት ባለመፍቀዱ ለረጅም ጊዜ አገራችን የቆየችው አንድ ወጥ በሆነው መንግሥታዊ መዋቅር ነበር። በዚህ የተነሳ የተለያዩ አመለካከቶችና ያገር ማሸሻያ ሃሳቦች ያልዳበረበት ፊውዳላዊ ስርአት የነገሠበት በመሆኑ ህዝቡን ለረጅም ዘመን ሰጥለጥ ብሎ ሲገዛ ቆይቶቷል። በዚህም የተነሳ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ጥያቄወችን ለማንሳት አገር አቋርጦ ወንዝ ተሻግሮ መሄድ ያስፈልግ ነበር። ታድያ አሁን እንደሚታየው ህዝቡን በተለያዩ ምክንያቶች ምርር ብሎ እዲናገርና እንዲበረግግ አደረገው።

በዚህ አማራጭ ባልነበረበት ሁኔታ ወታደሩ የለውጡን በር በርግዶ መግቢ አማራጭ የሌለው ሆኖ ተገኘ። ህዝቡ ባልተደራጀበት በዚህ ወቅት የተደራጀ በስነሥርአት የታረቀው የወታደሩ ክፍል ባይኖር ኖሮ ስርአተ አልበኑት ይነግሣል ተብሎ ይገመት ነበር። መበታተንና እርስ በርስ መነታረክ ይፈጠራል ተብሎ ስጋት ነበር። ከዚያም ስነበረው ፊውዳላዊ ስረዓት አመች መንገድ በመፍጠር ለውጡ በቀጥታ ተቀልብሶ ወደነበረው የጭቆና ሥርዓት እንደሚንበረከክ ግልጽ ነበር።

የኢትዮጵያን ለውጥ አስመልክቶ በውጭም ዓለም የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ሆኑ ተራማጆችና ተማሪዎች እንዲሁም አገር ወዳዶች የአብዮት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ሁሉም በየአቅጣጫው አገር ቤት ከገባ በኋላ ለውጡ በደበልጥ እንዲመነጠቅ ረድቶታል። ነገር ግን ንዑስ ከበርቴው እርስ በርሱ ባለመስማማት ከሁለት በመሰንጠቅ መኢሶንና ኢህአፓ በመባባል መኢሶን የተባለው ከደርግ ጋር ወግኖ ሲነሣ ኢህአፓ ደግሞ እሸፈረኝ በማለት ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት በሚል አቋም ወሰዱ።

እነዚህ ሁለት ድርጅቶች አንዱ አንዱን ለመጣል በሚያደርጉት መሯሯጥ እያሌ ወጣቶችና የህዝብ ወገኖች ያለ አግባብ ወድቀዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ደርግ ፋታ በማግኘቱ ሰደድንና ወዝ ሊግን በማቋቋም መከላከያውን ሲያዘጋጅ በዚሁ ወቅት የሰደድ መቋቋም መኢሶን አስጊ መሆኑን ከገመቱ በኋላ ነበር። ይሁን እንጅ ሰደድ ከመፈጠሩ በፊት ወዝሊግ በህቡዕ በመደራጀቱ ለወዝሊግ ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጡ የነበሩት ዶክተር ሰናይ ልኬንና ሊ/ኩ ዳንኤል አስፋው ሰደድ ሲቋቋም የወዝሊግ ወታደራዊ ክንፍ ሆነው ለሁለቱም ድርጅቶች ታማኝ ሆኑ።

እነ ሊ/ ኩ መንግሥቱ ሰደድን የህልውናቸው መጠበቂያ ታማኝ ድርጅት ሲፈጥሩ የደርግ አባሎችም በዚሁ ድርጅት ውስጥ ተኰለኰሉ። በተለይ እነ ዶክተር ሰናይና ዳንኤል አስፋው ከወዝ ሊግ ውስጥ አባሎችን እየጠቆሙ ወደ ሰደድ እንዲሔዱ

በማድረግ ሰደድ በበለጠ ለወዝሊግ ወታደራዊ ክንፍ እንዲሆን አደረጉ። በወዝ ሊግ ውስጥም ከፍተኛ ሚና ይጫወቱ የነበሩ ብዙ መኩንኖች የተከማቹበት ድርጅት ነበር።

እነ ሌ/ ኮ መንግሥቱም በሰደድና በወዝሊግ ሙሉ እምነት ስለነበራቸው የዶክተር ሰናይ ልኬና የሌ/ ኮ ዳንኤል ደበ እስከተገደሉ ድረስ ሳይታወቅባቸው ቆይቷል። ሰደድ በተቋቋመበት ጊዜ ከጦሩ በአባልነት ለመመልመል በነበረው እቅድ መሠረት።

፩ በፖሊስ መኩንኖች ማሰልጠኛ ት/ ቤት ሰንዳፋ

፪ በሆለታ ጦር ትምህርት ቤት

፫ በአየር ሀይል ጠ/መምሪያ ውስጥ አንድ ወር የፈጀ የፖለቲካ ትምህርት ሲሰጥ ቆይቷል። ይህ ሰደድ የተባለው ድርጅት መኢሶን የማይፈልገው ድርጅት ቢሆንም በዚያን ጊዜ የህዝብ ድርጅቱን በበላይነት የሚመራው መኢሶን በመሆኑ ከማደራጀት እንጻር የህዝብ ድርጅት ሀላፊወች አቶ ሀይሌ ፊዳና መሰፍን ካሱ እንዲሁም ፍቅሬ መርድ የተባሉት በቅርብ በመከታተል ለኩርሱ ሀላፊ ከሆነው ዶክተር ሰናይ ልኬ ጋር በአስተማሪነት ተከፋይ ሆነዋል። በትምህርት አሰጣጣቸው ላይ በበለጠ የሚያተኩሩት መኢሶን ሰደድን እንዴት እንደሚረዳውና በአጠቃላይ መስዮ ሰበሹን ለመርዳት እንደተዘጋጄ የሚያሳይ ነበር። ይህ ኮርስ በመሰጠት ላይ እንዳለ ፍቅሬ መርድ የተባለው ተገደለ። በሌሎች በሁለት በታዎች ትምህርቱን የሚከፈሉት አባሎች ብዙ ሲሆኑ በሰንዳፋ ማሰልጠኛ የመኩንኖች ት/ ቤት የነበሩት ግን ስልሣ ሰባት ከፍተኛ መኩንኖች ነበሩ።

በሠናይ ልኬም ሆነ ከላይ በተጠቀሱት የመኢሶን አባሎች አገላለጽ ከሆነ የአማርኛና የትግሪኛ ተናጋሪወች ለሰደድ መመረጥ ጉዳይ በጣም ጠባብ መሆኑን ተገንዝበናል። ብዙወቹ መኩንኖችም ከምልመላው ለመዳን ጥረት አድርገዋል። የኮርሱ ሀላፊ ዶክተር ሰናይ ልኬ በተቻለው መጠን የድሀ ቤተሰብ መሆኑን በማስረዳትና እንዲያውም እናቱ አማርኛ የማያውቁ መሆናቸውን እዘውትሮ ይናገር ነበር። በኮርሱ ከተሰተፉት መኩንንኖች አንዱ እኔ ነበርኩ። ሰናይ አንድ ቀን ከተከፋይዎች ውስጥ አማርኛ ወይም ትግርኛ የማይችሉ እጃቸውን እንዲያወጡ ጠይቆ ሰባት ሰው ብቻ ስለሆነበት ራሱን በእጁ ይዞ በመምህ ላይ እንዳለ ሰዓት ደርሰ ስለነበር በንዴት ከክፍል ወጣ። በተለይ ሰደድ የሌ/ ኮ መንግሥቱ እምበገነንነትን የሚገነባ በመሆኑ የመንግሥቱና የመኢሶን ቃልኪዳን እያከተመ ሲመጣ ለጊዜው ከሰደድ ይልቅ ወዝሊግ ች ሉታ ባላቸው መኩንኖችና ሲቪሎች የተመሰረተ በመሆኑ ሰደድን ለማቋቋምና ለመርዳት የሚል ሽፋን ተደርጉ የወዝ አባሎች በሰደድ ውስጥ ገብተው አመራሩን እንዲጨብጡ ሆነ። በመንፈስ ሰደድና ወዝሊግ የአንድ ቤተሰብ አባሎች ናቸው በሚል እምነት ሳቢያ የደርግ አባሎችም ሆኑ ሌሎች ወታደራዊ አባሎች በሁለቱ ድርጅቶች





ውስጥ ደስ ባላቸው ለመግባት እንደሚችሉ ተደረገ። ይህ ሁሉ የተወሳሰበ ሁኔታ ስለድርጅትም ሆነ ስለሶሻሊዝም ጨርሰው በማያውቁ የወታደር አበሎች ዘንድ ችግሩ ተደቅኖ ነበር።

ሰደድ፣ የወዝሊግ፣ መኢሶን፣ ማሌሪድ፣ ኢጭአት፣ ግንበር ከፈጠሩ በኋላ በየዜማ ላይ ናቸው ተብሉ ላይና ታች ዱብዱብ ሲሉ ደርግና መኢሶን ስጋ ሚዳ (ታጠቅ ሠፈር) በመሰልጠን ላይ በሚገኘው የሚሊሽ ጦር መጋጨታቸው ተሰማ። ይህንን አስመልክቶ መኢሶን ሚልሽያው መታዘዝ ያለበት በህዝብ ድርጅት ስለሆነ እኔ ማዘዝ አለብኝ ሲል ደርግ ደግሞ የለም መታዘዝ ያለበት በአብዮታዊ ደርግ ነው፤ መኢሶን አደራጅ እንጂ ፓርቲ ስለይደል እንደዚህ ያለውን ጥያቄ ሁለተኛ እንዳታነሱ በማለት አስጠነቀቀ። በዚህ ምክንያት መኢሶን ለማኩረፍ ሲሞክር ኢሕአፓ ለረጅም ጊዜ ያስቸገረኝን ያህል መኢሶንን በጭር ጊዜ ውስጥ ላጠፋችሁ እችላለሁ በማለት ደርግ መዛቱ ተሰማ። የሁለቱ ማለት የደርግና የመኢሶን የፍቅር ወረቀት በዚህ ረገድ ከተቀደደ በኋላ «ቀኝ መንገደኛው» መኢሶን አብዮቱን ጥሎ ፈረጠጠ «ገራወቹ» ደግሞ ከኔ ጋር ወግነዋል ሲል ደርግ ድንገተኛ መግለጫ ሰጠ።

በዚህ የተነሳ የመኢሶን አባሎች ከደርግ አደጋ ለመዳን ከአዲስ አበባ በመውጣት ለመሸሽ ሞከሩ። ነገር ግን የአዲስ አበባ አምስት በሮች የተዘጉ በመሆናቸው እንዳሁ በቀላሉ የሚታለፍባቸው አልነበሩም። ከዚህም በስተቀር የመኢሶንን መክራ ደርግ ከተመለከተ በኋላ ከደርጉ የዘመቻ መምሪያ ለሀገር አስተዳዳሪዎችና ለየጦር ክፍሉ ቴሌግራም አስተላለፈ።

የቴሌግራሙ ይዘት በአጭሩ እንደሚከተለው ነበር፤ አስራ ስድስት የሚሆኑ አገራቸውን የከዱ የመኢሶን አባሎች ወደውጭ ለመውጣት እየተሯሯጡ ስለሆነ በየክፍላችሁ ታድነው ቢቻል እጃቸውን በመያዝ እንዲሰኩልን፤ እለዚያም በተገኙበት እንዲደመሰሱ የሚል ነበር። በዚህ ቴሌግራም ውስጥ የአቶ ሀይሌ ፊዳ ስምም ይገኝበታል። ይህ ቴሌግራም ከደረሳቸው የጦር አዛዦች ውስጥ አንዱ እኔ ነበርኩ። ቴሌግራሙም በተላለፈ በአምስተኛው ቀን ደግሞ የመኢሶን ቀኝ መንገደኞች የተያዙና የተደመሰሱ መሆናቸውን የሚገልጽና ፍለጋውም እንዲቆም ሌላ መልዕክት ተላለፈ።

ከዚህም በኋላ ድርጅቶች ይዋሀዱ በተባለ ጊዜ ኢጭአት የመኢሶን ጥገኛ ስለነበር ከውይይቱ መገለል አለበት በመባሉ ተሠረዘ።ይህንን አስመልክቶ ውህደት ይፍጠሩ በተባለ ጊዜ በሰደድ ውስጥ የወዝሊግ አባሎች ሰርገው በመግባት ሰደድ የወዝሊግ ወታደራዊ ክንፍ ሆኖ የተቀረፀ ድርጅት መሆኑ ስለተደረሰበት ውህደት በመመሥረት ፈንታ የወዝሊግ አባሎች ተወንጅለው ተመቱ። ከነዚህም ውስጥ የወዝ ሊግንና የሰደድን ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት ውስጥ ሌ/ ኮ ሽታየና ሽለቃ ጌታቸው እግዱ ይገኝበታል።

ይህንን ምስጢር የደረሰበት የመቶ አለቃ ደስታ የተባለው የህዝብ ድርጅት አባል የነበረው ሲሆን ይህን በማድረጉ በእነ ሌ/ ኰ መንግሥቱ ላይ አንጃብ የነበረው አደጋ እስተመ ይህን ሁሉ እንዲወሰሰብ ያደረገው ከላይ እንደተጠቀሰው የወዝሊግ የረቀቀ የሥር ጉ ግብ አሠራር ነው። እዘውትሮ የመሪነት ዕድል ለማግኘት ቀዳዳ ይፈልግ የነበረው ሌ/ ኰ ዳንኤል አበሩው ከሌ/ ኰ መንግሥቱ ተደብቆ ከወዝሊግ ጋር በማሴር መጥውን ጊዜ በመጠባበቅ ላይ እንዳለ ከዚህ በራቀ ሁኔታ በነሌ/ ኰ መንግሥቱና በነሻንበል እለማየሁ ሀይሌ ወገኖች መከከል በተፈጠረው ችግር ዳንኤል አበሩውና ዶክተር ሰናይ ልኬ ተገደሉ።

ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ ሌ/ ኰ መንግሥቱ በድርጅቶችና በግለሰቦች እምነት በሰጣ ፓርቲው የሚመሠረተው ቡድኖች ወይም ድርጅቶች ውህደት ሣይሆን በኰሚንስቶች ውህደት ነው የሚለው ቅስቀሰ እንዲከሄድ አደረገ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በሌ/ ኰ መንግሥቱ ማእከላዊነት ሲሆን ብቻ ነው ተብ ሎ ከቅስቀሣ እልፎ በውሳኔ ተላለፈ። በዚህ መሠረት ሌ/ ኰ መንግሥቱ ግለሰቦችን እየጠራ በማነጋገርና በማሳመን፣ በመገፋፋት፣ በመደለል፣ በማስፈራራት በኢሰፓኮ ማእከላዊ ኰሚቴ ስም ጠሰቶቹን አንድ በአንድ በመምታት ጠያቂ የሌለው ጌታ ሆነ።

ይህን ሁኔታ ያጋለጠው የመቶ አለቃ ደስታም ለሌ/ ኰ መንግሥቱ ይህንን መሰይ ውለታ ከዋለለት በኋላ በሌላ ጥፋት ተወንጅሎ በመንግሥቱ ትዕዛዝ ተገደለ።





## ክፍል ፲

## የሽብር ፈጣሪ ቡድን

የሽብር ፈጣሪ ቡድን በአዲስ አበባ

የሽብር ፈጣሪ ቡድን በአውሮፕላን ጠለፋ

የሽብር ፈጣሪ ቡድን በመርሀቤቴ

በሰውጡ ውስጥ ሳይዘጋጁ ሥልጣን ያመለጣቸው ብዙሀን ግለሰቦች ነበሩ። እ ኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል እንዳለችው አህያ በሰንት ጥረትና ድካም የተገኘውን ለውጥ እኛ ከሌለንበት ወይም እኛ ካልመራ ነው ከሚል የግል ፍላ ጐት በመነሳት የተቀማጠለውን ህዝባዊ አመጽ ለመቀልበስ በየበታው አያሌ ጥረቶች ነበሩ። በዚህም ምክንያት ለውጡ እንደተጀመረ በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ውስጥ ከመለዮ ለባሹና ከሲቪሉ የተውጣጡ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆ ኑ ሰዎች ከፍተኛ ሽብር በመፍጠር የዘረፋ፣ የግድያ፣ የአውሮፕላን ጠለፋ ወንጀል በመፈጸም ፀረሕዝብ እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር።

በ ፲፱፻፷፯ ዓ ም መጀመሪያ ላይ በመለዮ ለባሹ ስም የተደራጁ ጥቂት ግለሰቦች የወታደራዊ ልብሰና መለዮ በማድረግ በሕዝብ ንብረትና በሕይወት ላይ ጉዳት ስለደረሱ ለጊዜው ደርጉ ተከታት ሎ ስለአልደረሰባቸው ከፍተኛ ስጋት አስከተለ። በዘረፋውም ያተ ኰሩት ትላል ቅ መኪናዎችን በመያዝ በሌሊት በመርካቶ ውስጥ በመዘዋወር ሱቆችን በማስከፈት ሸቀጣሸቀጥና ማንኛውንም ዕቃ በመጫን ወደ አለታወቀ በታ ይወስዱ ነበር።

በተለይ እቅመደከማ በሆ ኑ ቤቶች ላይ ገንዘብ፣ ወርቅ፣ ሌላም ጠቃሚ የሆ ኑ ነገሮችን በሌሊት በር አስከፍተው በመግባት ይዘርፋሉ። ይህ አፈጻጸም አስቸጋሪ የወንጀል ሥራ በመሆ ኑ ብዙ ሰዎች በተለይም ነጋዴው ወንጀሉን የሚፈጽመው ደርግ ነው በማለት ህሚታ በየበታው ቀጥ ሎ ስለ እንዲት ሴት ቤት በመግባት ወርቋንና ገንዘቧን በመንጠቅ ላይ እንዳሉ ከቤት ውስጥ የነበረች ሌላዋ ሴት ከዘራፊዎቹ መከከል አንድ ሰው በማየቷ ታጋልጠናለች በማለት እንደገደሏት ሪፖርት ተላለፈ። በዚህ ምክንያት ሌ/ ኰ መንግሥቱ ኃይለማርያም «ይህ አስቸጋሪ ወንጀል እንዴት ሊታወቅ አይችልም» ብ ሎ በፖሊሶች ላይ በመቆጣት አንድ ኮሚቴ በፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ መምሪያ እንዲቋቋምና አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ ተወሰነ።

በዚህም ኰሚቴ ኃላፊ ኰሰኔል ደበበ ሁሪቦ በተባሉት ሀላፊነት በወንጀል አመራር ዘዴ የሠለጠ ኑ መ ኰንኖችንና በለሌላ ማዕረ ጐችን አሰባሰበው በሥራ ላይ በማሰማራት ላይ እንዳሉ ከወንጀል ሠሪዎቹ ውስጥ ዋና የሆነው አሁንም በሕይወት ያለ የኰ ሎ ኔልነት ማዕረግ ያለው ሰው የኮሚቴውን መቋቋም ሰምቶ ኰ ሎ ኔል ደበበ ሁሪሳ

ወዳሉበት ቢሮ ሄደ የቀለጠፈ ሠላምታ በመስጠት ወንጀሉን በሚመለከት ረገድ ጠቅሰ «እኔም በዚህ ነገር እተባበራለሁና ማንኛውንም ነገር ብታማክሩኝ ጥሩ ነው አለ»። ቀጠል አድርጉም «እኔ እኮ ለውጡ እንደተጀመረ ሰሞን አንተ ሥልጣን እንዲታገኝ እጥር እንደነበር ታውቃለህ ወይ» የሚል ጥያቄ አቀረበላቸው። ኩሉ ኔል ደበበም አመሰግነው በዚህ ምርመራ ላይ እንድትተባበር ስልክ እደውልልሀለሁ በማለት አሰናበቱት።

ኩሉ ኔል ደበበ ሁሪሰ በወንጀል ምርመራ ሥራ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው በመሆናቸው ከኩለኔሉ የቀድሞ ታሪክ ተነስተው አሁን የተከሰተበት ችግር እንዳለ ከተገነዘቡ በኋላ ይህ ኩሉኔል የምርመራው መግቢያ ሊሆን እንደሚችል ወሰኑ።

ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ የኩሉኔል ደበበ ምክትል የሆነው ሌላው ኩሉኔል ይህን ሰው በሩቅ አይቶት ኖር በፍጥነት ለኩሉኔል ደበበ «ይህን ወንጀል የሚፈፅመው ይህ ኩሉኔል ነው፤ ስለዚህ ይህን ሰው እስሬ መመርመር አለብኝ አሏቸው።» እንዲጋጣሚ ሆኖ ሁለቱም ኩሉኔሎች ከአንዱ ሥፍራ ተወልደው አብረው ያደጉ የተማሩ ሲሆን የሥራ ገበታቸውም አገናኝቷቸዋል። ኩሉኔል ደበበም አልተቃወሙትም። ነገር ግን ሁኔታውን ከተረዳነው «እጅ ከፍንጅ ለመያዝና ተባባሪዎቹንም ለማወቅ በቅድሚያ መጣር አለብን። በሱም ብቻ መወሰን የሌብንም ምርመራው በማንኛውም ሰው ሆኖ በየትኛውም ቦታ መቀጠል አለበት» አሉ።

የሚገርመው ነገር ቢኖር እኔና ይህ ተጠርጣሪ ኩሉኔል በአንድ ቦታ ተመድበን እንሰራ ነበር። በዚህ ምክንያት ኩሉኔል ደበበ ይህን ሰው ስለፈለጉት በልክ ሲደውሉ እኔ አነሳሁ። ወዲያውም ይህ ኩሉኔል «እኔ ሥራ ስለበዛብኝ በስልክ ለሚፈልገኝ የለም በል » ብሎኝ ስለነበር ኩሉኔል ደበበ ሰላምታ ከሰጡኝ በኋላ፤ እንዳለ ማነጋገር እፈልጋለሁ አሉኝ። እኔም በነገረኝ መሰረት ውሸቴን የለም አልኩት። ወድያውም ማነው የፈለገኝ ብሎ ጠየቀኝ እኔም ኩሉኔል ደበበ አልኩት ምንም የሰጠኝ መልስ የለም ማስታወሻ ደብተሩን አንስቶ ከቢሮ ወጣ።

እንደማስታውሰው ይህ ቀን ሐሙስ ከሰዓት በኋላ ሲሆን እስከ ቅዳሜ ድረስ አልተገናኘንም። በዚህ መካከል በመንዝ አውራጃ መርዕድ ብሩና መስፍን ብሩ የተባሉት የራስ ብሩ ልጆች ሸፍተው ስለነበር እነሱን ለመያዝ ብዙ ጦር ተሰማርቷል። በዚያ የተመደበው ጦር ችግር ስለደረሰበት ይህ ኩሉኔልና ሌሎችም ባለሥልጣኖች ወደዚህ ቦታ ለመሔድ ስለሚፈሩ የጦሩን ችግር ለለማዳመጥ ይሸሹ ነበር። በዚህ ሰሞን የጦሩ ደመወዝ መላክ ስለነበረበት በሸዋ ክፍለ ሀገር ፖሊስ ውስጥ ያለው የበራሪ ጓድ በአንድ የመቶ አለቃ ኃላፊነት ትዕዛዝ ሰጥቶ ደመወዝ ተረክበው ለዓርብ ሌሊት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ወጥቷል።

በዚህን ጊዜ ኩሉኔሉ የደረሰበትን ችግር የምናውቀው ነገር አልነበረም። እሱ





ግን ከፍተኛ ዘዴ አዘጋጅቷል። ቅዳሜ ጠዋት በአንድ ሰዓት ሥራ ገባሁ። የዚህ ኩሉኔል ቢሮ ከኔ ቢሮ ጉን በመሆኑ ድምጽ ሰማሁ። ለማየት ወደሱ ቢሮ ስሔድ ከአንድ የሲቪል ጓደኛው ጋር ቆሞ ብሏል። አብሮት ያለው የሲቪል ጓደኛው የኩቱን እጅጌ አስቶርጦ ስለለበሰ ለመደበደብ ወይም ለመብረር የተዘጋጀ ይመስላል። ሰላምታ ተሰጣጠንና ወደቢሮዬ ተመለስኩ።

የበራሪው ጓድ ኃላፊና ደመወዙን የተረከበው መኩንን ወደቢሮዬ ገብተው ወደ መንዝ እንዳልተንቀሳቀሱ ከነምክንያቱ ነገሩኝ። ምክንያታቸው ኩለኔሉ « ጦሩን ለመጉብኘት ስለምሔድ ደመወዙን እኔ እወስዳለሁ » ስላላቸው ነው። እኔም ትዕዛዙ ባለመፈፀሙና ከጊዜው አንፃር በመነሳት ልክ እንዳልሆነ ለመንገር ወደ ኩሌኔሉ ቢሮ ገባሁ። በዚያን ጊዜ የኩሌኔሉ ቢሮ ሌሎች አራት ኩሌኔሎች ነበሩ። ሰላምታ ተለዋወጥንና የኩሌኔሎቹ አመጣጥ፤ ኩርሳቸው የሆነው ኩሌኔል ለገሠ ወልደ ማርያም ያገር ግዛት ሚንስትር ሆኖ በመሾሙ ደስታቸውን ለመግለጽ የገንዘብ መዋጮ ለመሰብሰብ እንደሆነ አስረዱኝ። ኩሉኔል ግን « መዋጮውን ለመክፈል አሁን ገንዘብ አልያዝኩም በኋላ እከፍላለሁና እስኪ ክፈሉልኝ » ብሎ ከመሀል እንዱን ጠቆመ። ከዚሁም አያይዞ ከማችሁ «ለገሠ አንድ ቀን ሚንስትር እንደሚሆን ይታየኝ ነበር » አለ። ውስጡ በቅናት ያረረ ይመስላል።

ወዲያውም ሁሉም ተሰናብተው ሲሄዱ እኔና ኩሌኔሉ ብቻ ቀረን። ቀጥየም ለምን የእኔን ትዕዛዝ እንደቀየረ ጠየኩት። ይቅርታ ጠየቀኝና «መንዝ ያሉ ወታደሮች ሁልጊዜ ባለሥልጣን ይምጣልን ይላሉ ከንተ በስተቀር የጉብኛቸው የለም። ስለዚህ የፖሊስ አውሮፕላን አያስፈቀዱኩ ስለሆነ ጉብኝቸና ደመወዝም ሰጥቸ ለመመለስ አስቤ ነው» አለ። እኔ ግን በቀና መንፈስ ዘሬ ቅዳሜ ነው ለምን አታርፍም ሳምንቱን በሙሉ ለመሥራት ይከብዳል አልኩት። እሱም ያሰበበት ስለሆነ «አመሰግናለሁ ግን ዝግጅቱን ያጠናቀቅኩት ስለሆነ መሔዱን እመርጣለሁ» አለ። እኔም የመቶ አለቃው የተረከበውን የአባሉች ደመወዝ ሞዴል በድቡት ተሰውሮ እንዲረከብ ካደረኩ በኋላ የሚበረው ከአርጌው አውሮፕላን ማረፊያ ስለሆነ ልሸኝህ ወይ ብለው የለም በመስለ እንዳልቸገር መኪናዬን ወስጄ አቶማለሁ አለኝና በዚሁ ተለያየን። የተረከበውም ገንዘብ ከስምንት ሺህብር አይበልጥም። ከዚህም ውስጥ ወደአራት መቶው የሥራ ማስኬጃ ነው።

በዚህ ዓይነት ኩለኔሉም ከሄደ በኋላ ቀኑ ቅዳሜ ስለነበረ ለዕረፍትና እንደዚሁም ከአዲስ አበባ እስከናዝሬት ያለውን የጥበቃ ሁኔታ ለመቆጣጠር ከዋናው የመረጃ ክፍል የሚያገናኘኝ የመገናኛ ራዲዮ ይዤ ወደናዝሬት አመራሁ። በሞጆ አዲሱ ድልድይ አጠገብ እንደደረስኩ ከመረጃ የሬዲዮ ጥሪ ደረሰኝ። ሁኔታውም ኩሉኔሉ የተሰፈረበትን አውሮፕላን በመጥለፍ ጅቡቲ ገቡ አለኝ። እኔም ማመን ስላቃተኝ ደጋግሜ ጠየኩት። ሪፖርቱን ሊቀይርልኝ አልቻለም።

ሪፖርቱን ለደርጉ የመረጃ ክፍል እንዲያስተላልፍ ነገርኩትና መኪናዬን ከመንገድ ዳር አቆሜ መተከዝ ጀመርኩ። የመረጃ ሠራተኛውም ለደርጉ መረጃ ሲያስተላልፍ ሊፍተናንት ኰሉኔል ዳንኤል አስፋው እዚያ ስለነበረ የኔን ስም በመጥራት «የት አለ» አለው። መረጃውም በመስመር ላይ ናቸው አለው። እኔም በንግግራቸው መሀል ገብቼ ዳንኤልን «እንደምን ዋልክ » አልኩት። ዳንኤልም ሰላምታ ሳይሰጠኝ «ይህ ሌባ የሠራው ሥራ አይገርምህ» አለኝ። መልስ የመስጠት እድል ሳይሰጠኝ «በሁለት ደቂቃ ልዩነት አመለጠኝ አውሮፕላኖች ደርሰውበት ከጅቡቲ ወሰን በመግባቱ አመለጠ » አለኝና ከኔ አንድም ነገር ሳይሰማ ሄደ። በኔና በኰሎኔል ዳንኤል አስፋው መካከል የሚያስተማምን ግንኙነት ስላልነበረ በነገሩ በጣም አሰብኩ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከኰሎኔሉ ጋር አብሬ በመሥራቴ የፈጸመውን ወንጀል ስለማላውቅ እኔንም ሊያጣምሩኝ ይችላሉ በሚል ሃሳብ ዕረፍት ከሌለው ትካዜ ውስጥ ሰመጥኩ።

ወዲያው በደርግ ጥያቄ መሠረት አውሮፕላኗ ከሁለት የሸለቃ ማዕረግ ካላቸው ፓይሎቶች ጋር ስትመለስ ኰሎኔሉን መልሰን እናስረክብም በማለት በጅቡቲ የነበረው የፈረንሳይ አስተዳደር ከለከለ። ኰሎኔሉም ከአውሮፕላኑ እንደወረደ ለደመወዝ የያዘውን ገንዘብ ለጅቡቲ ባለሥልጣኖች በማስረከብ የመንግሥት ገንዘብ መሆኑን አስረዳ። በዚህም ጊዜ የሲቪል ጓደኛው አብሮት ስለነበር ከሱጋር እጁን ሰጠ።

ውሎ አድሮ ፓይለቶች ከተመለሱ በሂላ በሰጡን ማብራሪያ መሰረት ጠላፊዎቹ የፈጸሙትን ትርኢት እንዲህ ሲሉ ያስረዱሉ።በመጀመሪያ ኰሎኔሉ ወደ አብራሪው ዘንድ ሲገባ ሁለተኛው አብራሪና የኰሎኔሉ ጓደኛ ከኋላ ይቀመጣሉ፤ ወዲያውም ኰሎኔሉ ሰላብ ሽጉጥ ያወጣና በፓይለቱ ላይ በመደገን ወደ ሞቃዲሸ እንዲበር ይጠይቀዋል። ፓይለቱም ቤንዚን የለም ይለዋል። በሁለተኛው ትዕዛዝ ወደ የመን ይለዋል። እርቀታቸው እኩል ስለሆነ ቤንዚን አይበቃም ይለዋል። የመጨረሻ ትዕዛዝ ጅቡቲ ይለዋል። በዚህ ተስማምተው ጅቡቲ ማረፍ ቻሉ። በዚህን ጊዜ ከኋላ ከተቀመጡት መካከል ሲቢሉ ከመቀመጫው ተነስቶ አጠገቡ ያለውን ፓይለት እንዳትንቀሳቀስ በማለት እጁን ከኪሱ አስገብቶ ማስፈራራት ጀመረ። ሰውየው በጣም ግዙፍ ስለነበር መግደል ቀርቶ ሰው የሚውጥ ይመስል እንደነበር ያብራሩታል። በመጨረሻ ሲወርድ ግን በኪሱ ምንም አይነት መሳሪያ እንዳልነበረው ተገልጿል።

ይህንን እስመልከቶ ደርግ የሚያስፈልገው ጥረት ተደርጐ ይህ ኰሎኔል በጃችን መግባት አለበት በማለት በደርግ አባል ሌተናት ኰሎኔል ተከ ቱሉ የሚመራ ቡድን ወደ ጅቡቲ በመሄድ የኰሎኔሉን ወንጀል ማስረዳት ጀመረ። ይኸውም ወንጀል ፩ አውሮፕላን በመጥለፍ ፪ የሠራዊቱን ደመወዝ በመውሰዱ፤ ፫ በአዲስ አበባ ውስጥ የጠለፋና የዘረፋ ወንጀል ሲፈጽም ስለተደረሰበት ፬ በዚሁ ወቅት የሰላማዊ ሰው ህይወት በማጥፋት፤ የሚሉ ነጥቦች ነበሩ። በጅቡቲ የፈረንሳዩ ወኪልም ያቀረበው ጥያቄ





ይህንን ሁሉ ወንጀል ሲፈጽም ለምን አልተያዘም ነበር። ተረክቤአለሁ የሚለውንም ገንዘብ ከሞዴል 6 ጋር አስረክቧል። ስለዚህ የተጧበጠ ክስ ስላልሆነ አውሮፕላን በመጥለፍ ብቻ በፈረንሳይ ሕግ ይቀጣል። አውሮፕላናችሁና ፓይለቶቻችሁን በጠየቃችሁን መሠረት ወዲያውኑ ለቀናል። በማለት መልስ ወዲያውኑ ተሰጣቸው።

ደርግ በዚህ ብቻ አላበቃም ጉዳዩን ወደ ኢንተርፖል አስተላልፎ ክሱን በፈረንሳይ መንግሥት ላይ ደረደረ። ኢንተርፖልም ደርግ ያቀረበውን ሠነድና በአራት ነጥቦች ዘርዝሮ ያቀረበውን ክስ ከመረመረ በኋላ ከፈረንሳዮች ጋር ተመሳሳይ መልስ ሲሰጥ ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ወንጀል ያልሠራ ሁሉ እየተያዘ እርምጃ የሚወሰድበት ወቅት ሲሆን ይህ ኰሎኔል ቀደም ብሎ ወንጀል መሥራቱን ከጠረጠራችሁት ለምን ይህን ያህል ዕድል ሰጣችሁት በሚል ክሱን ውድቅ ስላደረገበት ኰሎኔል ወደ ፈረንሳይ አገር ቤት ፓሪስ ተዘዋውሮ አንድ ዓመት ከተፈረደበት በኋላ መፈታቱ ተረጋግጧል።

## የሽብር ፈጣሪው ቡድን እበ ሉች በመርሐ ቤቴ

ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ ከመርሐ ቤቴ የተላለፈመው ተ ሐ ፖራም እንዲህ ይላል « በቀለ ሰዮምና እምሰት እባርቹ በሳንድርሽር መኪና ዓለም ከተማ ከመጡ በኋላ በድንገት የገዘቱን ጽሕፈት ቤትና የፖሊስ ጣቢያውን በመያዝ ራሳቸውን የደርግ አባል በማድረግ ለቁጥጥር እንደመጡ አስረድተዋል። ጉዳዩ ችግር ስለፈጠረብን ሁኔታው ይገለጽልን፤ » ይላል። ደርግም እነዚህን ሰዎች እራሳቸውን ከማጋለጣቸው በፊት ያልተደረሰባቸው ስለነበር ቢቻል እጃቸውን እንዲሰጡ ባይቻል ግን እንዲደመሰሱ የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈ። በዚህ ምክንያት እጃቸውን ለመስጠት ባይሆኑ ቀርተው እራሳቸው ተኩሱን ስለጀመሩት ዙሪያውን ተከበው ሲደመሰሱ አንድ የክብር ዘበኛ ጡረተኛ ከነህይወቱ ተያዘና የሃምሳ አለቃውን የሚያመጣ ሄሊኮፕተር ተልኮ ይጠቀሙበት የነበረው የጦር መሣሪያና ትጥቅ ከሃምሳ አለቃው ጋር አዲስ አበባ ገባ።

ሃምሳ አለቃው ከተያዘ በኋላ ተደፍኖ የቆየው ዘረፋና ግድያ እንዲሁም ብዙ ጉዳዮችን ለማወቅ በሩ ተበረገደ። ሃምሳ አለቃው ወደ ልዮ ምርመራ ዘንድ ስለነበረ የታጠፈ እንጀቱንና የተሰበረ ምላሱን እንዲፍታታ ምግብና ውሀ እንዲቀርብለት አደረግሁ። ዕድሜው በግምት ስድሳ ውስጥ ይሆናል። ምንድን ነው ጉዳዮ ብዩ ስጠይቀው የተሠራውን ሁሉ አንድ ባንድ ዘረዘረ። እኔ የምጠይቀው በምርመራ የሚመዘገብ ሳይሆን ጉዳዮ ምን እንደነበር ለመረዳት ብቻ ነበር። ስለዚህ

፩ አዲስ አበባ ከተማ ሲዘረፍና የሰው ሕይወት መጥፋቱን የሚያውቅ መሆኑንና በቅድሚያ አውርጦሳን ጠለፈ የተባለው ሰው ለዚህ ሁኔታ ዋና መሆኑን

፪ መርሐ ቤቴ የተገደሉት እነበቀለ ሥዮም ከኩለኔሉ ጋር አብረው ይሠሩ እንደነበር፤

፫ ሌፍተናንት ኩለ ኔል ንጉሤ የደርጉ የመረጃ ሹም የነበረመውና የሱ ምክትል ሽንበል ደባስ ተይዘው የተገደሉት ይህ ቡድን በዘጋጀው የሀሰት መፈንቅለ ደርግ የውሸት መረጃ መሆኑን፤

፬ ወደውጭ እየሸለኩ ያመለጡ አንዳንድ ሰዎች ከዚህ ቡድን ጋር ግንኙነት እንዳላቸው

፭ ዘረፋው የሚፈጸመው ለውጡን ለመቀልበስ የሚረዳ ገንዘብ ለመሰብሰብ ተብሎ መሆኑን

፮ የመለዮ ለባሹን እለባበስ የምንጠቀምበት ህዝቡ ወታደሩን ስለሚፈራ ሳያስቸግር ንብረቱን እንዲሰጥና በተለይም ደርግን በዘረፋ ወንጀል ለመወንጀል እንዲያመች መሆኑን ከገለጸ በኋላ አብረውት የተያዙት ወታደራዊ ትጥቆች ጋር ፎቶግራፍና ቴሌቪዥን ተነስቶ ወደልዮ ምርመራ ተልኮ ከዚያ በኋላ የታወቀ ነገር የለም።

ሽንበል ደባስ ከኔ ጋር ቅርብ ጓደኛ ከመሆኑም በላይ በየቀኑ ሳንገናኝ ያሳለፍናቸው ቀኖች አይገኙም። ሽንበል ደባስ በጣም ታማኝና ቀን የሆነ መኮንን ሲሆን በተለይ የመንግሥቱ ኃይለማርያምና የአጥናፉ አባተ ቢሮዎችና የሚገለገሉባቸው ሁሉ የሚፈተሸው በዚሁ መኮንን አማካይኝት ነው። ሽንበል ደባስ ከታሠረ በኋላ የታሰረበትን





ምክንያት ያልተሟላ ወሬ ብሰማም ለማመን አልቻልኩም። የሻለቃ ዮሐንስ የደርጉ የምርመራ ሹም አማካኝነት ደባስ ወደ ታሰረበት ሦስተኛ ልዮ ምርመራ ሐጂ ለማጣራት ብሞክርም አብሯቸው የታሰሩት ብዙ ሰዎች ስለነበሩ ሳይመቹኝ ተመለስኩ።

ከላይ የተጠቀሰው የ፶ አለቃ ከተያዘ በኋላ ግን ከፍሳ ጉቲ የጠቀሰልኝ ነገር ቢኖር የሻንበል ደባስን ጉዳይ ነው። ጉዳዮ እንደዚህ ነው። ቀደም ብሎ በሰላሙ ጊዜ ይህ ሃምሳ አለቃ ከዚህ አደገኛ ቡድን በተቀነባበረ ሴራ የተዘጋጀ ደርግ እንዴት እንደሚደመሰስ የሚገልጽ ንድፍና ጠቅላላ ሪፖርት ተሸክሞ ወደ ሻንበል ደባስ ይሄዳል። ከዚያም ያገኘሁት መረጃ ነው ብሎ ለሻምበል ይሰጠዋል። ደባስም ለጊዜው ለ፶ አለቃው ገንዘብ ይሰጥና በይበልጥ ተከታተል ብሎ ከመለሰው በኋላ ይህን ወረቀት ይዞ ከአለቃው ሌፍተናንት ኩሉኔል ንጉሤ ወስዶ ያስረዳውና ክትትል እንዲደረግ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ወረቀቱን ሻንበል ደባስ መኪና ውስጥ አስቀምጦ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ለሥራ ሲዘዋወር ሌፍተናንት ኩለኔል ንጉሤ በሌላ ጉዳይ ተጠርቶ ተይዞ እንዲታሰር ተደረገ። ቀጥሎም ለዚሁ የተመደቡ መርማሪዎች የሻንበል ደባስን መኪና መፈተሽ ጀመሩ። በዚያን ጊዜ ያስቀመጠው ወረቀት በጃቸው ስለወደቀ ወዲያውኑ አግድፈውና አንጓልተው ወደ እስር ቤት በማስገባት ጭካኔ በተሞላበት እኪኹን ታሰረ።

ሌ/ ኮ ንጉሤ የተባለው የደርጉ የመረጃ ሹም ሲሆን ሊታሰር የቻለው ከህዝብ የሚሰበሰበውን ንብረት በራሱ ፈቃድ ለባለንብረቶች መልሷል በሚልና ከአንዳንድ ሴተወይዘዝሮች ጋር የግል ግንኙነት አድርጓል ተብሎ በመወንጀሉ ነው። ከዚህም ሌላ ቢትወደድ አሊ ሚራህ የአፋር ባላባት ጋር ግንኙነት እንዳለውና በመሀከላቸውም ልዩ ጥቅም አለ ተብሎ ስለተጠረጠረ ከታሰረ በኋላ ተገደለ እንጂ የፖለቲካ ግንኙነት አልነበረውም።

የሌ/ ኮ ንጉሤ ምክትል የሆነው ሻምበል ደባስ ግን በማያውቀው ሁኔታ በሀሰት ተወንጅሎ ከመታሰሩም ሌላ ችግሩን ለማብራራት ዕድል እንዲሰጠው ጠይቶ ከተከለከለ በኋላ ተገድሏል።

ሻምበል ደባስ ለሌ/ ኮ መንግሥቱም ሆነ ለሌ/ ኮ አጥናፉ ጋር የነበረው የቅርብ ወዳጅነት ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ከፍርድ ፊት ቀርቦ ሀሳቡን ተንፍሶ እንዲሞት አልፈቀዱለትም። የኔና የሻምበል ደባስ ግንኙነት በሰው ጡ ምክንያት ሳይሆን ከዚያ በፊት ለረጅም ጊዜ የምንተዋወቅ በመሆናችን እጁ እስኪተያዝ ድረስ አልተለያየንም። ለኔም ብዙ ነገሮችን ለማወቅ ረድቶኛል።

ለሻምበል ደባስና ሌሎች አብረውት ተወንጅለው ለተገደሉት ሁሉ ተጠያቂውና ምክንያት የሆነው ይኸው የሽብር ፈጣሪ ቡድን መሆኑን የሽብር ፈጣሪው አባል የ፶ አለቃ ዘርዝሮ አስረድቷል።

## የራዛ ዘመቻ

በራዛ ሴሚናር ላይ በተገለፀው መሰረት ራዛ ማለት በትግረኛ አነጋገር የሚውጥ እሞራ ማለት ነው። ይህንን ስም ያፈለቀው በደርጉ የዘመቻ መምሪያ የሚገኝ አንድ የጦር ሠራዊት ባልደረባ ነው ተብሏል።

የዚህ ዕቅድ መነሻውና ግቡ በኤርትራ ክፍለሀገር የሚያውኩትን ቅጥረኛ ወንበዴዎች መደምሰስ ነው ይላል። በፐሮግራሙ ላይ ሦስት አይነት ዕቅዶች አሉት።

፩ በኤርትራ ካርታ ላይ በተጠቆሙት አንዳንድ ቦታዎች ላይ በተመለከተው <u>የቀይ ቀለም</u> የተቀባውን በመመልከት በሰውም ሆነ በንብረት እንዲሁም በከብት ላይ የመጨረሻ ርምጃ በመውሰድ መደምሰስ።

፪ ቢጫ ቀለም በተመለከተው የካርታ ክልል ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ከመንግሥት ጋር ያለ መስሉ በጉን ግን ለወንበዴዎቹ የሚረዳ ስለሆነ በጥንቃቄ እየታዩ እስፈላጊው እርምጃ የሚወሰድባቸው።

፫ አረንጓዴ ቀለም የተቀባው የካርታ ላይ የተመለከተው አውራጃና ወረዳ ፍጹም የመንግሥት አማኞች ስለሆኑ በማንኛውም ረገድ እንዲረዱና መንግሥትም ለነሱ እንደሚያስብ ማስረዳት ናቸው።

ለዚህ ዕቅድ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ ጦር ቢኖርም በተለይ ከአራቱ ክፍለ ሀገራት ጐጃም፣ ጐንደር፣ ወሎ፣ ትግራይ፣ ከሚገኘው ህዝብ በማውጣጣት ለማሰለፍ መቻል ነው።

ለዚህ ጦር የተዘጋጀ የጦር መሣሪያ ቢኖርም በልዮ ልዮ ምክኒያት የተሰበሰቡ የጥንት የጦር መሣሪያዎች ከመንግሥት፣ መሣሪያ ግምጃ ቤቶች ተለቅመው እንዲዘጋጁና ህዝቡ በተመደበበት ወረዳ ከደረሰ በኋላ እንዲታደል ሲሆን የመሣሪያዎቹ አይነት

አልቢን፣ ዲሞትፈር፣ ወጨፎ፣ ምንሽር፣ መውዜር (ቤልጅግ)፣ ለበን፣ የውሀ መትረየስ ተብለው የሚጠሩ አርጌ ጠብመንጃና መትረየሶች ተዘርዝረዋል።

የጠላት የጦር መሣሪያ ክላሽን አውቶማቲክ ጠመንጃ፣ ኤፍኤን፣ ኤምዋን፣ እና አያሌ ቁጥር ያላቸው ዘመናዊ መሣሪያ ናቸው። የሚል ግምገማ ነበር።

የዚህ ማብራሪያና ዝርዝር ሁኔታዎች ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል። ደርግ ስልጣን ላይ ከወጣበት መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ ም ጀምሮ በኤርትራ ይካሄድ የነበረው ጦርነት መልኩን እየለወጠ ችግሩ እየጠነከረ በመሄዱ እንደዚሁም ከኤርትራ ወደ መሐል አገር ይደረግ የነበረው የሽምቅ አደጋ በአንዳንድ ሰዎችና ድርጅቶች ላይ ጉዳት በመድረሱ ደርግን ከፋኛ አደናግጦት ነበር። ህዝቡን አሰባስቦ ወደ ውጊያ ቦታ ለመላክ ደግሞ በተለይም በጐጃም፣ በጐንደር፣ በትግራይና በወሎ ክፍለሀገር የነበረው የመሬት ስሪት የደርግን የመሬት አዋጅ አጥብቆ የሚቃረን በመሆኑ የህዝቡን እስተሳሰብና ቅጣ ለመለወጥና ጋብ ለማድረግ ህዝቡን ወደውጊያ መላክ አስፈላጊ ነው ብሎ ደርግ ወሰነ።በዚህም ምክንያት ያለ በቂ መሳሪያ እንዲሁም ያለጥይት ከአስራ ሦስት አመታት በላይ የሽምቅ ውጊያ ልምድ ካለው ከኤርትራ ድርጅት ጋር እንዲዋጋ በማያውቀው በረሀ፣ ደገትና ቁልቁለት፣ በግር እንዲጓዝ በማድረግ በህዝቡ ላይ ጉዳት አደረሰ። የ«ራዛ» ሰውር ግብ ግን ከሁሉም አቅጣጫ ለመብቱ የሚከራከረውን ለምን ብሎ የሚጠይቀውንና የደርግን ጭካኔ የማይቀበለውን በታሪክ ለአገሩና ለክብሩ ሲታገል የኖረውን ሕዝብ ለማኮሰሸትና ለመጨረስ ብሎም ለማስደንገጥ ነበር።

ለዚህ ዘመቻ ይሰለፋል ተብሎ የተገመተው ህዝብ ብዛት በአጠቃላይ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ይሆና ተብሎ ነበር።

ህዝቡ በዚህ ዝግጅት ውስጥ ከመግባቱ በፊት ይህን ዘመቻ የሚያስፈጽሙ ከ40 የማይበልጡ መኰንኖችና ወታደሮች ከመለዮ ለባሹ ልዮ ልዮ ክፍል ተመረጡ። ከመከላከያ ሚንስተር ትጥር ግቢ ውስጥ ለስምንት ቀን ሴሚናር በተሰጠበት ወቅት የኤርትራ አስተዳዳሪና የጦር ጠቅላይ አዛዥ ብ/ ጀኔራል ጌታቸው ናደው የምድር ጦር የዘመቻ መኰንን ኰሎኔል ደምሴ ቡልቱ ይገኙበታል።

ከሴሚናሩ ፍጻሜ በኋላ ለዚሁ ጦር የሚታደለውን ከየክፍሉ የተሰበሰበ ያረጀ ሚንሽርና አልቢን ባሩድ ቤት በሚባለው ጎፍ ሰፈር የመሣሪያ መጋዘን ውስጥ ጉብኝት ተደረገ። ካስ ጉብኝዎች ውስጥ የመሳሪያ ጠጋኝ የሆነው የሊ/ ኰ መንግሥቱ ኃለማያም እባት ባሻ ኃይለማርያም ይገኙበታል። ከጎብኝዎች ውስጥ የሸለቃ ማዕረግ የነበረው መኰንን ስለተሰበሰበው የጦር መሳሪያ ጥቅም ለባሻ ኃይለማርያ ጥያቄ አቅርበለት ነበር። ባሻ ኃይለማርያም ግን የምትለው ይገባኛል ስለመሳሪያ እናንተን ማስተማር አልችልም። ግን ዘመናዊ መሳሪያ ለታጠቀ ጠላት ይህ መሳሪያ አይጠቅምም፤ ብሎ ወደ ስራው ቦታ ገባ። በዚህ ቦታ ለሦስት ቀናት ያህል ተመለልሰን የዚህን አርጌ መሳሪያ የመፍታትና የመግጠም ትምህርት ተሰጥቶናል። የሚደረገው ስራ ሁሉ በመኰንኖች ማሳገጥና ጊዜን ማባከን ስለነበር ሴሚናሩን በትዕግስት አሳለፍነው። በዚህ አይነት ሁኔታ ነገሩ ከተጠናቀቀ በኋላ ከዚህ በታች የተመለከተው የራዛ የንቅናቄ መልዕክት ወጥቶ ለሁላችንም ታደለ።

## የራዛ የንቅናቄ ትዕዛዝ

በወሎና በትግራይ በኩል የተሠማሩ አዝማቾች፤ በጐጃምና በጐንደር በኩል የተመደቡ መኰንኖችና ወታደሮች በየተመደበበት ክፍለ ሀገር ከሚያዝያ መጨረሻ እስከ ግንቦት መጀመሪያ 1968 ዓ ም ድረስ እንዲንቀሳቀሱ ትዕዛዝ ወጣ። በየክፍለ ሀገሩ

የተመደቡት ብዛት ያለውን የገበሬ ጦር እደመሩ የተመደቡት የመሰዮ ለበሽ ቀጥር አነስተኛ ነበሩ ከዚህም ሌላ መኩንኖቹ ከግል ሽጉጣቸው በስተቀር ከመንግሥት መሰሪያ ማግኘት አልተቻለም። ምክንያት የነበረውም በቂ መሰሪያ ስላልነበር ነው።

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ተካፋይ ሆኘ በሁመራ በኩል ተመድቢ ነበር። የታጠቅሁትም ዑዚ መትረየስና 38 ከሊቨር ከልት ሽጉጥ ከደበኛው ክፍሌ ይዥው የሄድኩት ሲሆን ሽጉጡ የግሌ ነበር።

በጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ ከሁመራ ሌሳ ወልቃይትና ጠገዴ፣ ብርኩታና ከተከዜ ወንዝ አጠገብ በደምሩ በሦስት ግቢያዎች የተነግጠለ ነበር።

የጎጃም ክፍለ ሀገር ዘማችን ደግሞ በጎንደር በኩል አልፈው በአዲአርቃይ፣ በማይ ፀብሪና በእምባ ማድሬ አካባቢ ተከዜ ወንዝ አጠገብ ሠፍረው ነበር።

በዚሁ እቅድ መሰረት ከግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ ም ጀምሮ የጎጃምና የጎንደር አስተዳዳሪዎች የየአውራጃውን አስተዳዳሪዎች በማስከተል በወረዳዎችና በየቀበሌው በመዘዋወር ሕዝቡን በመቀስቀስ ለዘመቻ እንዲዘጋጁ ከደርግ የወጣውን ዕቅድ በተግባር ለመተርጎም መሯሯጥ ጀመሩ።በዚህም ዝግጅት ላይ የጎጃምና የጎንደር አስተዳደሪዎች የተለያየ አሠራር ነበራቸው።

በጎንደር ውስጥ የተሞከረው ቅስቀሳ ከጎንደር ዙሪያ በስተቀር በሌላው አውራጃዎች ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አልነበረም። ምክንያቱም አብዛኛው የጎንደር ህዝብ በለውጡ የተደሰተ ባለመሆኑ በየገጠሩ አፈንግጦ ከመንግሥት ጦር ጋር በመዋጋት ላይ ስለነበር ግማሹ ለመንግሥት አይታዘዝም ነበር። ስለዚህ አስተዳዳሪዎች ከፍተኛ ችግር ነበረባቸው። እንዲያውም የክፍለሀገሩ አስተዳዳሪ አቶ በዛብህ ጉበሬ የተባለው በሕዝብ ተጨፍጭፎ ተገድሏል።

የጎንደር ዙሪያ አውራጃ አስተዳዳሪወች በስራሩ ያልተደሰቱ በመሆናቸው ወደታሰበው የመሰብሰቢያ ወረዳ ለመሔድ የተዘጋጀው ህዝብ ሦስት መቶ ያህል ነበሩ። ለዚሁም አዝማሪው ከመጠጥ ቤት ተጎትቶ ከነማሲንቆው ሲስትርው ከሥራ ላይ ታፍኖ በየቤተክርስትያኑ ድኩማንና ምዕመናን እንዲሁም ሥራ ፈቱ እጅ እግሩ የተቆረጠው አይኑ የታወረ ሁሉ ነበር እንዲዘምት የተገደደው። 75.000 እንዲደርስ ነበር። ይኸ ቀርቶ ከ300 ያለነሰ ሰው ብቻ ነበር የተሳከው።

በዚሁ መሰረት አርባ ከባድ የጭነት መኪና ይህንኑ ይዞ ሁሉንም በየተመደበበት በታ ሲሔድ ሌላው የገበሬ ጦር እዚያው ድረስ ይሰከል ተብሎ በተስፋ ጉዞ ሆነ። ሰው የጦር መሣሪያ ስላልነበረው በመንገድ ላይ አርስ አደሩ እናባልፍም በማለት እየተከሰ አስቸግርን ነበር። ከነዚህ ውስጥ ሁመራ ኳሪ ሆኑች ነፍሰጡር መንገደኛ ከአገሬሬው ህዝብ በተተኮሰው ጥይት ተመትታ ሞታለች።

የጎጃም ዘማች ደግሞ በክፍለሀገሩ አስተዳደር የሚመራ ቡድን የአውራጃ





አስተዳደሪወችን በመያዝ ከግንቦት 1 ቀን 1968 ዓ ም ጀምሮ በየአውራጃውና በየወረዳው በመዘዋወር የዘመቻውን አላማ በማስረዳት ህዝቡ ጠመንጃውን እየያዘ እንዲሰበሰብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መሰብሰብ ጀመረ። ለተሰበሰበውም ህዝብ ስለራዛ ዘመቻ ሀቀን ሳይሆን በድብቅ የተደለተውን ቅጥፈት የተሞላበት ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሣ በማስጣት ሕዝቡ መዝመት እንዳለበትና ዋናው መሰብሰቢያ ባሕርዳር ሆኖ ግንቦት 11 ቀንና 12 1968 ዓ ም እንዲሰበሰብ ህዝቡን ለማጓጓዝ አውቶብሶችና የጭነት መኪናዎች ከግንቦት 6 ቀን 1968 ዓ ም ጀምሮ በየአውራጃው ከተሞች እንደሚላኩ መወሰኑ ተነገረ።

ለህዝቡ ከተነገሩት በተንኮል የተሸፈኑ አሳቦች ቃሰቶች ውስጥ የኤርትራ በአረብ ፔትሮ ዶላር የሰከሩ ጥቂት አፈንጋጮች ኤርትራን ለአረብ ለመሸጥ ውጊያ ከፍተውብናል።

እነዚህ በሀሽሽ እፅ የሰከሩ ጥቂት አፈንጋጮችን ለኢትዮጵያ አንድነት ሲታገል ለታሪክና ለትውልድ ሲያስተሳልፍ የኖረው የአራቱ ክፍለሀገር ህዝብ ዘምቶ እንደሚፅበል በማጥለቅለቅ ከነሽርጡ አንገት አንገቱን በመያዝ በአርብ አምስት ቀናት ውስጥ በድል አድራጊነት ወደመንደሩ ይመለሳል፣ የሚል ይገኝበታል። ይህ ስብከት በሁሉም በታ የተካሄደ ነው።

ህዝቡ አባባሉን ተቀብሎ መንግሥት አዝዟል የተባለውን ከሰማና ካጤነ በኋላ ወቅቱ የበልግና የክረምት ወራት መሆኑንና የተፈፋመ እርሻ ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልፆ ለመስከረም ወይም ለጥቅምት 1969 ዓ ም እንዲተሳለፍለት በመጠየቅ አንድ ሰኔ የነቀለውን 12 ሰኔ አይመልሰውም በሚል ግልጽና የማያሻማ ጥያቄ የሰነጠቅነውን መሬት እንድናሰብስው ይፈቀድልን ሲል በከፍተኛ ስሜት ልመናውን አቀረበ።

ይሁን እንጂ ምሰሹ አርቦ መብሳትም ሆነ መኖር የሚቻለው አገር ሲኖር ነው በሚል የለበጣ መልስ የደርጉ ጭፍን ትስዛዝ የግድ ተግባራዊ እንዲሆን ምርጫም ጥያቄም ሊኖር እንደማይችል በግልጽ ተነገረ። የየሀና ብልህ የሆነው የጎጃም ህዝብ በተሰባሰበበት በታ ሁሉ ሰንጋ ጥሉ ደግሰ አዘጋጅቶ ስንብቱን ከከናወኑ በኋላ ተጨማሪ ጥያቄ አቅርቦ ምለሽ በማጣቱ ለጉዞ ተዘጋጀ።

ይህን ጥያቄ ባቀረበበት ወቅት የተሰበሰበው ህዝብ በግምት ከ30,000 በላይ በለጠመንጃ ሲሆን ከ20 000 በላይ ደግሞ ጃሌ በድምሩ 50 000 ይደርስ እንደነበረ ተረጋግጧል።

ከግቦት 7ቀን 1968 ዓ ም ጀምሮ ተሽከርካሪወች ወደ ሁሉም አውራጃ ተንቀሳቅሰው በቃሳቸው መሠረት ዘማች ለመሰብሰብ ሲሞክሩ 5000 በሚኖርበት በታ ከ10 እና ከ15 ሰው ያልበለጠ እየያዙ ተሽከርካሪወች ወደ መሰብሰቢያ ግቢያው ወደባህርዳር መጓዝ ግዴታ ሆነ። ይህም ማለት ሕዝቡ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ዘመቻውን ለመካፈል ያለመፈለጉን በግልጽ አስታወቀ።

እስከ ግንቦት 10ቀን 1968 ዓ ም ከሞላው ጉጃም 2000 ሰው ብቻ ተሰበሰበ። በዚህ መሠረት የሁኔታው አለመሰከት ለደርግ በተገለጠበት ጊዜ ከገበያ ፣ ከመንገድና አስፈሳጊ ከሆነ ቦታ በማስገደድ እንዲሰበሰብ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት አፈሣ መካሔድ ጀመረ። በአፈሣውም ልክ ጉንደር ክፍለሀገር በተፈፀመው መሠረት አካለ ጉደ ሉወችና ለዘመቻ ቀርቶ በዚህ ዓለም ለመኖር ያቃታቸው በሽተኞች ነበሩ የታፈሱት።

ለመሰብሰቢያው ቦታ የባህርዳር ቤተመንግሥት ተመርጦ ስለነበረ በዚያ ይታይ የነበረው ህሊናን የሚዘገንን መፈጠርን የሚያስጠላ ትዕይንት ታይቷል።

በዚሁ መሠረት አዝማች መኰንኖች በሽተኛውን ከለዮ በኋላ ከተገመተው 35000 ሰው ውስጥ 4000 ብቻ ይዘው በ80 መኪና በጉንደር በኩል ወደ ትግራይ ጉዞ ተጀመረ።እነዚህ 4000 ሰወች ከጥቂቶቹ በስተቀር መሣሪያ ያልያዙ ነበሩ። በዚሁ መሰረት የጉንደር ከተማ ታልፎ ከደባርቅ በኋላ ሊማሊሞ ሲወርዱ ሁኔታው አደገኝነት የነበረውና በማንኛውም ጊዜ ጥቃት ሊሰነዘር እንደሚቻል ግምት ውስጥ በማስገበት የተጫነው አብዘኛው የማይሠራ መሣሪያ ለሕዝቡ እንዲታደልና የተመጠነ ትምህርት እዲሰጥ ለደርግ ጥያቄ ቀርቦ እሸፈረኝ አለ።

ይህ ከታወቀ በኋላ ጉዞው ቀጥ ሎ አዳርቃይ ሲደርስ በዚህ ሁኔታ መቀጠል እንደማይቻል በመገንዘብ የመጣው ይምጣ በማለት አመራሩን የያዙት መኰንኖች መሣሪያውን ለሕዝቡ በማደልና 30 ጥይት በመስጠት በአደርቃይ አከባቢ ትምህርት መስጠት ተጀመረ። ትምህርት ስለመሣሪያ አጠቃቀም ማለምና ማነጣጠር የነፍስ ወከፍ መጠነኛ ስልትና መሣሪያ ማስተኰስ ብቻ ነበር። ጊዜው አጭር በመሆኑ በዕቅዱ መሰረት ትምህርት ሳይሰጥ ጉዞ ወደ ማይፀምሪከተደረሰ በኋላ በመሰሪያው ልምምድ ላይ የተሰጠው ጥይት አፈርና ጉመንዘር የተሞሉ ሆኖ ተገኘ። ከሰሰሰው ጥይት ውስጥ ሁለቱብቻ ደንበኛ ጥይት ሆኖ ይገኝ ጀመር።

ደርጉ ይህንን ቢያውቅም እንዲያልቅ የተፈረደበት ህዝብ ስለነበረ ሪፖርት ሲቀርብለት አላሰደነገጠውም። ይህን ሁኔታ ሕዝቡ ከተመለከተ በኋላ ያለ ማቋረጥ ልዮ ልዮ ተቃውሞ ቢያሰማም ደርግ ስህተቱን ሳያርም ጉዞውን እንዲቀጥል ማስገደዱን ቀጥ ሎ ነበር።

ይሁንና ህዝቡ እንቢ በማለቱ ባለበት ቦታ እንዲቆይ ደርግ ትዕዛዝ ባይሰጥም ግዴታ ህዝቡ ባለበት ቦታ ሆኖ ተለዋጭ ትዕዛዝ መጠባበቅ አልቀረም። በተጨማሪ ለሕዝቡ ስንቅ ይሆናል ተብ ሎ የተጫነው ድርቆሽ ከ ኰብ ጋር የተቀላቀለ ስለነበረ የጠራ የጤፍ እንጀራና የደሮ አይን የመሰለ ጠላ ተጠቃሚ የነበረው የጉጃም ህዝብ ከፍተኛ ችግር ላይ ወደቀ በረሀብም መሞቱ ተከሰተ። በዚህም የተነሣ በወባና በተቅማጥ የሚሰቃየውና የሚሞተው ህዝብ ቀላል አልነበረም።

በዚህ ሁኔታ አንድ ወር ካለፈ በኋላ በሌላ አቅጣጫ ማለት በትግራይ ግንባር





በኩል የወ ሉ ዘማች ህዝብ ላይ በኤርትራ ድርጅቶች አማካይነት ጥቃት ተሰንዝሮባቸው ከፍተኛ ጉዳት በመድረሱና በተሰበሰበውም ህዝብ የተማረከው ተማርኰ የተረፈው ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ በመበታተኑ በዚህ ሳቢያ ዘመቻው ከሸፈ።

ይህ ምክንያት ሆኖ የጉጃም ህዝብ ወደ አገሩ እንዲመለስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ደባርቅ ተጓዘ የሌ/ኰ አጥናፉ አባተን ስንብት እንዲጠባበቅ ተደርጉ ሌ/ኰ አጥናፉ እስኪመጣ ድረስ በወባ የተ ጉዳው ህዝብ የደባርቅን ብርድ መቋቋም ስለአቃተው በሁለት ቀን ውስጥ ከሀያ በላይ ቁጥር ያለው ህዝብ ስለሞተ በቀጥታ ጉዞ ወደ ጉጃም ሆነና የጉጃም ህዝብ የራዘን ዘመቻ በዚህ አይነት ፈፀመ።

በሁመራና በወልቃይት ጠገዴ የነበረው ሁኔታ እንዲህ ነበር። ከመጀመሪያው እንደተገለፀው በዚህ አቅጣጫ የተሳከው ህዝብ ከጉንደር ዙሪያ በመሆኑ ከሦስት መቶ ያልበለጠ ህዝብ ለሰስት ጣቢያወች ተከፋፈለ። ነገር ግን እስከ አስር ቀን ውስጥ በተደረገው ሙከራ አስተዳዳሪወች ህዝቡን እንደተፈለገው ለማዘዝ ባለመቻላቸው የሰበሰቡትና የሳኩት ህዝብ ቁጥር በአጠቃላይ ከ800 በላይ አልነበረም።

በጣም የሚገርመው ደግሞ የሁመራ ነጋዴና ገበሬ በሁመራ የሚካሄደው የእርሻ ሥራ በሚያገኘው ምርት በገንዘብ አፍንጫው ድረስ የተሞላ በመሆኑ እንኳንስ የደርግን ትዕዛዝ መቀበሉ ቀርቶ በአገሪቱ ውስጥ ለውጥ መካሄዱን በሚገባ አጢኖ የተመለከተው አይመስልም ነበር።

በዚህ ምክንያት የራዛ ዘመቻ ጥያቄ ሁለተኛ እንዳይነሳ በማለት ህዝቡ አስተዳዳሪዎችን አስጠነቀቀ። ህዝቡ የታጠቀው አውቶማቲክና ዘመናዊ መሰሪያ በመሆኑ በግድ ማዘዙ ቀርቶ እንዲያውም የዘመቻውን መንፈስ ያበላሽብናል በማለት ከፍተኛ ስጋት አስከትሏል።

በግድ ከየአውራጃው የተሳከው ህዝብ በቁጥሩ አነስተኛ ቢሆንም እራሱን እንዲጠብቅበትና ለዘመቻም እንዲዘጋጅ የጦር መሣሪያ እደላ ተደረገ። ህዝቡ መሣሪያውን ከተቀበለ በኋላ መሣሪያውን እየያዘ ወደ አገሩ መመለስ ስለቀጠለ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሆነ። ደርግም ይህን ሁኔታ ሪፖርት ሲደረግለት ይህ የሌረኞች ሪፖርት ነው አለና ሪፖርታችንን ውድቅ አደረገው።

ያም ሆነ ይህ ከላይ እንደተገለፀው በወ ሉና በትግራይ ህዝብ ላይ በኤርትራ ድርጅቶች አማካይነት ጉዳት ከደረሰ በኋላ በተመሳሳይ በዚህም ክፍል እንዳይደርስ ዘመቻው መታገዱንና ነገር ግን ሌ/ ኰ አጥናፉ አባተ በቦታው ተገኝቶ ብንዲራ በመስጠት ህዝቡን እንደሚያሰናብት በተላለፈው ቴሌግራም ተገለፀልን።

የሁመራ ሀብታም ህዝብ ይህን ዜና በመስማቱ በሰልፍ ላይ ተገኝቶ የሌ/ ኰ አጥናፉን ንግግር ለማዳመጥ ፈቃደኛ በመሆን በአቀባበሉ ሰልፍ ላይ ከሦስት ሽህ በላይ ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀ ህዝብ ታ ዮ።

በፕሮግራሙ መሠረት ሌ/ ኰ አጥናፉ አባተ ሌ/ ኰ አሥራት ደስታ የደርግ አባል ሸለቃ አዲስ ተድላ የደርግ አባል ሆነው ከጠዋቱ አራት ሰአት ላይ በአውሮፕላን እንደደረሱ በራዛ የጦር አዛዦች አማካይነት አቀባበል ተደረገላቸው።

ሌ/ ኰ አጥናፉም የፕሮግራሙ መጀመርና የቆመበትንም ምክንያት ለህዝቡ በመግለጽ የአርበኞች ባንዲራ ነው ተብሎ ለህዝቡ ተወካይ ቀኛዝማች ገብረሀይወት ለተባሉ ሰው አጥናፉ አስረከበ። በባዓሉ ወቅትም ሁለት ኤፍ 5 የተባሉ የጦር አውሮፕላኖች በመብረር በዓሉን ለማድመቅ ሞከሩ። በዚህ ጊዜ ሌ/ኰ አስራት እየተዘዋወር የህዝቡን ድምጽ በቴፕ ሲቀዳ ሻለቃ ሀዲስ ደግሞ ፎቶግራፍ ያነሳ ነበር። ይህ ከተከናወነ በኋላ በደስታ ምክንያት በአንዲት መጠጥ ነጋዴ ቤት እራቧ በተከሰቸው አውቶማቲክ ጠመንጃ ምክንያት ሁሉም ህዝብ በየአቅጣጫው ተኩስ ስለከፈተ የደርግ አባሎቹ በመደናገጥ እየሮጡ አውሮፕላን ውስጥ በመግባት ወደመጡበት ሲመለሱ የራዛ የብዙ ጊዜ ፕሮግራምና ብዙ ገንዘብ የባከነበት ዕቅድ ምንም ፋይዳ ሣይሠራ በዚህ ስነስርዓት ብቻ አከተመ። በዚህ የዘመቻ ዕቅድ ብዙ ሚሊዮን ብር የምንሽርና የአልቢን ጥይት መግዣ ተብሎ ወደማሲያን አገር የተላከ የአገሪቷ አንጡራ ሀብት በደርግ አባሎችና በሌሎች ግለሰቦች እጅ ባክኖ ወደ መንግሥት ካዝና ሳይመለስ ቀርቷል።

በጐንደር በኩል በወልቃይት ጠገዴ በሠፈረው ጦር ላይ በወባ ምክንያት ቁጥሩ ያልታወቀ ሰው ሞቷል። በማይፀብሪ የዘመተው የጐጃም ህዝብ ግን ከላይ እንደተገለጸው ከሀያ በላይ ሞተዋል።

የወሎና የትግራይ ጦር ግን በቦታው ስላልነበኩ ጉዳቱን አላውቅም። ነገር ግን በኢፒሌፍ እና በኢሌፍ እጅ በብዙ ሽህ የሚቆጠር ህዝብ እንደተማረከና በውጊያውም ጊዜ ብዙ ሰዎች እንደሞቱ ተረድተናል። ቆይቶ የተማረከውን ህዝብ ደርግ እንዲረከብ ቢጠየቅ አላውቅም በማለቱ በሁለቱም ድርጅቶች በኩል የተማረኩት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ማድረጋቸውን ተረድተናል።





## የነበልባል ጦር

የዚህን ጦር አቋምና ታሪክ ለመግለጽ ያስፈለገበት ምክንያት ከሌላው የጦር ክፍል የተለየ አላማ ስለነበረው ነው።

፩ኛ እንደሁኑ የኢትዮጵያ ጦር የተንዛዛ ሳይሆን በለውጡ መጀመሪያ ላይ የነበረው የቀድሞው ጦር በወታደራዊው ጥንካሬና ስልት የታነጸ ቢሆንም በቁጥር አነስተኛ በመሆኑ አዲስ ለበቀለው ቀራኒ ለበዛበት ደርግ ሥልጣኑን የሚያስጠብቅበትና ሕዝቡን የሚቆጣጠርበት ተጨማሪ ጦር ለማብዛት ከነበረው ምኞት በመነሳት የተቋቋመ ነበር።

፪ኛ ደርግ ሥልጣን የተረከበው ከብዙ የአገሪቱ ችግር ጋር በመሆኑ አጋጣሚ ሆኖ ለውጡ በተከሰተ ማግስት የኢትዮጵያ ጐረቤት የሆነችው ጅቡቲ ከፈረንሳይ ቀኝ አገዛዝ ስር ነፃ የምትወጣበት ጊዜ በመሆኑ የሱማሌ መንግሥት በጅቡቲ ላይ በነበረው አመለካከት ደርግ በወታደራዊ ሀይል ግልፅ ለመግባት ምኞት ስለነበረው የነበልባል ጦር በዘመናዊ የጦር መሳሪያና ስልት መደራጀት አለበት በማለት ከእስራኤል በመጡ አሰልጣኞች በአጭር ጊዜ ውስጥ ስልጠናው እንዲጀመር በመሆኑ በአዋሽ አርባ ስልጠናው ቀጠለ።

፫ኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመለዮ ለባሾች ውስጥ ተውጣጥተው ሥልጣን ለሕዝብ ለማስረከብ የመሸጋገሪያ ኮሚቴ በመሆን እራሳቸውን ደርግ ብለው ከሰየሙ በኋላ በሚወስዱት አንዳንድ የተሰባተ እርምጃ የነበሩበትና የመረጣቸው ጦር ሁሉም ሥልጣኑን ለሕዝብ አስረክበው ወደ ጦር ሠፈራቸው እንዲመለሱ ተጽዕኖ ስለነበረባቸውና ፍርሀታቸው እየጨመረ ስለመጣ ሁኔታውን ለመቋቋምና ጦሩን እንደየአስፈላጊነቱ ለመከፋፈልና ለመምታት ብሎም በክብር ዘበኛው ምትክ በክብር ዘበኛው መልክ ነበልባል ተቋቋሞ የደርጉ ዘብ እንዲሆኑ ከታሰበው ሌላው አማራጭ አንዱ ነው።

፬ኛ በኤርትራና በመሀል አገር ከመቸውም በበለጠ የፀጥታ መቃወስ እየጨመረ በመሄዱ ከሌላው ተግባሩ ውጭም እንደአስፈላጊነቱ ፀጥታ የማስከበር ተግባር ላይ ሊውል እንዲችል ታስቦ ነበር።

፭ኛ ለውጡን ምክንያት አድርጎ የሱማሊያ መንግሥት ከኢትዮጵያ መሬት ለመንጠቅ ከፍተኛ ዝግጅት እንደሚያደርግ ከመታወቁም አልፎ ጦርነት በመለስተኛ ደረጃ ስለጀመረ ይህ ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ ይህ የነበልባል ጦር ለዚሁ ተግባር እንዲውል በብዛት ለማሰልጠን ከእቅዱ ውስጥ አንዱ ነው።

ይህ ጦር ይመራ የነበረው ከምድር ጦርና ከመከላከያ ሚኒስተር ውጭ በቀጥታ

በደርጉ ሲሆን የነበልባል ጠቅላይ መምሪያ በሚል ልዩ ተቋም ነበረው።

የዚህ ክፍል የጦር መሪዎችና አሰልጣኞች ከመሰው መለዮ ለባሽ ክፍሎች የተውጣጡ ሲሆኑ በማዕረግ ከሌ/ ኰሎኔል እስከ ተራ ወታደር ይገኙበታል።

ለመጀመሪያ ጊዜ የእስራ ኤል የጦር አሰልጣኞች በአዋሽ አርባ በሚባለው የማሰልጠኛ ወረዳ ከአዲስ አበባ በመመላለስ ከሰለጠኑ በኋላ ደርጉ ከቻይናና ከሌሎች የኮሚኒስት አገሮች እርዳታ ማግኘት ሲጀምር በአስቸኳይና በፍጥነት ከበታው እንዲገለሉ በተወሰደው እርምጃ መሰረት እስራ ኤሎች እንዲወጡ ሆኑ።

ከእስራ ኤሎች ቀጥሎ ደርግ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቻይናዎች ጋር ግንኙነት በመጀመራቸው በሌ/ ኰ ጌታሁን ሀይሌ የሚመራ አሥራ ሁለት ምክትል መቶ አለቆች ከጦርና ከፖሊስ ሠራዊት የተውጣጡ የሚገኙበት መኰንኖች ይዞ ወደ ቻይና በመሄድ ለጥቂት ጊዜ የመሣሪያ መፍታት መገጠም ትምህርት ከተማሩ በኋላ ወደአገራቸው ሲመለሱ የከላሽን ጠመንጃና ቀላል መትረየስ ይዘው በመመለስ የነበልባል ጦር ለመጀመሪያ ጊዜ በተለየ አዲስ አቋም ነበልባል ታጠቀ። ቻይናዎችንም በብዛት ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ደርግ የማስተናገዱን ተግባር ቀጠለ። ነገር ግን ወደ ነበልባል ጦር መጥተው ያደረጉት ነገር አልነበረም።

ቀደም ብሎ እስራ ኤሎች በነበሩበት ጊዜ ይዘውት የመጡትን ኤፍ ኤን የሚባለውን ጠመንጃ በመታጠቅ የነበልባል ጦር የተሰጠው መሣሪያ መጥፎና ያረጀ በመሆኑ በሰልጠና ላይ ያለው ጦር ሲተኩሰው ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዘነ ስለነበር በመሰብሰብ ላይ እንዳለ ነበር ቻይና ክላሽን ከሸን ይዘው ከተፍ ያሉት።

ጦሩም አዲስ ባገኘው መሳሪያ በመሰልጠን ላይ እንዳለ ደርጉ አቅጣጫውን በመቀየር ከመስኮቦችና ከኪውባዎች ጋር ግንኙነቱን ከፈጸመ በኋላ እስራ ሌሎች በመጡበት አኳኋን ቻይናዎችም እንዲወጡ ስለተደረገ የጦር መሣሪያ ከቻይና መቅረቡ ቀርቶ ከመስኮብ መጉረፍ ጀመረ።

የእርዳታውና የሥልጠናው ጉዳይ እንደዚህ ሁኖ ሳለ በነበልባል የሚገኙ አሠልጣኝና አዛዥ መኰንኖች ደርግን በመቃወም የነበልባል ጦር መታዘዝ ያለበት በምድር ጦር መምሪያ እንጂ በደርግ መሆን የለበትም በማለት ትልቅ ተቃውሞ አቀረቡ።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሌላው የጦር ክፍል የዚህን ጦር ተግባር በመጠርጠር ሌላውን ተቃዋሚ የጦር ክፍል ለማስመታትና ለግል ሥልጣን መጠቀሚያ ሊያደርጓቸው ነው በማለት ተቃውሞው ቀጠለ። ደርጉም በመደናገጥ ሌ/ ኰሎኔል ተስፋየ ወልደ ኪዳን የመከላከያው ኃላፊ ሌ/ ኰሎኔል ተካ ቱሉ የደህንነት ኃላፊ ሌ/ ኰሎኔል ሥዩም መኮንን የደርጉ የጥበቃ ክፍል ሹም ሆነው በነበልባል ጦር ሠፈር ከተገኙ በኋላ በሰልፍ ላይ ያሉትን መኰንኖች በማዋረድ የተወሰኑ መኰንኖችንና ባለሌላ ማዕረጎችን መርጠው ወደ አዲስ አበባ በመውሰድ የት እንደደረሱ ሳይታወቅ ቀርቷል።





ይህን በመሳሰሉ ሁኔታዎች ቀራ ነው እየሰፋ በመሄዱና የሶማሊውም ጦርነት እየገፋና እየጠነከረ በመምጣቱ በኤርትራና በመሀል አገር ያለው ሁኔታም እያደገና እየከፋ በመሄዱ በእቅዱ መሠረት ሁኔታዎች ለማሟላት ባለመቻሉ በንደት፣ በቁጣና በቂም በመነሳት አሥሩን ሻለቃ ጦር ወደ ኤርትራ፣ ባሌ፣ ትግራይና ጎንደር በመከፋፈል አሠማሩት።

እንደገናም በተሻለ መንገድ የሰለጠነውን ሌላ አሥር ሻለቃ ጦር በጠቅላላው በሁለት ጊዜ ሰልጥኖ የወጣው 20 ሻለቃ ጦር በተለያዩ ጦርነቶች ተማግዶ ከማለቁ በስተቀር የተደከመበትና ጭቅጭቅም የመፍጠሩን ያህል ጊዜና ዕድሜ አግኝቶ ለሀገሩ የሰጠው ጥቅም አልነበረም።

ለዚህ ሠራዊት ይሆናሉ ተብለው የተመረጡት ከንግድና ከግብርና እንዲሁም ባላሰቡበት ሁኔታ ተገደው የተሰበሰቡ ሲሆን በዚህ ግዳጅ ላይ እንዲውሉ ሲደረግ ለቤተ ሰባቸውና ለልጆቻቸው የገለጹት ነገር ባለመኖሩ በጦርነት እስካለቁበት ጊዜ ድረስ ጥያቄ ከማቅረብ አልተቆጠቡም።

በተለይ መኰንኖችና የበታች ሹሞች እንዲሁም ነበር ወታደሮች ለዚህ ግዳጅ የተመረጡት በደርግ በኩል በጣም የሚፈሩና የሚጠሉ በመሆናቸው ከዚሁ ጦር ጋር ወደጦርነት በመጨመር እንዲያልቁ የተደረገ እቅድ እንደነበር በግልጽ የታወቀ ነበር። ሆኖም ደርጉ በተመኘው መሰረት በዚሁ ጦር ውስጥ የነበሩ መኰንኖችና የበታች ሹማምንት በሙሉ በጦርነት አልቀዋል።

## በደርጉ ውዥንብር የተፈፀሙ ስህተቶች

ደርጉ በስልጣን ላይ ቁጢጥ ካለ በኋላ ከየአቅጣጫው ብዙ ተቃውሞዎች ተከስተዋል።

የግፍና የጭካኔ ክንዱን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ የተጀመረውንና ከወጣትነቱ በመሆኑ በነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ውስጥ የተፈፀሙትን ያለፍርድ ግድያንና እፈናን ጥምር ለምሳሌ ያህል እንመልከት።

፩ኛ ጥቅምት 1967 ዓ ም ጦሩን ሊከፍሉ ነው በማለት የመብትና የዲሞክራሲ ጥያቄ በቀረቡ የጦሩ አባሎች ለአረመኔአዊ ቅጣት ተዳረጉ።

1 ፶ አለቃ መንግሥተዓብ ሀይሌ
2 ፲ አለቃ መኩነን ካሣ
3 ወታደር ማሰው ኃየለ ምክኤል
4 ወታደር ብርሀኑ መሀሪ
5 ወታደር ወልደ ሚካኤል ከበደ

የተባሉት ያለምንም ጥፋት መረሸናቸው ይታወቃል።

፪ኛ በህዳር 1966 ዓ ም ከቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር በጥይት የተጨፈጨፉ የሠራዊቱ አባሎች፤

1 ሻምበል በላይ ፀጋየ
2 ሻምበል ወልደ ዩሐንስ ዘርጋው
3 ሻምበል ደምሴ ሺፈራው
4 መቶአለቃ ተስፋየ ተከሌ
5 ምክትል ፲ አለቃ ተከሌ ሀይሌ
6 በቀለ ወልደ ጊዮርጊስ

የተባሉት ሲሆኑ ወንጀላቸውም «የደም መፋሰስ ለመፍጠር ጥረት እያደረጉ ነው።» የሚል ነበር። በእውነቱ ከሆነ ግን እነኝህ ሰዎች የጠየቁት ነገር ቢኖር በአስቸኳይ ስልጣኑን ለሕዝብ እናስረክብ እኛም ወደ ካምፖችን እንመለስ የሚል ነበር።

፫ኛ ሐምሌ 1968 ዓ ም በልነበሩበትና ባልሰሩት ወንጀል የተገደሉት እነዚህ ነበሩ፤

1 ዶክተር አበበ አሰፋ
2 አቶ ጌታቸው ዋለልኝ
3 ጁንየር ቴክንሽን አየለ አበዝን
4 አቶ በትረማርያም አሰፋ





5 አቶ ሽታው አበበ
6 አቶ ዘውዱ ተረፈ
7 አቶ መርስሔ ይሁን

እንግዲህ ከዚህና ካለፉት ሁኔታዎች የምንመለከተው ነገር ቢኖር ከጦር ኃሎች አልፎ ወደ ሲቪል፣ በፍርድ ሳይሆን በይሆልናል የሚደረገው የሰውን ልጅ መብት ማፈንና እንዲያውም መረሸን ለሰውና ለነበረው ትራኔ መፍትሄ እንሰጣለን ያሉትን ጥቂት ፋሽስቶች ጸባይ ነው። ወደ ሰዎች ሁኔታ ስንመለስ ዶክተር አበበ አሰፋ በሥራ ላይ እንዳለ ይታመምና ወደ ቤቱ ይሄዳል። ጓደኞቹ ደግሞ ለመጠየቅ ከሥራ መልስ ወደ ዶክተር አበበ ቤት ይሄዳሉ። የደርጉ ልዩ አፋኝ ጓዶች ብዙ ሰዎች ከዶክተር አበበ ቤት መግባታቸውን እንደሰሙ ቤቱን በርግደው ገብተው በመትረየስ ጨፈጨፏቸው።

፬ኛ አቶ በትረማርያም አሰፋና አቶ ሽታው አበበ ለዘመድ ሠርግ ተጠርተው አዲስ አበባ ይገኙ ነበር። ሥራቸውም አስተማሪነት ነው። ሁሉም የጉጃም ክፍለ ሀገር ተወላጆች ነበሩ።

ሌትናት ኮሎኔል ብርሀኑ ሀይሌ የክብር ዘበኛ ፳፯ኛ ሻለቃ አዛዥ፣ መቶአለቃ ሀይለማርያም ሀሰን የዚሁ ሻለቃ ባልደረባ ደርጉ በህዝቡና በጦር ኃይሎች ላይ የሚፈጽመውን ኢሰባዊ ተግባር በመቃወም በአሰብ ወደብ በትዕዛዛቸው ስር የሚገኘውን ሠራዊት በማሰመጽ በሐምሌ 1968 ዓ ም ኢትዮጵያ ከደርግ አገዛዝ ስር ተላቃ ጊዜአዊ ህዝባዊ መንግሥት እንዲመሰረት ያቀረቡት ጥያቄ አግባብ አይደለም በሚል ምክንያት መኩንኖቹ ህዝቡንና ጦሩን በማስተባበር ላይ እንዳሉ ደርጉ በቀጥታ ከራዲዩ ሰራተኞች ጋር ግንኙነት በማድረግ ከውስጣቸው በገንዘብና በማዕረግ ገዝቶ ሁለቱንም መኩንኖች ሳያስቡት አስገድለዋቸዋል።

፭ኛ በሰዳሞ ክፍለ ሀገር የኩንስ ጉሳዎችና የጉጂ ጉሳዎች ከጥንት የመጣ ግጭት እንዳላቸው የታወቀ ነው። በነዚህ ሁለት ጉሳዎች መካከል በደረሰው ግጭት ምክንያት 153 የሚሆኑ የሰቦም ሰሮ ወረዳ ነዋሪዎች እንዲታሰሩ ሆነ። በዚህም የተነሳ የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ ሻለቃ ተፈራ ወልደትንሳይና የአሬሮ አውራጃ አስተዳዳሪ ሻለቃ ታከለ ወልዴ በጭቅጭቅ ላይ እንዳሉ ሰዎቹ በእሳት ተቃጠሉ። በዚህም ምክንያት የአሬሮ አውራጃ አስተዳዳሪ ሻለቃ ተከለ ወልዴና የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ አራት ኪሎ ታሰሩ። ይህንን ከባድ ወንጀል ለማጣራት የደርጉ የምርመራ ሹም ሻለቃ ዮሐንስና እያሌ ተከታዮቹ ወደ በታው በመሄድ ለማጣራት ሲዘጋጅ የአውራጃ ፖሊስ አዛዥን በነፃ ለቀው ሻለቃ ታከለ ወልዴን እነ ሻለቃ አጥናፉ አባተ በሄሊኮፕተር ይዘው ወደ ሲዳሞ ክፍለ ሀገር አሬሮ አውራጃ በመውሰድ ህዝቡ ሰብስበው ሻለቃ ታከለን ነሐሴ 1968 ዓ ም ገደሉት።

ነገር ግን ሻለቃ ታከለ እንደገለጸውና በነሻለቃ ዮሐንስ በኩል የተገኘው መረጃ እንደታወቀው እነዚህን ሰዎች እንዲታሰሩ ያደረገው የክፍለ ሀገሩ አስተዳደሪ ሻለቃ ተፈራ ወልደትንሳይ ነው ተብሎ ጥፋቱ ወደ ሻለቃ ተፈራ በማምራቱና ይህ ከሆነ ደግሞ ሌ/ ኮ መንግሥቱን የሚነኩ ጉዳዮች ነበሩ ስለተባለ ሻለቃ ተፈራን ከቦታው አንስቶ ወደ ባሌ በማዛወር ሻለቃ ታከለን ደግሞ በመግደል የህዝቡን ዉኸት ለማደፈን በቀጥታ የነመንግሥቱ ሴራ መሆኑ የታወቀ ነበር። ስለሁኔታውም ሲገልጹ ምን ያህል ሻለቃ ታከለ ጨካኝ እንደሆነና ደርግም ለአራር ህዝብ ደሙን የተጠማለት መሆኑን አብራርቷል። ሆኖም የትኛው ትክክል ሆኖ በህይወት ያሉት ወደፊት የሚጠየቁበት ጉዳይ ነው። ነገር ግን እነዚህ ምንም የማያውቁ 153 አርሶ አደሮች መሞታቸው ሀቅ ነው።

፳ኛ መቶ አለቃ መላኩ ተፈራ የደርግ አባልና በሂላም የጐንደር ክፍለ ሀገር አስተዳደሬ ነበር።

በ1966 ዓ ም ገደማ ደርግ በጣም የተደከመበትና ተቃዋሚ ቡድኖች በአንገሩ የገነኑበት ጊዜ ነበር። በተለይም በጐንደር ክፍለ ሀገር ኢዲኅ /EDU/ ከገጠሽ በሰይ የሚሆነውን የገጠር ክፍልና ጥቂት ከተሞችን የሚቆጣጠርበትና ኢህአፓ /EPRP/ ደግሞ በከተማና በገጠር ትግሉን ያፋፋመበትና በተለይም ወጣቱ በብዛት (95% ማለት ይቻለል) የኢ ሀ አ ፓ ደጋፊና አባል የነበረበት ጊዜ ነበር።

መቶአለቃ መላኩ ወደ ጐንደር ሲሄድ አንድ ተልዕኮ ነበረው፤ ይሄውም በወጣቱ መሀል ሽብር ለቆ ህዝቡን ማደናገጥና በደርግ ቁጥጥር ስር ማድረግ ነበር። ይህን ተልኮውን ከግቡ ለማድረስ መላኩ የጐንደር ህዝብ በጣሊያን ጊዜ እንኳን አይቶት በማያውቅ አረመኔያዊ ግድያና ግርፋት በአጭር ጊዜ ውስጥ ህዝቡን አደናገጠው። ይህን ተግባሩን ለማከናወን የሚረዱት ሸምበል ዘሪሁን በተባለ መኩነን የሚመራው በግድያና በአፈና በግርፋት ስራ በተለይ የሰለጠነው የአፋኝ ጓዱ ከአዲስ አበባ ተላከለት።

የመላኩና የአፋኝ ጓዱ ዋና ኢላማና በአጭር ጊዜ ለማጥፋት የተነሱት ወጣቱን ነበር። ሆኖም ሌላው ህዝብ አብሮ መቆጠሩ አልቀረም። ከሰሩት አሰቃቂ ሁኔታዎች ውስጥ እንደዶችን ለመጥቀስ እሞክራለሁ።

ወጣቶችን እያስገደዱ እየገረፉ ነጋዴዎችን በማሰር ቤታቸውን በመፈተሽ የተገኘውን እቃ ሁሉ መውረስ መዝረፍ፤ ባለትዳሮችን የገንዘብና የግብረ ሥጋ ግንኙነት መጠየቅ፤ ልጃገረዶችን መድፈር በአደባባይ መግረፍና ማሰቃየት፤ በገፍ መግደልና አሬስቸውን መወርወር፤ የመሰሰሉት ነበሩ።

ለማስረጃነት አንድ በቅርብ የማውቀውን የግፍ አገዳደል ለመጥቀስ እወዳለሁ።

በ1969 ዓ ም በግንቦት ወር በ ጐንደር ከተማ አዘዞ ቀበሌ እድሜያቸው በግምት ከ14 እስከ 60 የሚሆኑ ሰዎች አስቀድሞ በተዘጋጀ ጉድጓድ ዳር እጃቸውንና እግራቸውን ታስረው





ተደርድረዋል።

መቶአለቃ መላኩ በሸምበል ዘሪሁን ወታደሮች ታጅቦ ከቦታው ደረሰ። ከሱንና ቅጣቱን ለመበግት የተጋበዙ ብዙ የጦር ሰራዊትና የፖሊስ ባልደረቦች በቦታው ይገኛሉ። ጥፋት የሚባለውም በመላኩ አንደበት ተነበበ። ይሄውም የኢህአፓና የኢዲኅ አባላት መሆናቸውን እንደሚጠረጠርና በፀረ አብዮት ተግባር ተሰትፈዋል የሚል ነበር። መላኩ ከሱን አንብቦ ሲጨርስ «ቀጥል» የሚል ቃል ሲናገር ወዲያው ኑ የጥይት እሩምታ በሰዎች ላይ ወረደ። ሚዳው በንፁህ ደም በሸቀጠ፤ ደግቸው እንደ ጉፍ ወረደ በቦታው ተፈናጠቀ የጉርጓዱ አፍ ጽጌረዳ መሰለ። የተቆፈረው ጉድጓድ ከተረሸኑት 85 ሰዎች በግምት ወደ 60 የሚሆኑትን ይዞ ሞላ። የቀረው ሬሳ ደግሞ ሜዳ ላይ ተቆለለ። በዚህም አላበቃም፤ እያንዳንዱን አሬሳ እያገላበጡ ኪሱን መፈተሽና ያሰሩትን ሰዓት መፍታት በግድያው የተሰማሩት ወታደሮች ቀጠሉ። ወርቁንም ከጣታቸው ለማውለቅ የሚያሳዩት ትንቅንቅ በቀላሉ የሚረሳ አይደለም። መቶአለቃ መላኩ ይህ ሁሉ ሲደረግ በቦታው ላይ ቆሞ ይመለከት ነበር። በቀሩት እስረኞች ላይ የዚህ አይነት እርምጃ ከመውሰድ ወደ ሂላ እንደማይል አስጠንቅቆ የሰነ ስርአቱ ፍፃሜ ሆነ።

ለአንድ ደቂቃ የዚህን አሰዛኝ ሁኔታ ለሚያንሰላሰለው 85 ሰዎች በሙሉ እስኪገደሉ ድረስ ተራው ያልደረሰው እስረኛ ምን አይነት ጭንቀት ይኖርበት ይሆን? ሞታቸውን አይተው ሲሞቱስ የተመለከተ ሁሉ ምን ተሰማው።

መላኩ ይህ ሁሉ ሲሆን አንድም የሰው ህይወት ያለፈች አልመሰለውም ነበር። እንዲያውም ለአንዳንድ ለቀረቡት ሰዎች «እናንተ የጐንደርን ህዝብ እታውቁትም እን ተወልጀ ያደግሁት እዚህ ነው። የጐንደር ሰው እንደ ቴዎድሮስ ያለ ጨካኝ ነው የሚወደው» በማለት እራሱን ከቴዎድሮስ ጋር ለማወዳደር ይሞክር ነበር።

መላኩ ተፈራ በዚህም አልተወሰነም። የብዙ ሰዎችን ትዳር አፍርሷል። ባሎቻቸውን እያሰረ ለመፍታት ከኔ ጋር እደሪ እያለ ብዙ ሴቶችን ደፍሯል፤ ለግብረ ስጋ ግንኙነት ብቻ በመኖሪያ ቤቱ ከአምስት ያለነሱ ሴቶች እንደነበሩ ይታወቃል። ትንሽ ገንዘብ ያላቸውን እንኳን ሳይቀር እየገደለ ንብረታቸውን ወርሷል፤ ሚስቶቻቸውን ለዝሙት ዳርጓል።

ይህ ግለሰብ ከመንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር የጠና ወዳጅነት አለው። ይህ በቀላሉ ከ15000 እስከ 20000 ሰው ደም ያፈሰሰ አሁንም አዲስ አበባ ከተማ ይገኛል።

፫ኛ ሸምበል በሻ ገብረህይወት የደርግ አባል፤ ይህ ሌላው አረመኔ መቶ አለቃ መላኩ ወደ ጐንደር ሲላክ አብሮት የሄደ የደርግ አባል ነው። ገብረህይወት እንደፈለገው የመግደል ፈቃድ የተሰጠው በቀጥታ ከሊቀመንበሩ መንግሥቱ ኃይለማርያም ነው።

ይህ ሰው በይበልጥ የሚደሰተው ደግሞ ሰውን አስር አይኑ እያየ ወደ ገደል በመወርወር ነው።

ቀሰውስቱንና መነኩሰቱን ተማሪዎችንና አስተማሪዎችን አዳህሪያን እያለ «ኢዬቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ያደረጋት ጠሰቶቹንና ከዳተኞችን በገደል በመወርወር፤ እጅ በመቁረጥ፤ አይን በማጥፋትና በእሳት በማቃጠል ነው።» እያለ እናንተም እንተባበርም ካላችሁ እስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል፤ በማለት ብዙ ቀሰውስትን ወደ ገደል ወርውሯል።

በመጨረሻም መላኩና ገብረህይወት በሰኔ ወር 1979 ዓ ም የግፍ ስራቸውን ለማከናወን በሄሊኮፕተር ሲጓዙ በደረሰው አደጋ ገብረህይወት ነደ ሲሞት መላኩ ተረፈ።

፰ኛ ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር መለስ ስንል ደግሞ ከጉንደርም ሆነ ከሌሎች ክፍለተ ሀገሮች ተመሳሳይ ስቃይና መከራ ደርሷል። ምንም እንኳን አዲስ አበባ የፋሽስቶች መመንጫ ቢሆንም ህዝቡን ወጣት ከሽማግሌ ሳይለዩ ያሰሩ፣ የገረፉ፣ የደፈሩና የገደሉ የትም ቢሆን ፋሽታዊ ስራቸው አንድ ነው።

ሰውጡ እንደጀመረ ከደረሰንበትና ከሰማነው ውስጥ አንድ ምሳሌ ብቻ መጥቀሱ ይበቃል። ከሰበታ ወጣ ብሎ ያለው ፉፋቴ አጠገብ ባለው ድልድይ ስር ሰባት ወጣቶች ከተበደቡ በኋላ በሽቦ ታንቀው በደምብ ባልተቆፈረ ጉድጓድ ተቀብረዋል። ከነኝህ ወጣቶች እንዲት ልጃገረድ ህይወቷ አሳለፈ ኑሮ አንገቷን በትንሹ ወጣ አድርጋ ስታጣጥር እንዲት ሴት በአካባቢው ስታልፍ አይታ ጠጋ አለች። ሴትዬዋም ሰው መሆኑን ተገንዝባ በድንጋጤ ለሰበታ ፖሊስ አመለከተች። ፖሊሶች ሁኔታውን ስለማያውቁ ልጅቷን አውጥተው ለህክምና ወደ አዲስ አበባ ላኳትና ጉዳዩን ለሸዋ ፖሊስ አመለከቱ። ግድያው ገና ያልተጧጧፈ በመሆኑ ፖሊሶች ጉዳዩን ለደርግ የጥበቃና መምሪያ ሀላፊ ኰሎኔል ዳንኤል አስፋው አስታወቁ።

ዳንኤል ወዲያውኑ ልጅቷ የተኛችበትን ሆስፒታል ዳግማዊ ምንሊክ መሆኑን አጣርቶ ጉዳዩን መጀመሪያ ያመለከተውን ፖሊስ በእስቸኳይ ጽህፈት ቤቱ እንዲመጣ ጠራው። ግድያው የተፈጸመው ሚያዚያ 1967 ዓ ም ስለነበር ዳንኤል ነገሩን ለመደባበቅ ሞከረ። ስለዚህም ስታጣጥር የተገኘችው ወጣት ሆስፒታል ከደረሰች በኋላ የት እንደደረሰች አልታወቀም። ከሰበታ የተላከውም ፖሊስ ወደ ዳንኤል ከሄደ በኋላ ምን እንደሆነ ያወቀ የለም።

፱ኛ በአዲስ አበባ ከተማ ከተፈፀሙት ጭካኔዎች ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ምሳሌ እንደዚህ ነው። በሌ/ ኰ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ላይ የመግደል ሙከራ ይደረጋል። ይህ እንደሆነ ወዲያውኑ የመንግሥቱ ወዳጅና ጓደኛ የነበረው ለፖለቲክ ትምህርት ወደ ሞስኮብ ሄደ በቅርብ የተመለሰው ሽምበል አበበ የተባለው ወደ ካሳንችስ ሰፈር በማምራት መንግሥቱን ለመግደል ሞከረ የተባለው የኤርትራውያን ነፃ አውጭ





ድርጅት ነው ስለተባለ ሽምበሉ ትግርኛ ተናጋሪዎች ላይ በቀል ለመውሰድ በምስግር ፋብሪካና በደብረ ብርሃን መንገድ አካባቢ ህዝቡን ሲያስቃይ አምሽቶ ህዝቡ ወደየቤት ማምራት ሲጀምር ሽምበል አበበ እንደራሴ ሆቴል በመባል ወደሚታወቀው ቡና ቤት አምርቶ በቡና ቤቱና በመኝታ ክፍሉ ያሉትን ሁሉ አስወጥቶ በሆቴሉ በስተጀርባ ባለው የመኪና ማቆሚያ ሰብስቦ ሁሉም ሰው እንዲምበረከክ አደረገ።

ከዚያም የተንበረከከውን ሰው እየፈተሸ ሳለ አንድ ለስራ ጉዳይ ከሌላ ክፍለ ሀገር የመጣ የአውራጃ አስተዳዳሪ ሌ/ ኰሎኔል በድንገት አልጋ ፍለጋ ወደ ቡና ቤቱ ሲገባ እሱንም እንዲበረከክ አዘዘው። ኰሎኔሉም ማንነቱን ለማስረዳት ሞክሮ ለጊዜው ባይሳካም በልምምጥ ወደ ቤቱ እንዲገባ ተፈቀደለት። የኰሎኔሉን ጉዳይ በማየት ደግሞ ሌሎች የተመሳሰለ ጥያቄ በማቅረብ ቢማጠኑም አበበ በጭራሽ አለ። ሰዎቹ የመጡት ከባሕር ዳር ከተማ በመንግሥት ስራ ለስብሰባ ነበር ተብሏል። እነኝህ ግለሰቦች ትግረኛ ተናጋሪዎች ናቸው።

የቡና ቤቱ የታወቀችው ካሸር (ገንዘብ ተቀባይ) ትግርኛ ተናጋሪ በመሆኗ ከተንበረከኩት አንዷ ናት። ሽምበል አበበ ሰዎች እንደተንበረከኩ ያለምንም ጥፋት በጥይት ጨፈጨፋቸው። ጊዜው ገና ግድያ ያልተፋፋመበት ጊዜ በመሆኑ ህዝቡን አደናግጦታል።

ይህ ግለሰብ በአስ አበባ ከተማ ካዛንችስ አካባቢ ብዙ ሴቶችን በጥይት በመግደልና በማቁሰል የታወቀ በመሆኑ ለመንግሥቱ ብዙ ሪፖርት እንደደረሰውና ሽምበሉንም ቢሮው አስጠርቶ ስካሩንና ግድያውን እንዲያቆም ትዕዛዝ የሰጠው መሆኑ በጊዜው ቢታወቅም ለፈጸመው ከባድ ወንጀል አልተጠየቀም።

፲ኛ ሌላው ግፍ ደግሞ በአብዬቱ ላይ ህዝቡን እንዲከፋፈል፣ ሽብር እጥረት ለመፍጠር የሞከሩና በጠቃሰይም አሸጥረኛ ነጋዴዎች በማለት ያለውን የእሰራር ብልሽትና የችሎታ ማነስ በነጋዴዎች ላይ ለመለከክ በተደረገው ሙከራ በሳጠፉት ጥፋት የተገደሉት የጠበሬ ነጋዴዎች ስም እነሆ ቀርቧል።

አቶ መኑር ካሊል ሀሰን
አቶ ተስፋዬ ኪሮስ ወልደ ሥላሴ
ሸክ ጀማል ኢብራሂም
ሐጅ አደም መሐመድ
አቶ መሐመድ ሰይድ
አቶ በዛው ነጋሽ
አቶ ደምሴ ከበደ
አቶ እሰፋ ካሣ

ሲሆኑ ህዝቡን ለማረጋጋት፣ ነጋዴዎችን ለማስፈራራት የተደረገ ነበር።

፲፩ኛ  የራሱን ሰዎች እንደ አዞ እየዋጠ ማልቀስ ደግሞ የአንድ ሰሞን ተግባሩ ነበር። ለምሳሌ ያህል በፀረ አብዮተኞች ተገደሉ የተባሉ የደርግ አበላትና የመኢሶን መሪዎችን መጥቀስ ይቻላል።

መቶ አለቃ ግብያው ተመስገን የደርግ አባል የማስታወቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ
ኮሎኔል ካሣየ ማንደፍሮ  የከፋ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ
አቶ አብደላ በድሉ  የሐረር ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ
አቶ አብደላሒ አብድረህማን  የመኢሶን ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረ

እነዚህ ሰዎች ከደርጉ የተሰጣቸውን ማንኛውንም አይነት ስራ ለመስራት ከመግረፍ እስከ ተኩሶ መግደል እንቅ ማስቃየት የመሰሰለውን አረመኔያዊ ስራ ለመፈጸም ወደ ኋላ ብለው አያውቁም ነበር። በሰፈሩበት ቀና መስፈር አይቀርም እንደሚባለው ሁሉ ደርጉ የገደላቸውና የራሱ እምሳል የፈጠራቸውንም ቢሆን ከመግደል ወደኋላ ስለማይል በነዚህ አራት ሰዎች ላይ በድብቅ እርምጃ ከወሰደባቸው በኋላ ፀረ አብዮተኞች ገደሏቸው በማለት የውሸት እንባ አፍስሷል።

ይህ መጽሐፍ የሚዘረዝረው አብዮቱ ከፈነዳበ በሁለት ዓመት ውስጥና እልፎም ከዚያ በኋላ የተፈጸሙትን ጥቂቶችን በስሆኑ ከመጀመሪያው ጠቀሉትን ወጣት ፋሽስቶች መግለጹ በጣም አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ1966 እስከ 1968 ዓ ም ድረስ የተከሰቱት ገዳዮች ከዚህ በታች ያሉት ናቸው።

፩ ሻለቃ መላኩ ተፈራ
፪ ሻለቃ አሊ  መብ
፫ ሻለቃ ጌታቸው  ሽበሽ
፬ ሻለቃ ብርሀኑ  ከበደ
፭ ሻምበል ገብረሀይወት

፮ መቶ አለቃ ደበታ  ሲሆኑ እብረዋቸው ግፍ ሲፈጽሙ የነበሩ የተደራጁ የሲቪል ገዳዮችና አፋኞች እንደነበሩ አይዘነጋም፤ በአጠቃላይ ወንጀለኞች እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት ደግሞ አይቻልም።

በተለይ እፋኝ ጓድ ተብለው የሚጠሩት የስለጠኑ ወታደሮች ቀድሞ ከነበሩበት ከድሬዳዋ ምድብ ስራቸው ተነስተው በደረጉ ትዕዛዝ ስር በመሆን፤ ከላይ ከተጠቀሱት መኮንኖችና እንዲሁም የነ ሌ/  ኮ  መንግሥቱ የወንጀል ስራ ተባባሪ እንደሆኑ ተደረገ። ይህ ክፍል ግን ቀድሞ ይሰራ ከነበረው ገዳጅ ሌላ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ በመዘዋወር ይሰሩ እንደነበር ይታወቃል። አዛዦቻቸውም የአሁኑ ሜጀር ጀኔራል በጊዜው ሌ/ ኮ ሥዩም መኮንን ነበር።

በተለይ ይህንን ስራ በማግኘታቸው ቋሚ ደመወዛቸው ተቀምጦ ከአየር መንገድ ስለሚከፈላቸው እንደ አጋጣሚ ሆኖ አየር ጠለፋ እንኘተው ከገደሉም ሹመት





ስለሚገኝበት ከክፍሉ ለመሄድ የሚመኘው ብዙ ነበር። በዚህም ቦታ የሚመደበው በዘመድ እንጅ እውቀት ወሰኝ አልነበረም።

በ፲፱፻፷፰ ዓ ም በለውጡም ወቅት ለደርጉ ጥበቃ ወደ ቤተ መንግሥት ይሄው ክፍል በመሄድ ቁጥሩ ወደ ሻለቃ ጦር ከፍ ብሎ ነበር። ይህም ክፍል በቀጥታ በደርግ ስለሚታዘዝ በለውጡ መጀመሪያ በየክፍለ ሀገሩ በመላክ የመንግሥት ተቃዋሚ ናቸው የተባሉትን በክፍለ ሀገሩ ከድሬዎች ጠቋሚነት መምህራን፤ ተማሪዎችና ሌሎችም ያለምንም ወንጀል በሌሊት ከቤታቸው ታፍነው ወደ ስውር ቦታ ተወስደው ከተገደሉ በኋላ ባልታወቀ ቦታ በአንድ ላይ በመቅበር ለዘመድ የት እንደደረሱ እንዳያውቁ ይደረግ ነበር። ይህንን ገዳጅ የሚፈጽመው ክፍል ተመልሶ እዲስ አበባና ደብረ ብርሀ ባለው የጦር ሠፈር ሄዶ ይቀመጥ ነበር። በኋላም በየክፍለ ሀገሩ መሪ በነበሩ የደርግ አባሎች ጋር ጠባቂና ገዳይ በመሆን ለሕሊና አስከፊ የሆኑ ግድያዎች ይፈጽሙ ነበር።

## ክፍል ፲፩
## የግለሰቦች ሚና
### 1 ኰሎኔል ዓለምዘውድ ተሰማ

የመጀመሪያውን ወታደራዊ ንቅናቄ ቅድመ ሁኔታ ስንከታተል መሠረታዊ የሆኑ እያሉ ታሪኮችን ለማወቅ ያስችሉናል። ከአሮጌው ፊውዳል ሥርዓት ወደ አብዮታዊ ለውጥ ለማሸጋገር እያሌ የጭቆናና የብዝበዛ ሥርዓቶችን ለማጥፋት አገርን ለመሠረታዊ እድገትን ለማዘጋጀት የሚቻለው በቆረጡ ታሳቢ የሕዝብ ወገኖች በመሆኑ በለውጡ ጊዜ የሚደቀንባቸውን እያሌ የተወሳሰቡ ነገሮች ለማለፍ ከስፈለገም ሕይዎታቸውን ለሞት እሳልፈው ለመስጠት በመንፈስ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ለአንድ የሕዝብ ወገን ለሆነ ሰው የመጀመሪያ ተግባሩ ይሆናል።

ይህም በመሆኑ እንደነዚህ ዓይነት ሰማዕታት መልካምም ይሁኑ መጥፎ፣ አስደሳችም ይሁን አሸባሪ፣ ቀጥተኛ የሆነ ሀቀኛ መንገድ በመከተል ለህዝብ እድገት ሲሉ ብዙ ችግሮችን ማሳለፍ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ ነው በሀገራችን የተከሰተውን ፲፱፻፷፮ ዓ ም የሕዝብ አመጽ የመሩትን ሰዎች የግል ሚናቸውን በጭሩ ለመግለጽ የፈለግሁት።

በዚህም መሰረት ይህን የመሰለ ታሪክ ከሰሩት ቆራጥ መለዮ ለባሾች ውስጥ አንዱን የኰሎኔል ዓለምዘውድን ታሪክና የፈጸማቸውን ሥራዎች ለመጥቀስ እወዳለሁ። በግለሠቡ የሕይወት ታሪክ ውጥ ብዙ ያልታወቁና በሚገባ ያልተጠቀሱ ነገሮችን በዚህ አጋጣሚ ማወቅ እንችላለን።

በለውጡ ዋዜማ ላይ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትና ካቢኔያቸው ሽብር ባጋጠመበት ወቅት በዚህ አጋጣሚ ሁኔታ ተጠቅሞ ያረጀውና ያፈጀው መንግሥት ካቢኔ ከሥልጣን ለማውረድ ለመጀመሪያ ግዜ እድማውን ከጀመሩት መኰንኖች መካከል የአየር ወለድ ሻለቃ አዛዥ ኰሎኔል ዓለምዘውድ አንደኛው ነበር።

ኰሎኔሉ በአድማው ውስጥ ከመጠመዱ በፊት በኑሮውም ሆነ በሥራው ጭራሽ የማይደሰት እንደነበረና በተለይም የአየር ወለድን ጦር ለማዘዝ በዚያን ግዜ ብዙ መኰንኖች የሚፈልጉ በመሆናቸው በሥራው ላይ እንዳንድ መሰናክሎች ይገጥመው እንደነበር ይናገራል።

ሁለተኛው የአየር ኃይል እና የአየር ወለድ ሠራዊት በሥራው ሆነ በኑሮ በአንድ ክልል ውስጥ በመሆናቸው እርስ በርስ የሚያደርጉት ግጭት እየተከረሩ እስከመደባደብና መገዳደልም በመድረሳቸው ሁለተኛው ችግሩ ነበር።

ሦስተኛው ደግሞ ለውጡን እስመልክቶ በገባበት የሥራ ኃላፊነት ላይ እንዳንድ





ምሁሮችና ወታደሮችም ሆኑ ሲቪሎች ንጉሡ በአስቸኳይ እንዲገለበጡና የደም መፍሰስንም የሚያስከትል አመጽ እንዲሰሩ ይደረግበት የነበረው ግፊትና ተጽዕኖ ቀላል አልነበረም።

አራተኛው ጉዳይ እዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ልጅ እንዳልካቸው መኰንን ጋር ከለው የግል ትውውቅ በመነሣት ያኔ በያዘው ጊዚያዊ ስልጣን መጠቀም ለስልጣናቸው መጠናከርና በጠላቶቻቸውም ላይ ድል ለማግኘት የሚያደርጉበት ተጽእኖ ነበር።

አምስተኛው ንጉሡም ቢሆኑ የኰሎኔል ዓለምዘውድን ወድያ ወዲህ ማለት በቀላሉ አላዩትምና በዚህም ምክንያት በገንዘብና በማእረግ ለመደለል በጄኔራል አበራ ደምሴ በሌሎችም ባለሥልጣኖች በኩል ተወጥሮ በመያዝ ግራ የተጋባ ሲሆን አንድም ስጦታ ለመቀበል አለመፍቀዱ ደግሞ ከፍተኛ ችግር ነበር።

የመከላከያ ሚንስተር የነበሩት ጄኔራል አቢይ አበበ ለኰሎኔሉ የቅርብ ወዳጅ የነበሩ ናቸው። እሳቸውም የመከላከያ ሚንስትር ሆነው ከተሸሙ በኋላ ከሳቸው የሚፈለገው ጠንካራና ቆራጥ አዛዥ መሆን ሳለ ኰሎኔሉ ሥልጣን እንዲይዝ በመገፋፋት (ማለትም የራሳቸው የነጄኔራል አቢይ ሥልጣን) ያበቃና ያከተመላቸው መሆኑን ከነገሩት በኋላ በነሱ ላይ የነበረው እመለካከት አከተመ። ከዚያም አልፈው ጄኔራል አቢይ ኰሎኔሉ የጄኔራልነት ማዕረግ ተሰጥቶት የጉጂም እንደራሴ እንዲሆን የታሰበ መሆኑን ገልጸውለት የሚመጣው ነገር አይታወቅምና መጠጊያ ትሆነናለህ ብለው ያቀረቡለትን ልመና አልተቀበለም።

በአየር ኃይሉና በአየር ወለዱ መካከል ያለው ግጭት እንዲወገድና በሁለቱ መተባበር ንጉሡን አውርደው በሱ መሪነት ሥልጣን መያዝ እንደሚቻል ከአየር ኃይሎችና ከሌላም ክፍል የተላኩትን መኰንኖች ሀሳባቸውን በመጠራጠር ሳይቀበላቸው ቀርቷል። ነገር ግን እንቢተኛነቱ የሚጸናው የአየር ወለድ የአስተዳደር መኰንን ከነበረው ሻምበል አብይ ኑር ጋር በሚደረገው ድርድር ሻምበሉ ከተስማማ በኋላ ስለሆነ በዚህም ምክንያት ሻንበሉ ተጠይቆ ንብ ያሰውራ «ኢትዮጵያም ያለ ንጉሥ አትኖርም ጠቅላይ ግዛቶቻችንም አይከፋፈሉም» በማለት ስለተቃጣ ዕቅዱ ከሸፈ። ከዚህም በላይ የአየር ወለድ ጦር ልምምድ እያደረገ ስለሆነ ሄዳችሁ ማየት ትችላላችሁ ብሎ ዘተባቸው። በዓለም ዘውድና በአብይ ኑር መካከል የሚደረገውን የሀሳብ ልውውጥ ከሞከሩት መካከል አንደኛው እኔ ነበርኩ። ከአየር ኃይል ከአየር ወለድ እንዲሁም ከሲቪል ወገን ሻምበል አብይ ኑርን አግባብቶ ኰሎኔል ዓለምዘውድ መንግሥት ለመገልበጥ ፈቃደኛ እንዲሆን የደከሙት ሰዎች አሁንም በህይወት አሉ።

ኰሎኔል ዓለምዘውድ ግን ከጊዜው በመነሳት ከአካባቢው ሁሉ ተጽኖ የሚያደርግበት ስለመሰለው ወደፊት ከመግፋት ይልቅ ሥራውን ለቆ መሰናበት ስለፈለገ የስንብት ደብዳቤ ጽፎ ለጄኔራል አቢይ አቀረበ። ጄኔራል አቢይም ጃንሆይ ሳያውቁ

መሰናበት አትችልም በማለታቸው ኰሎኔሉ «እኔና ጃንሆይን የሚያገናኘን ነገር ስለሌለ ስንብቱን እፈልጋለሁ» ብሎ ስለከረረ «ባይሆን የስድስት ወር ፈቃድ ይሰጥሀል እንጅ አትሰናበትም» ብለውት ተስማምቶ ወጣ።

በዚህ ዕለት ከሰዓት በኋላ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ከጄኔራል አቢይ ቢሮ ሲወጣ የቀድሞ ባለሥልጣን ሚስቶች በድንጉት ከበቡትና ባሎቻቸው እንዲፈቱላቸው ጠየቁት። ኰሎኔሉም እኔ ሥራየን ያስረከብኩ ስለሆነ አያገባኝም በማለት ወደ መኪናው ሲገባ ሲል ሁለት መኪና አየር ወለድ ወታደሮች ከመከለከያው ግቢ ቆመው አየ። ምንድ ነው ብሎ ቢጠይቅ አንድ መኰንን እርስዎን እንፈልግም ነው የሚሉት አለው። እሱም ከት ብሎ ከሳቀ በኋላ «እኔ ራሴ ትቸው የለም እንዴ ለአንድ ቀን ለምን አይታገሱም» አለና ከመኪናው ውስጥ ገብቶ ወደ ደብረዘይት መኖሪያ ቤቱ ሔደ። ጦሩንም በግድ ያሰደመው ሻንበል ገብረ ሕይወት የተባለው የቅርብ ወዳጁ ነበረ። ይህም ሰው በመጨረሻ ወደሱዳን ሲኰበልል ተይዞ ደርግ ረሸኖታል።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ኰሎኔሉ ሥራውን ከለቀቀ በኋላ የፀጥታ ኰሚቴው ተጠናክሮ የጸጥታ ኮሚቴ ተብሎ ነበር። ከዚህ በኋላ ዓለምዘውድም በስውር ከተቀመጠበት ቤት ሆኖ ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ ስልክ ደውሎ አጥናፉንና ብርሃኑ በየሀን ሲያነጋግር ሁለቱም የቅርብ ወዳጆቹ ከመሆናቸውም በላይ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ አብረውት የሠሩ በመሆናቸው ድምፁን በሰሙ ጊዜ «እባክዎን ይምጡ የርስዎ ከኛ ጋር መሥራት የበለጠ ያጠናክረናል» አሉት። እሱም እናንተ ዝንጀሮዎች ምናችሁ ይታመናል በማለት ከቀለደ በኋላ ለሻለቃ አጥናፉ እንዲህ አለው «ባሁኑ ጊዜ ንጉሡን አትንኩ፣ ችግር ይፈጠራል፤ በመጀመሪያ በአካባቢያቸው ያሉትን አጽዱ፤ ከዚያ በኋላ ብቻቸውን ይቀራሉና ማንኛውንም ማድረግ ይቻላል» አለው። አጥናፉም በበለጠ ተደሰተ፤ ቀጥሎም «ያንን ሸንቀስ ብታስመጣው ይሻላል፤ እሱ ማስተባበር ይችላል አንተም የሱ ምክትል ሆነህ ብትሰራ መልካም ነው። በኔ ጊዜም አለማስመጣቴ በጣም ይቆጨኛል አለው።» በዚህ ውይይት ላይ አብረን የነበርን አምስት ሰዎች ነበርን፤ እኛም በመገረም ማንን እንደሆነ ጠየቅነው። ዓለም ዘውድም «ሻለቃ መንግሥቱ ሀይለማርያም የሚባል ሐረር ያለ ነው» አለን። ከጥቂት ቀናቶች በኋላ መንግሥቱ በኰሚቴው ውስጥ እንዳለበት ሰማን።

በዚህ መካከል ጊዜው እየረጠ ነው። ሁኔታዎች ሁሉ እየተለዋወጡ ናቸው። ስለዚህ የኰሎኔል ዓለም ዘውድ የመጨረሻ ውሳኔ ወደ ትውልድ አገሩ ጉጃም ሔዶ መቆየት ስለመረጠ ከአዲስ አበባ ምንም ነገር ሳይደርስበት ጉጃም ክፍለ ሀገር ቡሬ ዳሞት ገባ። የኰሎኔሉ ወደ ጉጃም መሔድ አሁን የተቋቋመት የጸጥታ ኮሚቴ የተጠናከረ ባለመሆኑ የሸፈተ እንደሆነ ያስቸግራል በሚል ብዙ አማላጅና አያሌ ሠላዮችን ወደ ቦታው በመላክ ልምምጥ ሲያደርጉለት ሰንብተዋል። ኰሎኔሉ ግን የሱ





ወደዚያ መሔድ ያስቆጣው የቆለ ዳሞት አውራጃ ሕዝብ ሌላውንም በማስተባበር መሸፈ[illegible] በማለት የኰሎኔሉን መሪነት ጠየቀ። ኰሎኔሉም ለውጡ ለእናንት የሚበጅ እንጅ እናንተን የሚጐዳ አይደለም። ለውጡንም ከመጡት ውስጥ አንደኛው እኔ ነኝና መሸፈት የለባችሁም አለ። ህዝቡ ግን አልተቀበለውም።

ይህን ሁኔታ የፀጥታው ኰሚቴ ይሰማ ስለነበረ ሻለቃ አጥናፉና ሻለቃ መንግሥቱ በስልክ ተማጥነው ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ጋበዙት። ኰሎኔል የዓለም ዘውድም በምሳጢር አዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ የቅርብ ወዳጆቹን ከአረፈበት ቤት ሆኖ ጠራው። ነገሩ በጣም የሚያስገርም በመሆኑ ሁሉም ተደናግጠው ለምን እንደመጣ ጠየቁት። ሁለቱ ሻለቆች እንደጠሩት ገለጸ። ሁሉም ዓይንህ ለአፈር ብለው ረገሙትና አሁንም በደንብ ሳታማራ እንዳትገናኛቸው ተባለ። ኰሎኔሉም እሺ አለና ከምሽቱ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ድጋሚ እንደሚገናኙ ዘመዶቹ ገልጸውለት ወደሥራቸው ሄዱ። ዓለም ዘውድም በቀጠሮው መሠረት ለመገኘት ለአጥናፉና ለመንግሥቱ ስልክ ሲደውል ሌ/ ኰ ዳንኤል ስልኩን አነሳ። ዓለምዘውድም ከሁለቱ ሻለቆች ጋር ቀጠሮ እንዳለው ነገረው ዳንኤልም የተደሰተ መስሎ እባክዎን ናፍቀውናል ይምጡ፤ እነ አጥናፉ ወደውጭ ወጥተዋል፤ በኋላ ያገኟቸዋል አለው። ዓለም ዘውድም የአረፈበትን ሰው አስገድዶ በመኪና አራተኛ ክፍለ ጦር በር ላይ ሲያደርስ ዳንኤል ወታ[illegible]ችን አዘጋጅቶ ይጠብቀው ነበርና እጅ አግሩን አጣምረው ተሸክመው በአራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ እስር ቤት ጨመሩት። የዓለም ዘውድ ታሪካዊ ሥራ በዚህ ሁኔታ [illegible] በመጨረሻም ከስልሳዎቹ ባለሥልጣኖች ጋር ጨምረው ገደሉት።

የኰሎኔል ዓለምዘውድ በለውጡ ውስጥ የነበረው ታሪክ ይህ ሲሆን በሱ ታሪክ ውስጥ አያሌ ነገሮች ተወስነው ቀርተዋል።



ኰ/ ዓለምዘውድ ፡ ተሰማ
የአየር ወለድ አዛዥ የነበሩ

## 2 ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቲዎፍሎስ

## ፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቲዎፍሎስ በኢትዮጵያ ሁለተኛ ፓትርያርክ ናቸው። ፓትርያርክ በሰሊዮስ እስኪሞቱ ድረስ በምክትልነት ከዚሁም ሥልጣናቸው ላይ የሐረርጌ ክፍለሀገር ጳጳስ በመሆን እንደራሲያቸውን ሐረር ውስጥ አስቀምጠው ሠርተዋል። የአቡነ ቴዎፍሎስ የዚህ ስልጣን ባለቤት መሆናቸው እንደሚያስረዳው ፓትሪያርክ ባስልዮስ አርፈው በምትክቸው ስለተመረጡ ነው።

የ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ በነበረው ለውጥ ላይ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ሳያሰሙ በኢትዮጵያ አስተዳደር ታሪክ ውስጥ ቤተ ክህነት የሚያሠጋና የአስተዳደሩም መሣሪያ መሆኑን በተገነዘቡ መኰንኖች ውሳኔ መሠረት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ተይዘው እንዲታሰሩ ተደረገ። እርምጃው በሳቸው ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ጳጳሶች፤ ካህኖች፣ መሪጌታዎች እየታደኑ ወደወህኒ ቤት የተሰከሩበት ጊዜ ነበር።

ፓትሪያርኩ ግን የታሰሩበት የተገለለ ቦታ በጃንሜዳ በክብር ዘበኛ ቅጥር ግቢ ውስጥ በክብር ዘበኛ ቁጥጥር ሥር ነበር። በዚህም እስር ቤት ረዘም ላሉ ወራት ቆይተዋል። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ባልታወቀ ምክንያት ከታሠሩበት እስር ቤት በመጥፋታቸው በደርጉ ቤተ መንግሥት ውስጥ ጭንቀት ተፈጥሮ ነበር።

ይህንን አስመልክቶ ያጋጠመኝን መግለጽ እፈልጋለሁ። እኔና የሥራ ጓደኛዬ ቢሮ ተቀምጠን ስለ ሥራ ጉዳይ በመወያየት ላይ እንዳለን ከጥዋቱ አራት ሰዓት ሌ/ ኰ ዳንኤል እሰፋው ስልክ ደውሎ የሥራ ጓደኛዬን አነጋገረው። ዳንኤልም ሲናገር አብዮታችን ካጋጠመን ሁኔታዎች ውስጥ እንደዘሬ ጉድ ሆነን እናውቅም፣ ያ የማይረባ ቄስ ከታሰረበት ጠፍቷል። ወዴት እንደሄደ እናውቅምና እናንተም በፍለጋው ተባበሩን አለ። የሥራ ጓደኛዬም የጠፋው ማን እንደሆነ ስላልገባው ዳንኤልን ጠየቀው። ፓትሪያርኩ ነዋ አለ። ቀጥሎም አገሩ ጉጃም ስለሆነ ወደዚያው ሊሔድ ይችላል። በሔሊኮፕተር ወይም በትንሽ አውሮፕላን ከገር ሊወጣ ይችላል ብለን ስለምንገምት የጥበቃ በታዎችን ሁሉ አጠናክሩ አለ።

የሥራ ጓደኛየም የኔን ስም ጠራና አብረን በመሆን ወደ ጉጃም አቅጣጫ ጥበቃውን እናጠናክራለን፤ ለበር ጠባቂዎችና ለአውራጃዎች ትዕዛዝ እናስተላልፋለን አለውና ስልኩን ዘጋ።

የሥራ ጓደኛየም ሁኔታውን ነገረኝና ሁለታችንም ለተወሰነ ደቂቃ ቆሞ ብለን ማሰብ ጀመርን። ትንሽም ቆይተን ሣናስበው በአንድ ጊዜ ለመናገር ሞከርን። ተሰብስቅንና





ሁኔታው በመረጃ ሠራተኞች በኩል ለክፍሎች እንዲተሰለፍ አድርገን እኔና እሱ በኔ ኔጅነት በሽልሰዋገን መኪና በጉጃም በር በእንጦጦ በኩል ጉዞ ቀጠልን። በመኪናችን ውስጥ ራዲዮ ስለነበረን በእጠቃላይ ስለሚደረገው ፍለጋ ያለውን እንቅስቃሴ እንቆጣጠራለን። ዳንኤልም የሚሰጠውን ትዕዛዝ እንሰማለን።

የፓትሪያርኩ መጥፋት የምንደግፈው ስለነበረ በጉጃም አቅጣጫ የሚደረገው ፍለጋ በራድዮ እንዲተሰለፍ እሳደረግንም፤ ነገር ግን ፍቼ፣ ገብረ ጉራቻ፣ ጉሐጽዮን፤ በተባሉት ከተሞች እየደረስን በዕለት ሁኔታ በመመዝገብ አበሎች ፍለጋውን እንዲቀጥሉ ከደረግን በኋላ በዚያው አካባቢ ስንዝናና ዋልን። ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ከዳንኤል ጋር ለመነጋገር ራድዮ ከፍተን ጥሪ በናደርግ በደስታ ተውጦ ያቀጣፈ ቄስ እረፉ እስደፍቀን ያዝነው እዚሁ በእደብ አበባ ጉፋ ሠፈር እራሱ በሠራው ገብርኤል ቤተ ክርስትያን ውስጥ ተሸጉጦ ባሰደገው በራሱ እሽከር ጥቆማ ተያዘ ስለተባበራችሁን እመሰግናለሁ አለና ራዲዮኑን ዘጋው።

በፓትሪያርኩ መያዝ እኛ ብቻ አይደለንም የተበሳጨ ነው። እያሌ ወታደራዊና የሲቪል አበሎችን ሁሉ አሰዝኗል። ከግማሽ ሰዓት በኋላ ዳንኤል በድጋሚ ደወለ። የደወለበትም ምክንያት በአንበ እውራጃ ሸፍተው የነበሩት ሰዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ከሌሉቹ መኰንኖች ጋር ጸብ ፈጥሮ ደዉ ቃዉ ቃል። እኔ ራሴ ቸግሮናልና ለመወያየት በደንብ የሚያስረዳ አንድ መኰንን ላኩልን አለ። እሱም ጉዳዩን ለማስረዳት ቤተ መንግሥት ዳንኤል ቢሮ ገብቼ ሰላምታ ሰጠሁት። እሱም ብዙም አላነጋገረኝም። በቀጥታ

ጉዳዮን ከጨረሰ በኋላ ቀና ብሎ አይቶኝ በቀጥታ የተጠራሁበትን ምክንያት ማብራራት ጀመረ። ስለሚፈልገው ጉዳይ ግን በኛ በኩል የሚታወቅ አልነበረም። ወድያውኑ ሻለቃ ዮሐንስ የሚባለውን ስልክ ደውሎ ከነጋገረ በኋላ ጉዳዮ በደርጉ ምርመራ ክፍል ውስጥ የተያዘ ነው። ዳንኤል እኔን ቀና ብሎ ካየኝ በኋላ ይህ ጉዳይ በኛ በኩል የሚፈፀም ይመስለኛል መሄድ ትችላለህ አለኝ። እኔም ከዳንኤል ቢሮ ወጣሁና ሻለቃ ዮሐንስ ከተባለው የደርጉ ምርመራ ክፍል ሹም ጋር ለመገናኘት ገባሁ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ዳንኤል ለምን እንደጠራኝ ነገርኩት። ዮሐንስም የሚሰራውን እያውቅም ብሎኝ በሌላ ጉዳዩች ላይ አውርተን ወደ ቢሮየ ተመለስኩ። ሻለቃ ዮሐንስ ሌ/ ኰ ዳንኤልን የገደለው ነው።

ስለፓትሪያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ ጉዳይ ለሻለቃ ዮሐንስ በናደርግ የዋልነውን ፍለጋ አስረድቸው ነበር። እሱም በጣም ተናደደ። ከኔም ሆነ ከዳንኤል የተሻለ ጉዳዮን ያውቀዋል። ዮሐንስም እንዲህ አለ «ያዋረዱት እራሳቸውን ሳይሆን ሁላችንንም ነው፤ በባይ እንደደረስንበት ከሆነ መውጣት ይችሉ ነበር። አሁን የዳንኤል መጫወቻ ሆኑ። ጠጉራቸው ተላጭቷል፤ ቆምጣ አስለብሷቸዋል፤ እግራቸው እንዲሄዱ አድርጓቸዋል፤ እጃቸውንና እግራቸውን አጣምሮ አስሯቸዋል፤ ወደፊትም ሊገሏቸው ይችላል!» አለና

ስሜቱን ገለጠልኝ። በኋላ ሌላ ግዜ እንደምንገናኝ አድርገን በሄድኩበት አኳኋን ቤተ መንግሥቱን ለቅቄ ወጣሁ።

የፓትርያርኩ ጣጣ በሳቸው ብቻ አላበቃም። በጠፉበት እለት የነበረ የጥበቃ ዘቦች ሁሉ ታስረው እየተሰቃዩ ነው። ከሳቸው መጥፋት ጋር ተባብረዋል የተባሉ ሰዎች በሙሉ በምስጢር እየተጠለፉ የት እንደደረሱ አልታወቀም። መጨረሻው አልታወቀም እንጂ ሊያወጧቸው ነበር ተብለው የተጠረጠሩ ብዙ ድርጅቶችና ሰዎች ነበሩ ተብ ሉ ምርመራው ቀጥ ሎ ነበር።

ከዚህ በኋላ ለጥቂት ዓመታት በቤተ መንግሥቱ እስር ቤት ውስጥ ታስረው ከቆዩ በኋላ ከብዙ የቀድሞ ባለሥልጣኖች ጋር የት እንደደረሱ እስከ ሁን አልታወቀም። ስለዚህ የነ ሌ/ ኰ መንግሥቱ የጭካ ኔ እርምጃ በቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ላይ ይኸንን ይመስል ነበር። የፖትርያርኩ መጥፋትና በኋላም መያዝ ትክክለኛው ሁ ኔታ ይህን ነው። ይህንንም ለማብራራት የፈለግሁበት ብዙ ሰዎች በተለያየ ትርጉም የፖትርያርኩን ሁ ኔታ ስለሚገልፁት ተጨባጩን ሁ ኔታ ለማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ በበታውና በስራው ላይ ተሰማርቸ ያየሁትን ለመግለጽ ያህል ነው።





## 3   ሌ ኰ እጥናፉ አባተ

ሌ/ ኰ እጥናፉ አባተ የ፲፱፻፷፮ ዓ ም ህዝባዊ አመጽ በተነሳበት ወቅት የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪ ነበር። ዩንቨርሲቲው ለዕረፍት ሲዘጋ እጥናፉ ከቤተሰቡ ጋር በአራተኛ ክፍለ ጦር ውስጥ ይኖር ነበር። በዕረፍት ላይ እያለ በአዲስ አበባ የመ ኰንኖች እንቅስቃሴ በመጀመሩ ተሰታፊ በመሆን በኮሚቴው አባልነት አገለገሏል።

የመ ኰንኖች ከሚቴ ወታደራዊና ህዝባዊ አመጽ እየገፋ በሄደበት ወቅት ከሌሎቹ የኮሚቴ አባ ሎች ጋር ቀደምት በመሆን በቀድሞ የለሥልጣኖችና የካቢኔ አባ ሎች ተይዘው እንዲታሰሩ ውሳኔ ካሳለፉት መ ኰንኖች ውስጥ አንዱ ነው።

በኋላም በአራተኛ ክፍለ ጦር አባ ሎች አስገዳጅነት በጦሩ ጥያቄ መሠረት ኰሚቴ እንዲቋቋም ተጠይቶ የጦር ኃይ ሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኰሚቴ የተባለውን እንዲፈጠር ካደረጉት መ ኰንኖች ውስጥ ሌ/ ኰ እጥናፉ ግንባር ቀደም ነበረ።

ሥራውን ታሪክ አይዘነጋውምና በዚያ ውዥንብር በበዛበት ሰዓት ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት የተዘጋጀና በቆራጥነትም የማስተባበሩን ተግባር በኃላፊነት በመረከብ ድርሻ ሥራውን የተወጣ ነው። ነገር ግን እጥናፉ በዚያን መጠን ግትርና ነገሮች አገሰብሮ ለማወቅ የማይችል በመሆ ኑ የነኰሎ ኔል መንግሥቱ ሥልጣን መረማመጃ ሆ ነ።

በየዋህነቱና ሰውንም ስለሚያምን የሚሠራውን ስህተትና የሚገጥመውን መሰናክል አያውቅም ነበር። ከውጭና ከውስጥ ሀሳብ ሲቀርብለትም ሳይጠቀምበት ቀርቷል። በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ላይም ከፍተኛ እምነት ነበረው። እስከመጨረሻው ድረስ «ዕድል እንሰጠው ከምንገኘው የደርግ አባላት ውስጥ የተሻለው እሱ ነው። አገሩን ይወዳል። በኔ ላይም ክፉ ነገር እንደማያስብ አምናለሁ» እያለ ተዝናንቶ ደረቱን ለጥይት የሰጠ ቢኖር እጥናፉ ነው ማለት ይቻላል።

የደርግ አባል ቢሆንም በምሁሮችና በተማሪው ጭፍጨፋ ላይ ብዙ ጊዜ ተቃዋሚ ነበር። የኤርትራንም ጦርነት በኃይል እንደማይወጡት የተገነዘበ በመሆ ኑና ሐሳቡን በግልጽ በማቅረቡ እንዲገደል ካደረጉት ነጥቦች ውስጥ ዋነኛው ነው።

እጥናፉን ያመ ኑት የደገፉት ሁሉ ብዙ ችግር ደርሶባቸዋል። እጥናፉን መሣሪያ በማድረግ ሌ/ ኰ ዳንኤል አስፋው በነመንግሥቱ ላይ ተንኮል ይሸርብ እንደነበር እጥናፉ እጠናቶ ቢያውቅም ሐሳቡን አልተቀበለውም። የዳንኤል ሴራ የገባቸው ለእጥናፉ ቅርብ የነበሩ መ ኰንኖች ዳንኤል ለእጥናፉ የሚሰጠውን ምክር እንዲያቆም ያሳሰቡት ነበር። ይህንንም የሚያደርገው እጥናፉን ለመደገፍ ሳይሆን እጥናፉ መንግሥቱን ከተቃወመና እርምጃ ከወሰደበት የሚቀጥለው እርምጃ እጥናፉን ለማጥፋት ቀላል በመሆ ኑ የሥልጣን መረማመጃ መሰላል ለማድረግ እንደነበረ የታሰበ ነው።

በ፲፱፻፷፰ ዓ ም ለመጨረሻ ጊዜ ሊፍተናንት ኰሎ ኔል እጥናፉ አሥመራ ከርሞ

እንገረመንገዱን ወደ አዲስ አበባ ሲያልፍ አድዋ የሚገኙትን የጦር አዛዦች ለማነጋገር ወደአድዋ ሔዶ ባደረገው ስብሰባ «የኤርትራ ጦርነት በኃይል አይፈታም፣ አገሪቷን ከምናጠፋ ሕዝቡንም ከምንጨርስ ሰላም መፈለጉ ጥሩ ነው፤ ይህንን አዲስ አበባ ስደርስ በሪፖርት አቀርባለሁ» አለ። ቀጥ ሎም «ከአሜሪካኖች ልናገኝ የነበረው እርዳታ የታገደ ስለሆነ የአሜሪካ መሣሪያ የታጠቃችሁ ክፍ ሎች ቁጠባ እንድታደርጉ ያስፈልጋል» በማለት ቀደም ብ ሎ በቴሌግራም የተገለጸውን ማብራሪያ በግልጽ አረጋገጠ። ቀጥ ሎም «ይህንንም ስላል ኩ ችግራችንን እንወጣም ማለት አይደለም» ካለ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። በዚህ ዕለት ከተከተ ሉት ካድሬዎች ውስጥ አንድ የመቶ አለቃና አንድ ጄንየር ቴክ ኒሽን ወደኋላ ቀረት ብለው «አጥናፉ በየደረሰበት በማይረባ ነገር አፉን ይከፍታል፣ እስከ ሁን ባሥመራ የፈጸማቸው ፀረአብዮት ሥራ ዎች ሪፖርት ተደርገዋል። በኛ ግምት አዲስ አበባ ከደረሰ በኋላ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል» በማለት ለ ኔና ለአንድ የሥራ ባልደረባዩ ከነገሩን በኋላ ከአጥናፉ ጋር አብረው ወደአዲስ አበባ በረሩ። እንግዲህ ይህን ሁ ሉ ስንመለከት ሌፍተናንት ኰሎ ኔል አጥናፉ ጊዜያ ዊ ሥልጣን እንጅ ምንም መሠረት እንዳልነበረው እንረዳለን። አጥናፉን ተገን አድርገው በመንግሥቱና በሌ ሎቹ ፀረሕዝብ የደርግ አባ ሎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ የቃጡ ብዙ ነበሩ። ነገር ግን አጥናፉ ብዙ ዓይ ነት መከራ ዎችን እንዳከሸፈና እስከ ጊዜ ሞቱ ድረስ በመንግሥቱ ላይ አንድም ተን ኰል እንዳሰቀደ አያ ሌ ምልከቶች አሉ። መንግሥቱ ኃይለማርያም ግን አንድም ቀን እንዳልተኛለት ግልጽ ነበር። መንግሥቱ በአጥናፉ ሕይወት ላይ ለመፍረድ የተዘጋጀባቸው ምክንያቶች አሉ። አንዱ ምክንያት በአጥናፉ አካባቢ ያ ሉ መ ኰንኖችና፣ እንደዚሁም ምሁሮች፣ ፊውዳ ሎች፣ ኤርትራውያኖች፣ ይጠቀሙበታል ከሚል ፍራቻ ነበር። ከአጥናፉ ሞት በኋላ ሥልጣኑን አቶብቁበው ይጠባበቁ የነበሩ የደርግ አባላትም ግፊት እንደነበረበት የሞቱን ውሳ ኔ ድምጽ ከሰጡት ሰዎች መረዳት ይቻላል። በዚህም ምክንያት መንግሥቱ በአጥናፉ ላይ ሌ ሎቹን ካሳደመ በኋላ ራሱ ግን የሰጠው ድምጽ በሦስት እግራሞች ላይ የተከፋፈለ ነበር። ፩ኛ ጡረታ ይውጣ ፪ኛ ለትምህርት ወደውጭ ይሒድ ፫ኛ ከሥራ ይሰናበት የሚል ሲሆን የሞት ቅጣት ያልጨመረበት ምክንያት የሞት ቅጣት ነጥቡ ባዘጋጃቸው አክራሪ የደርግ አባ ሎች ድምጽ እንደሚወሰን ስለሚያውቅ ነበር። በዚህም መሰረት እንዲሞት ድምጽ ተሰጠ። ሆኖም አጥናፉ ሞቷል፣ መንግሥቱም ነግሷል፣ ታሪኩን እየዘረዘርን ከማለፍ በስተቀር ሌላ የሚደረግ ባለመኖሩ ነፍስ ይማር በማለት ይህችን አጭር ማስታወሻ መዝግበናል። የአጥናፉ የህይወት ታሪክ ይሄ ብቻ ነው ለማለት አይደለም። ሆኖም ለዚህ መጽሐፍ አስፈላጊ የመሰለኝን ለመመዝገብ ያተኮርኩበት የሁለቱ ዓመት ውጤት ነው።





## 4 ሌ/ ኰሎ ኔል ዳንኤል አስፋው

ሌ/ ኰ ዳንኤል አስፋው የደርግ አባል አይደለም። ነገር ግን በዚያው ግቢ ውስጥ ደርግ የሚያከናውናቸውን ሥራ ወች ለማስፈፀምና የደርጉንም ህልውና ለመጠበቅ የተመደበ የዘመቻ ክፍል ኃላፊ ነው።

በቀድሞው መንግሥት ጊዜ ተጨቆኖ ነበር የሚለው ዳንኤል የተጨቆነው በራሱ ሥነስርዓት ባለማክበርና አስፈላጊ ያልሆነ ፀባይ ለበላዮቹ ለማሳየት በወታደራዊ ሥነስርዓት አዘውትሮ ስለሚቀጣ ነበር። በዚህ መሠረት ለውጡ ከመጣ በኋላ የተሰጠውን ሥልጣን በመጠቀም ተቆጥሮ የማያልቅ ሕዝብ ፈጅቷል። ዳንኤል ከመንግሥቱ የበለጠ ወደር የማይገኝለት ጨካኝ ነበር። ብዙ የጦር አዛዦችን፣ ሚንስትሮችን፣ ተማሪዎችን፣ ምሁሮችን፣ ሲጨርስ በራሱ ውሳ ኔ እንጂ የሥልጣን ዕዝ በመጠበቅ አልነበረም። መንግሥቱም ቢሆን በዘዴ አስጠግቶ ሥልጣን በመስጠት ይህንን የመሰለ ወራዳና ቆሻሻ ተግባር እንዲሠራ ይገፋፋው ነበር።

ዳንኤል የደርግ አባል አለመሆኑ በጣም ይቆጫዋል። ስለዚህ አንድ ቀን በደርግ መንጋ መከከል መትረየስ ለማሽከከት የማያወላውል ዕቅድ ነበረው። ዳንኤል ከ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ጀምሮ አውቀዋለሁ። በለውጡ ጊዜ ግን ብዙ ይጠራጠረኝ ስለነበረ ለማሰር ወይም ለመግደል ብዙ ጥረት አድርጓል። ነገር ግን እኔን የሚያድኑኝ ብዙ ሁ ኔታዎች ስለነበሩ አልቻለም። ይህ አልበካ ቢለው በደርግ አባ ሎች ላይ ርምጃ ለመውሰድ በነበረው እቅድ እ ኔንም ወገን ለማድረግ ሞክሮ ነበር። እ ኔም በልዩ ዘዴ ከጠገቡ ለመመሸሽ ችያለሁ። በዚህም እቅዱ ብዙ መ ኰንኖችን እያስፈራራ እሱን እንዲደግፉት ያደርግ ነበር። ሌ/ ኰ አጥናፉም ከመንግሥቱ ጋር እንዲጣላ ብዙ ሞክሮ ለማ ቅረብ ሞክሯል። ግን ሁሉም ሰው በሰዳንኤል ተንኮል ሰላወቀ እስከሞተ ድረስ ብዙ መ ኰነኖች ይሸሹት ነበር። ሌ/ ኰ መንግሥቱንም እያታለለ አድብቶ አንድ ቀን በአፉ ጥይት ሊያ ጉርሰው የነበረው እቅድ ቀላል አልነበረም። ሆኖም ከዳንኤል ሥልጣን መያዝ ይልቅ መንግሥቱ በያዘው ሁ ኔታ ቢቆይ የሕዝቡን እልቂት ይቀንስል ብለን እንገምታለን።

የዳንኤልን ጭካ ኔና ግፍ በቅርብ የሚያውቁ አይገረሙም። እርግጥ የብዙ ደርግ አባላትንና የሌ ሎችን ኢትዮጵያውያን ሕዝብ ነፍስ ያጠፉ ከመሆ ኑም በላይ ከመጀመሪያው ጭካ ኔን በሰረገላ ሰብ ከደርግ የደም ሥር እንዲያሀድ ያደረገ ነው። ሌ/ ኰ ዳንኤል በጣም ጨካኝ ከመሆ ኑ የተነሳ በነበረው የጠቲት እንቅስቃሴ ውስጥ ለመጀመሪያ ሰው በመግደልና በማሰር ተግባር ለሌሎች ወታደራ ዊ ክፍሎች ምሳሌ የሆነ ሰው ነው። ዳንኤል ለስልጣን በጣም ስግብግብ ከመሆ ኑም በላይ ወገኖቹን ለማሰቃየት በጣም ቀራጥና ጨካኝ። የዕድሜው ማጠር ብቻ ወሰኝ ሆነ እንጂ በአጠቃላይ በደርግ

አባሎች በለሥልጣንነት በፍፁም አይስማማም ነበር። የዳንኤል ተግባር በየምዕራፉ የተገለፀ ስለሆነ ሙሉ ታሪኩ ከሌሎች መሰል ጓደኞ ከተግባራቸው ጋር ወደፊት በደምብ መጻፍ ያለበት ጉዳይ መሆኑን አብሬ ማስታወስ እወዳለሁ።





# 5 ብር/ ጀኔራል ጌታቸው ናደው

## የኤርትራ አስተዳደሪና የጦሩ የበላይ አዘዥ እንዳደሉ።

ብር/ ጀኔራል ጌታቸው ናደው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፍፃሜ አከባቢ በሐረር ክፍለ ሀገር በጅጅጋ አውራጃ ይገኝ የነበረውን የመከናይዝድ ብርጌድ በአዛዥነት ይመሩ ነበር። ደርግ ከተፈጠረ በኋላ ደግሞ የኤርትራ ክፍለ ሀገር አስተዳደሪ ሁነው ሰርተዋል።

የጀኔራል ጌታቸውን ታሪክ ለመግለጽ ያስፈለገበት ምክንያት ያገዳደላቸው ሁኔታ ምን ያህል ተንኮል እንዳለበት ለመግለጽ ያህል ብቻ ነው።

ጀኔራሉ ትጉህ ሠራተኛ ከመሆናቸው ሌላ ኃይለኛና ትዕቢተኛ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። የደርጉ አባላት ከሻለቃ በታች በመሆናቸው ንቀታቸውን በተለያየ ጊዜ በማሳየታቸው የደርጉ አባላት ይንቁናል በማለት በየጊዜው ያማርሯቸው ነበር። ብዙዎችም ለኮሚቴው አቤቱታ አቅርበዋል።

ከለውጡ በፊት ጅጅጋ በነበሩበት ጊዜ ጀኔራል ሐይሌ ባይከዳኝ ከሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጋር ተጣልተው በቀል ለመውሰድ በተዘጋጁበት ጊዜ ጀኔራል ጌታቸው ሻለቃ መንግሥቱን ያውቁት ስለነበር ወደኔ ይዛወር በማለት ከወሰዱት በኋላ ሹመት ተዘሎት ስለነበር የተዘለለውን ሹመት እንዲያገኝ ከረዱት ሰዎች አንዱ ናቸው።

ከለውጡም በኋላ ጀኔራል ጌታቸው በአዛዥነት የሰሩባቸው ክፍሎች የአየር ወለድና የሆለታ ጦር ትምህርት ቤት ጀኔራሉን ለመክሰስ ሲሯሯጡ ሻለቃ መንግሥቱ «የድር አዛዦችን እኮ ለምስክርነት ያስፈልጉናል» በማለት እንዳይከሰሱ አድርጎ እንዲያውም ወደ ኤርትራ በአስተዳዳሪነትና በዚያው ለሚገኘው ጦር ዋና አዛዥ ሆነው እንዲሰሩ ድጋፍን የሰጠ መሆኑ ግልጽ ነው።

ሌ/ ኰሎኔል ዳንኤል አስፋው ጀኔራሉን በጣም ይጠሉቸው ስለነበር የሻለቃ መንግሥቱን ድጋፍ ማግኘታቸው ያናድደው ነበር። ዳንኤል አስፋው የሚጠላቸው ደግሞ ጀኔራል ጌታቸው የአየር ወለድ አዛዥ በነበሩበት ጊዜ ብዙ ስለቀጡኝና በኋላም ከአየር ወለድ አስወጥተው ወደ በረና ስለቀየሩኝ ነው የሚል በውር ደባ ስለነበረው ከሰይ እንደተጠቀሰው ይሰሩባቸው የነበሩበትን ክፍሎች በመቀስቀስ አድማ በማስነሳት እንዲታሰ ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ነበር። ጀኔራል ጌታቸው ለሰነፍ ወይም ለወር በላ መኰንኖች ምቹ አልነበሩም። በህይወታቸውም ማመስገን አይወዱም ነበር፤ ነገር ግን ጉበዝ የሆነ የሥራ ዊቱ አባል ከቶ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያደርጋሉ። ይህን በሚመለከት ከለውጡ በፊት በአንድ የመኰንኖች ግብዣ ላይ ሻለቃ መንግሥቱን ጉበዝ ሰራተኛ ብለው ማመስገናቸው ይነገራል።

ወደ አገደደላቸው ሰንመለስ ደግሞ ጄነራሉ ለስራ ጉዳይ ተጠርተው ከአሥመራ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ በደብረዘይት የሚገኘውና በአሥመራ ያለው የአየር ወለድ ጦር ደርግ ሥልጣኑን ለህዝብ እንዲያስረክብ እና እንዲሁም የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርበው ከጄነራሉና ከሌሎች የደር አባለት ጋር ተፋጠው እንደነበር የሚታወስ ነው። ነገር ግን እመቴ በዚህ እንዳለ ጄነራል ጌታቸውም በተጠሩት መሠረት አዲስ አበባ ሄደው በስብሰባ ላይ ከዋሉ በኋላ ለምሰ ወደ ቤታቸው ሄዱ።

ሌ/ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ይህንን ሁኔታ በመጠቀም በግድያ ሙያ የሰለጠኑ ወታደሮች ነጠላና ኩት አስለብሶ ከኤርትራ የመጡ አቤቱታ አቅራቢዎች አስመስሎ በቀጥታ ቦሌ አካባቢ ወደሚገኘው የመኖሪያ ቤታቸው ላከ። እንደደረሱም ለሚጠብቁ ዘቦች «ከኤርትራ የመጣን እንግዶች ነን፤ አቤቱታ ስለለንም ከጄነራል ጌታቸው ጋር መነጋገር እንፈልጋለን» ብለው ሲጠይቁ ዘቡ በተጠየቀው መሰረት ለጄነራሉ አስታወቀ። እሳቸውም ሰዎችን ለማነጋገር ከቤታቸው ወጣ ሲሉ ወረቀት የሚያወጡ መስለው አውቶማቲክ ጠብመንጃቸውን አውጥተው ጄነራል ጌታቸው ናደውን ገደሏቸው። ዘቡም ተኩስ ከፍቶ አንዱን የአፉኝ ጓድ ሲገድል በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ዘቡም ተገደለ።

ወዲያውም ሌ/ ኮ ዳንኤል የግድያውን መሳከት እንደሰማ ታንከችን ወደ ጄኔራል ቤት በመላክ የጄኔራሉ እመፅ ከፍተኛ እንደነበር ለማስመሰል ሞከረ። በዚህም ብቻ አልተመለሰም። ሌ/ ኮ መንግሥቱና ለደርግ አባላት በሙሉ ጄኔራሉ የአየር ወለድን አፈንጋጮች ይዘው አመጽ ለማድረግ ሲሞክሩ ስለተደረሰባቸው እርምጃ ተወስዶባቸዋል አለ። ይህ ሲፈፀም ከዳንኤል በስተቀር መንግሥቱም ሆነ ሌሎች የደርግ አባሎች እጃቸውን አላስገቡም ተብሎአል።

ሁኔታውም የተፈጸመው ሐምሌ 1968 ዓ ም ሲሆን ስለጄኔራሉ መገደል ግን የተገለጸው በሌሎች አባሎች ላይ ግድያ በተፈጸመበት ከ8 ቀን በኋላ ነው። ይህም የተደረገው በፍርድ የተገደሉ ለማስመሰል የነበረ ሙከራ ነው። እነ ዳንኤል ብዙ የሠራዊቱ አባሎችንና ንፁህ ሰዎችን በእንዴት ያለ ዘዴ ይገድሉ እንደነበር ከሞላ ጐደል ለመግለጽ ተሞክሯል። የጄኔራሉ አገዳደል በብዙ ሰዎች ዘንድ አጠያያቂ ሆኖ የቆየውን በጥሩ ለማስረዳት እንደሚረዳ እምናለሁ።



ብ/ጀ ጌታቸው ፡ ናደው
የኤርትራ አስተዳደሪና
የጦሩ የበላይ አዛዥ





## በሸዋ ክፍለ ሀገር እምጸው ስለነበሩ ግለሠቦች

መርዕድ ብሩ
መስፍን ብሩ
ደጃዝማች ፀሐዩ እንቁሥላሴ
ብርጋዴር ጄነራል ተፈራ ደሜደሰ

መርዕድ ብሩና መስፍን ብሩ የራሥ ብሩ ልጆች ናቸው። መርዕድ ብሩ የተባለው በካናዳ ውስጥ ወታደራዊ ትምህርት ተምሮ በመቶ አልቃና ማዕረግ ተመርቆ እንደነበርና በዚህም ሙያው እንዳላገለገለበት ይነገራል። ሆኖም መርዕድ አሩሲ ክፍለሀገርና በሌሎች በታዎችም ጥምር እርሻዎች እያስሩፉ በዚህ ሙያው ይተዳደር ነበር።

ሁለቱም ወንድማማቾች በ1966 ዓ ም በመጣው ለውጥ የተስማሙ አይመስልም። በዚህም መሰረት ለውጡ እቅጣጫውን ከመቀየሩ በፊት በድብቅ ምግብና የጦር መሳሪያ በማጓጓዝ በመንዝና ግሺ አውራጃ ማከማቸትና ማደራጀት ጀመሩ።

የወንድማማቾች መሸፈት ለደርግ ግልጽ አልነበረም። ከነሱ ይልቅ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ሊሸፍቱ ነው፤ እህልም ወደ መንዝ በመኪና እያመላለሱ በማከማቸት ላይ ናቸው። የሚል ሪፖርት ይተላለፍ ነበር። የዚህንም አባባል እውነተኛነትን ልጃቸው ሻምበል ይጥና–ጋሻው ከበደ በሸዋ ፖሊስ ውስጥ የበራሪ ጓድ ሀላፊ ሆኖ እየሰራ በነበረበት ጊዜ የወሬውን እውነተኛነት ያብራራ ነበር። ነገር ግን በደርጉ የጥበቃ ክፍል በኩል ይህ ጉዳይ ሁለተኛ እንዳይነሳ ተብሎ ሲከለከል ሻምበል ይጥና–ጋሻው ከበደ ደግሞ እለቃውን ሌ/ ኮ ገብረትንሳይ የተባለውን በጥይት በመግደሉ ታስሮ ወደ ወህኒ ቤት ከገባ በኋላ የደጃዝማች ከበደ ተሰማ መሸፈት ቀርቶ በመርዕድ ብሩና በመስፍን ብሩ ላይ ብቻ ሪፖርት አተኩረ። በዚህ ጊዜ የሸለቃ መንግሥቱና የደጃዝማች ከበደ ተሰማ የዝምድና ግንኙነት ጨርሶ አይታወቅም ነበር።

ሻምበል ይጥና ከበደም ቢሆን ይህንን ግንኙነት የሚያውቅ አልነበረም። እኔም የሻምበል ይጥና–ጋሻው የቅርብ አለቃው ስለነበርኩ እንደዚህ ያለውን ሁኔታ ለማወቅ ችግር አልነበረብኝም። ለምሳሌ ያህል ከመታሰሩ ለምንት ቀን በፊት በ67 ዓ ም ተረኛ መኮንን ሆኖ አድር ጠዋት ወደ አባቱ ቤት ሳደርሰው እሱ ከመኪና ከመውጣቱ በፊት ሻለቃ መንግሥቱ ሻለቃ አጥናፉ አባተ ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳንና ሻለቃ ኪሮስ አለማየሁ ሁነው በፔጆ 505 መኪና ከመጡ በኋላ ወደ ደጃዝማቹ ቤት ገቡ፤ ሻምበል ይጥናም አባቱ ከመንግሥቱ ጋር ስላላቸው ግንኙነት አልገለጸልኝም። ሆኖም ሁልጊዜ እንደሚመጡ ነገረኝ። የደጃዝማቹም የመሸፈት ወሬ እነመርዕድ ሳይታወቁ እየተዘጋጁ እንዲቶኑ

ረድቷቸዋል።

መርዕድና መስፍን በአውራጃው እየተዘዋወሩ ህዝቡን በማሰባሰብ ለጦርነት እየተዘጋጁ ነበሩ። በደርግም በኩል መንዝና ግሼ ለአዲስ አበባ ቅርብ በመሆኑ አደገኛ ሁኔታ መሆኑን በመረዳት ከአየር ወለድ፣ ከፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ፣ ከሸዋ በራሪ ጓድ ፖሊስና ከብሔራዊ ጦር በማውጣት ወደቦታው ተላኩ።

ይህም ጦር መንዝ እንደደረሰ መርዕድና መስፍን ብሩ ህዝቡን በማሰባሰብ ውጊያ ገጠሙት። ጦሩም በድንጋይ ናዳና በጦርነት በደረሰበት ከባድ ጉዳት ብዙ ወታደር ተገደለ። ብዙውም ተበታተነ። በዚህ ዕለት የአየር ወለዱን ጦር የሚመራው ምክትል የመቶ አለቃ ከሲፋ ተገደለ። የግሸ አውራጃ አስተዳዳሪ የነበረው ሻለቃ በገደል ተገፍቶ ሞተ። በህዝቡም በኩል ከፍተኛ ጉዳት ደርሶ ነበር፤ ከሦስት መቶ የማያንሱ ሰዎች በአንድ ቀን ውጊያ ብቻ ሞተዋል። መርዕድና መስፍን ይህንን ጦርነት ከመሩ በኋላ ወደ ዋሻ ገብተው ተሰወሩ።

ደርግ በበኩሉም በጣም ደነገጠ። እነመርዕድ ለጥቂት ጊዜ በመደበቅ ራሳቸውን ስለሰወሩ በመሸበርና ራሱንም በማታለል አገር ለቀው በጅቡቲ በኩል ወጥተው እንግሊዝ አገር ለንደን ከተማ መታየታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ማሰወራት ጀመሩ። መርዕድና መስፍን ግን የትም ቦታ ሳይንቀሳቀሱ በዚያው በመንዝ ውስጥ እየተዘዋወሩ ህዝቡን ከማሰባሰባቸውም በላይ ወደ ወሎ እየገቡ ተመሳሳይ ሁኔታ እየፈጠሩ ነበር።

በኋላም በድንገት የመንዝና ግሸን ዋና ከተማን መሃል ሜዳን በመውረር በቦታው የሚገኘውን የተውጣጣ ጦር ከመደምሰሳቸውም በላይ በተማው የሚገኘውን የመንግሥት ንብረት አዘረፉት። እየማረኩ የወሰዷቸውን ወታደሮችም በስቅላት ቀጧቸው። ለደርግና ለተበታተነውም ወታደር ወረቀት ጽፈው በተኑ። ከተበተነው ጽሁፍ እማስታውሰው «እኛ ልዑል መርዕድና መስፍን መሐሪ ነን፤ ወታደሩ ሁሉ ለዚህ በረሃ እንዳይታዘዝ፤ ሁላችሁም እጃችሁን ስጡ» ይል ነበር። መርዕድና መስፍን ፀጉራቸውን ሹርባ ተሰርተው ነበር።

ደርግም ለጊዜው ጦር ስለሌለው ከመለዮ ለባሹ አውጣጥቶ የመጨረሻ ትዕዛዝ በመስጠት ወደ መንዝ ተላከ። የተላከውም ጦር በቀላሉ ድል ማድረግ አልቻለም ነበር። ከፍተኛ ውድቀት እየደረሰበት ውጊያውን ቀጠለ። ውጊያውም እየዋለ እያደረ ሲሄድ እነመርዕድ መቷቷም ስለቃታቸው ወዲያ በማፈግፈግ አብሯቸው ያለውን የህዝብ ጦር መሪዎች ወደሌላ አቅጣጫ እንዲሄዱ አድርገው እነሱ ግን አንድ ዋሻ ውስጥ ገብተው አደፈጡ። ሰዎች ወደሌላ አቅጣጫ እንዲሄዱ ያደረጉበት ምክንያት ጦሩ ከነዚያ ጋር ተሰቦ እንዲከተል ለማድረግ ነበር። ዕቅዳቸውም ትክክል ነበር። ነገር ግን አንድ ቄስ ከነሱ ጋር አብሮ የነበር በአንድ ቀጥቋጦ ስር ተሸጉጦ ተገኘና እነሱ የሄዱበትን አቅጣጫ መራባቸው። ከበባው በሄሊኮፕተር እየተቃኘ በአግረኛ ጦር እሰባው ቀጠለ። በዚህን ጊዜ እነመርዕድ ታይተናል ብለው በጦሩ ላይ ተኩስ ከፈቱ። ጦሩም አቅጣጫቸውን ከወቀ በኋላ ከበ በጥቅምት ወር 1967 ዓ ም ደመሰሳቸው።





ይህ ሁኔታ ለደርጉ ሪፖርት እንደደረሰው አንገታቸው ተቆርጦ ለመሀል ሜዳ ሰው በአደባባይ ከታየ በኋላ በአሰቸኳይ ወደ አዲስ አበባ እንዲላክ ለጦሩ አዛዥ መልዕክ አስተላለፈ። ሁሉም ነገር በደርግ ትዕዛዝ መሰረት ከተፈጸመ በኋላ አዲስ አበባም ለህዝቡ በቴሌቪዥን እንዲታይ ተደረገ። ሌላው ሰውነታቸው ግን እዛው ዋሻው ውስጥ እንደቀረ በቦታው የነበሩ ወታደሮች ገልጸዋል።

እነመርዕድ ከሰሩዋቸው ስህተቶች ውስጥ ጥቂቶች፦

- በጦርነት ብቻ የሚያሸንፉ መስሏቸው ነበር።
- ፖለቲካውን ምንም አልተመለከቱትም ነበር።
- በል ዩ ል ዩ ምክንያት እያ ኩረፉ ወደነሱ የተጠጉትን መለዮ ለባሾች ማታገል አልቻሉም።
- በውጊያ የማረኳቸውን ወታደሮች የቀጠሉበት መንገድ ሌላውን ወታደር ከማስቆጣቱም በላይ ወደነሱ በፈቃዱ እንዳይሄድ አድርጐታል።
- እነዚህን በሚመስሉ ሁኔታዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የትጥቅ ትግል የጀመሩትን መርዕድና መስፍን ብሩ ባጭሩ እንዲቀጭ ሆኗል። መስፍንትና መኳንንት የጦር አለቆችና ሌሎች አባቶቻችሁን እጃችንን ያዙን እያሉ በፍርሃት ለደርግ ሲያመለክቱ እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች የፈጸሙት ቆራጥነት ቀላል አለመሆኑና አሁን ከሚደረገው ህዝባዊ ትግል አንዱ አካል ነው ማለት ይቻላል።

## ደጃዝማች ፀሐ ዩ እንቁስላሴ

ደጃዝማች ፀሐ ዩ እንቁስላሴ የተባሉት የከፋ ክፍለሀገር እንደራሴ ነበሩ። በየካቲት 1966 ዓ ም የፈነዳው የህዝብ አመጽ ሳቢያ በስልጣናቸው ጊዜ ያስቃዩዋቸው ግለሰቦች ወታደሩና በጠቃላይም ህዝቡ በከፍተኛ ደረጃ ተነሳስቶ እጃቸውን እንዲሰጡ ተጠየቁ። ደጃዝማች ግን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ከፋ በሚገኘው ቤተ መንግሥት በር ላይ መትረየስ ጠምደው አሸፈረኝ አሉ።

በክፍለ ሀገሩ የሚካሄደውን አመጽ ይመሩ የነበሩ ሻለቃ ለሜሣ ሑሴ የሚባሉ የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አዛዥና የመቶ አለቃ አምሀ የሚባል የክፍለ ሀገሩ ፖሊስ የትምህርት ክፍል ሀላፊ የወታደሩንና የህዝቡን አመጽ አስተባብረው በደጃዝማች ላይ ከፍተኛ ህውከት ፈጠሩ። በኋላ ግን ከአዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ደጃዝማች ፀሐ ዩ አዲስ አበባ በድብቅ ሲገቡ አመጹን የመሩት ደግሞ በል ዩ ዘዴ አዲስ አበባ እንዲሄዱ ትዕዛዝ ስለተሰጠ በዚህ መሰረት ሰዎችም ተላኩ። የክፍለ ሀገሩ የፖሊስ አዛዥ ብ/ ጄ በረከት ገብረመድህንም ከደጃዝማች ፀሐ ዩ ጋር ተወንጅለው ወደ አዲስ አበባ ተላኩ። በኋላ ግን ወደ ከፋ ተመልሰው በደርጉ ትዕዛዝ ተገደሉ።

ደጃዝማች ፀሐዬም አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ንጉሡ ያሉበት ሁኔታ እሳቸውን ለማዳን ቀርቶ እራሳቸውንም ለመከላከል ያላቸውን ዕድል ከገመገሙ በኋላ ከወንድሞቻቸው ጋር ተመካክረው ለመሸፈት እንደሞከሩ፤ በንብረት መወረስ ላይ ከወታደራዊ ኮሚቴ የተሰጠው መግለጫ ስላሰጋቸው ወንድሞቻቸው ደግሞ ከመሸፈት ስለፈገፈጉ ነገሩን በመመልከት እሳቸው ብቻቸውን ለመሸፈት ወሰኑ። ከዚያም እያደዘው ቤተሰቦቻችሁ ደኅና ሆነው አይፈርዱላችሁም። በማለት ለወንድሞቻቸው የአሽሙር ቃል ከተናገሯቸው በኋላ ጉዟቸውን ሲቀጥሉ ታናሽ ወንድማቸው ፊታውራሪ ታደሰ እንቀበለሴ ከወንድሜ አልለይም በማለት አብረዋቸው መጓዛቸውን በዚያውጊዜ ተከታትለን ያገኘነው ዜና ነው።

ንጉሡም የደጃዝማችን መሸፈት በሰሙ ጊዜ እንዲመለሱ ጠይቀዋቸው ነበር። ደጃዝማች ፀሐዬ ግን የመለሱት መልስ ቢኖር «እስከዛሬ በሥጋዬ ሲያዙ ኑረዋል፤ ከእንግዲህ ግን በነፍሴ ማዘዝ አይችሉም» ጃንሆይ አሽከር ጌታውን ሲከዳ እንጂ ጌታ አሽከሩን ሲከዳ አልታየም፤ እረ ለመሆኑ ምን አደርጋለዎታለሁ? ባሪያዎ ፅእ በማለት በድፍረት ተቃውመው ጉዟቸውን እንደቀጠሉ ታውቋል።

ደጃዝማች ሽፍትነቱን ተያይዘው በተወለዱበት አካባቢ በመርሀቤቴ ግና በመዘዋወር ላይ እንዳሉ ህዝቡ በሥልጣን ላይ እያሉ ያልጠየቁን አሁን በምን ትዝ አልንዎት በማለት ጥያቄና አምቢተኝነቱን አስታወቀ። እሳቸውም የመርሀቤቴን ጉዟቸውን ትተው በሰላሌ አውራጃ በእንሳሮ ወረዳ በወበራ ምክትል ወረዳ እየተዘዋወሩ ህዝቡን ለማስተባበር ቢሞክሩም የምኞታቸውን ያህል የህዝብ ድጋፍ ስላላገኙ ህይወታቸውን ለማቆየት ብቻ ከወንድማቸው ከፊታውራሪ ታደሰ ጋር ሆነው ከአንድ ቤት ውስጥ እንዳሉ በአካባቢው ፖሊስ አዛዥ ህዝቡ ከበ እጃቸውን እንዲሰጡ ቢጠየቁ አሻፈረኝ ብለው የተኩስ መልስ ስለሰጡ በሐምሌ ወር 1966 ዓ ም የመጀመሪያው ተገዳይ ሆኑ። ወንድማቸውም እጃቸውን ስለሰጡ በሄሊኮፕተር ወደ አዲስ አበባ ተልከው ከታሰሩ በኋላ ከ60ዎቹ ባለሥልጣኖች ጋር ተረሸኑ። «የፍየል ወጠጤ» የሚለው ቀረርቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ደርጉ ሰው ሲገድል የመግለጫ ማርሽ አደረገው። በደርጉ ከተገደሉ ባለሥልጣንም ይሁን ተራ ሰው እሬሳ ለቤተሰብ የተሰጠውና የተቀበረው የደጃዝማች ፀሐዬ የመጀመሪያና የመጨረሻ ነው።

ደጃዝማች ፀሐዬ የጉጂም ክፍለ ሀገር እንደራሴ በመሆን ለረጅም ዓመታት ስለሰሩ በሳቸው አስተዳደር ያልተስማማ ሰው ሁሉ ብዙ ችግር ይደርስበት ስለነበርና በጠቅላላውም የጉጂም ህዝብ በጥብቅ ይጠላቸውና ያምጸባቸው ስለነበር አስከሬናቸው ወደ ጉጂም ተልኮ ህዝቡ እንዲያየው ለማድረግ ደርጉ አስቦ እንደነበር ይነገራል። የጉጂም ህዝብ ግን ደጃዝማች ፀሐዬን የምንፈረደቸው በህይወታቸው እንጂ በበድናቸው አይደለም። ስለዚህ ደጃዝማች የፈፀሙት ጀግንነት ሁላችንንም የሚያኮራ ስለሆነ በክብር እንዲቀበሩ እንጂ ወደ ጉጂም እንልካለን የምትሉትን አንቀበልም። በማለት ተቃውመዋል። እንዲያውም አስከሬናቸው ለቤተሰቦቻቸው እንዲመለስ የተደረገበት ዋናው ምክንያት የጉጂም ህዝብ





ተቃውሞ መሆኑን ደጃዝማች በሞቱበት ወቅት በደርግ አባሎችም ሆነ ቅርብ ለሆኑ ምንጮች ተሰምቷል።

## ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ይሔይስ

ብ/ ጄ ተፈራ ይሔይስ እስተገደሉ ድረስ መሸፈታቸው አይታወቅም ነበር። የሸፈቱትም በየረርና ከረዩ አውራጃ በሸንኮራ ወረዳ ከሰም ቀበና ከተባለ ጫካ ውስጥ ነበር።

ጄኔራሉ የተደበቁበት ቦታ እስቸገሯቸው ወይም ምግብና ውሀ ፍለጋ ይሁን ሌላ ነገር ከጫካው ወጥተው ሲዘዋወሩ ሁለት የከብት ጠባቂዎች ያገኙዋቸዋል። እሳቸውም ምግብና ውሀ ይጠይቃሉ። እነዚህ በግምት ከሰላሳ ዓመት የማይበልጡ ሰዎች ወደ አንድ ቤት አስገብተው ከስቀመጡዋቸው በኋላ ጄኔራሉን ለመግደል ይስማሙና ወደ ቤቱ ገብተው የያዙትን ምግብ ያቀርቡላቸዋል። ወዲያውንም በያዙት መጥረቢያ እራሳቸውን በመምታት በሐምሌ ወር 1967 ዓ ም ገደሏቸው።

ይህ ዜና ለደርጉ የዘመቻ መምሪያ እንደደረሰ ደርጉ በአስቸኳይ ሰዎችንና የጄኔራሉን መሳሪያ ወደ አዲስ አበባ እንዲላክ ይጠይቃሉ። በትዕዛዙ መሰረት አንድ ኤፍ ኤን ጠመንጃና አንድ ክላሽ ሽጉጥ ከሁለቱ ከብት ጠባቂዎች ጋር ወደ ሸዋ ፖሊስ መምሪያ ይላካሉ። ወዲያውንም ወደ ቤተ መንግሥት የደርጉ የዘመቻ መምሪያ ሰዎቹ ተልከው ከሌ/ ኰ ዳንኤል አስፈው ፊት ይቀርቡና በዳንኤ ተመስግነው ሽልማትም እንዲሰጣቸው ለሸዋ ፖሊስ ትዕዛዝ መጣ።

ሰዎቹ በሰጡት ቃል መሰረት የሸዋ ፖሊስ አባላት የጄኔራሉ አገዳደል ትክክል አይደለም በማለት ኰለኔል ዳንኤል ያዘዘላቸውን ጠመንጃ ሳይሆን በጣም ያረጀ መሳሪያ ያስጥይት ሰጥተው አሰናበቷቸው። ሰዎቹም ተደናግጠው በሀዘን ወደመጡበት ተመልሰዋል።

የጄኔራል ተፈራ ይሔይስ አሟሟት ትክክለኛ ታሪክ ይሄ ብቻ ነው። ነገር ግን ደርጉ ጄኔራሩ በህዝብ ላይ እንዲመጹና ብዙ ጦርም ዘምቶባቸው የተገደሉ አስመስለው ለህዝቡ ገልጸዋል። ሆኖም ጄኔራሉ በፍርሀት ወይም የሰው ምክር ሰምተው ወደ ጫካ የገቡ ይመስላል። በደርጉም ሆነ በሌሎች ክፍሎች የሚፈለጉ አልነበሩም። ስለዚህ የጄኔራል ተፈራ ይሔይስ ትክክለኛው ሁኔታ ይህ ስለሆነ ምናልባት ቤተሰቦቻቸው ያልተረዱ ከሆነ ለማወቅ ይረዳል ከሚል ሀሳብ በመነሳትና እንደዚሁም እነዚህ ከብት ጠባቂዎች የፈፀሙትን ጭካኔ ምን ያህል እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ከዚህም ሌላ በዚህ ለውጥ ምክንያት በደርጉም አረመኔያዊ ትዕዛዝ በእንደዚ ባለ ተልካሻ ምክንያት ብዙ ሰዎች ሳይታወቁ በጫከውና በገደሉ ወድቀው እንደቀሩ መረዳት ይቻላል።

## ርዕስ

የኢትዮጵያ መሰዮ ለበሽ ቅድመ ሁኔታ
የበረና ጦር እንቅስቃሴ
የአዲስ አበባ መኩንኖች እንቅስቃሴ
የኮንጉ ዘማቾች እንቅስቃሴ
የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሰራዊትና ብሔራዊ ጦር
የንጉሡ ከዙፋን መውረድና መታሰር
ንዑስ ደርግና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት
ደርግና ጄኔራል አማን አንዶም
ንጉሡ በእስር ቤት ዘመናቸው
የደርጉ የውስጥ ችግር
የነጄኔራል ተፈሪ በንቲ አገዳደል
ተወሳሰበው የቆዩ ሁኔታዎችና
የኢማሌድህ ግንባር
የሽብር ፈጣሪ ቡድን
የራዛ ዘመቻ
የነበልባል ጦር
በደርጉ ውዥንብር የተፈጸሙ ስህተቶች
የግለሰቦች ሚና
ኰሎኔል ዓለም ዘውድ ተሰማ
ብፁ አቡነ ቴዎፍሎስ
ሌ/ ኰ አጥናፉ አባተ
ሌ/ ኰ ዳንኤል አስፋው
ብ/ ጄ ጌታቸው ናደው
እነ መርዕድ ብሩ
ደጃዝማች ፀሐዩ እንቁሥላሴ
ጄኔራል ተፈራ ይሄይስ